# ዲሞክራሲያዊ የለውጥ እርምጃዎች እንድምታዎች እና አማራጮቻቸው በኢትዮጵያ

ቅጽ አንድ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies

# ዲሞክራሲያዊ የለውጥ እርምጃዎች
# እንድምታዎች እና አማራጮቻቸው
# በኢትዮጵያ

## ቅጽ አንድ

## ሕገ-መንግስት፣ ብሔር-ተኮር ፌደራሊዝም፣የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሕዝባዊ ምርጫ

2012

**አርታኢዎች**

አበበ አሠፋ

ክቡር እንግዳወርቅ

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

FORUM FOR SOCIAL STUDIES (FSS)

© 2012 ዓ.ም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
አዲስ አበባ
ማንኛውም የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው

ISBN: 978-99944-50-71-9

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
ፖ.ሳ.ቁ. 25864 ኮድ 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ኢሜይል፡ fss@ethionet.et
ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org.et

ይህ መጽሐፍ የታተመው በናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲ (National Endowment for Democracy) የገንዘብ ድጋፍ ነው በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን፣ የድርጅቱን አጋሮችና የገንዘብ ድጋፍ የሠጠውን ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲ አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቅ ይችላል።

# ማውጫ


*መቅድም* ........................................................................................iii

*መግቢያ* ........................................................................................v

**ሕገ-መንግሥት፣ ብሔር-ተኮር ፌደራሊዝም እና ፖለቲካዊ ሪፎርም**

የኢትዮጵያ ፌዴራል ስርዓት አመሠራረት መነሻ ዕሳቤው ችግሮቹና የዜግነት መብት .............................................................. 1

*አሰፋ ፍስሀ*

የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም እንዲሰራ ስለማድረግ ....................................... 29

*ዘመላክ አይተነው*

**የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕዝባዊ ምርጫና የሕዝብ ውክልና በኢትዮጵያ**

የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕዝባዊ ምርጫና የሕዝብ ውክልና በኢትዮጵያ............. 47

*ካሳሁን ብርሀኑ*

የውክልና፣ፖለቲካ ሀገራዊ ምርጫ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ ...... 67

*ዮናስ አሸኔ*

## መቅድም

**ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ** (Forum for Social Studies-FSS) በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ልማታዊ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ጠለቅ ያለ ጥናትና ምርምር የሚያካሂድ፤ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውይይት እንዲያደርጉ መድረኮችን የሚያዘጋጅ መንግስታዊ ያልሆነና ለትርፍ ያልተቋቋመ ሀገር በቀል የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅት ነው። የድርጅቱ እንቅስቃሴ በመንግስት ፖሊሲ አውጪዎች፣ አስፈጻሚ የመንግስት አካላት፣ ምሁራንና ተመራማሪዎች፣ የሲቪል ማኅበራትና በአጠቃላይ በህብረተሰቡ መካከል በአገራዊ ጉዳዮች ላይ በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሠረተ፣ ግልጽና ቀና ውይይት ማድረግ ጤናማ የውይይት ባህልን ከማዳበርና ግልጽና አሳታፊ የፖሊሲ ቀረፃና ትግበራ ስርዓትን ለማስፈን ከማስቻሉ ባሻገር ለአገር ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት፣ ለዴሞክራሲ መዳበርና ለዜጎች ዕኩልነት መስፈን ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል በሚል ዕምነትና መርህ ላይ የተመሠረተ ነው።

ድርጅቱ ከሚያካሂዳቸው የጥናትና ምርምር ስራዎች በተጨማሪ ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን የሚያዘጋጅ ሲሆን፤ በመድረኮቹም የመንግስት ፖሊሲ አውጪዎችና አስፈጻሚዎች፣ የሲቪል ማኅበረሠብ አካላትና ተመራማሪዎችን ጨምሮ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በወቅታዊ አገራዊ የልማት ጉዳዮች ላይ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ግልጽ፣ ገንቢና አሳታፊ ውይይቶች ያደርጋሉ።

ድርጅቱ ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት ብዛት ያላቸው ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ሕብረተሰቡን ሲያሳትፍ የቆየ ሲሆን፤ የነዚህን የውይይት ወጤቶችን በተለያዩ ህትመቶችና የብዙሀን መገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት ለህዝብ ተደራሽ ሲያደረግ ቆይቷል። ይሁን እንጂ በ2001 የወጣው የኢትዮጵያ በጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ በጣለው ገደብ ሳቢያ ድርጅቱ በአገራችን የፖለቲካና ፖለቲካ ነክ ጉዳዮች ላይ የሚያደርገው የጥናት፣ ምርምርና ሕዝባዊ የውይይት መድረክ ስራዎች ተቀዛቅዘቀው መቆየታቸው ይታወሳል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በአገሪቱ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የፖለቲካ ሪፎርምና በመንግስት የተወሰዱ እርምጃዎች ይህንን ተቀዛቅዞ የነበረ ስራ ዳግም በመመለስ ረገድ በሁለት በኩል አስተዋፅዖ እንዳደረገ ይታመናል። የመጀመሪያው እርምጃ በሲቪል ማኅበራት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ገደብ አስቀምጦ የነበረው አዋጅ መሻሻል ሲሆን፣ አሁን ተሸሻሎ በወጣው የሲቪል ማኅበራት አዋጅ (ቁጥር 113/2011) ቀደም ሲል የነበሩት ስራ መስኮች ገደብ ተነስቶ ማንኛውም የሲቪል ድርጅት በየትኛውም

ሕጋዊ ሥራ ላይ የመሠማራት ሙሉ መብት ሰጥቷል፡፡ በዚህ ምክንያት በፖለቲካና ፖለቲካ ነክ ጉዳዮች የምናደርገውን የጥናት፣ ምርምርና ሕዝባዊ የውይይት መድረክ እንቅስቃሴዎች ለመቀጠል ችለናል፡፡ በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ከ2010 ጀምሮ ዘርፈ-ብዙ በሆነ የፖለቲካ ሪፎርም ሂደት ውስጥ ያለች ከመሆኗ አንፃር ሪፎርሙ ቀደም ሲል ያልተነሱ ውይይትና ክርክርና የሚያስፈልጋቸው ወቅታዊ ሁኔታዎችን ይዞ መምጣቱ የፖለቲካና ፖለቲካ ነክ ጉዳዮች ላይ የሚደረገውን ሕዝባዊ የውይይት መድረክ ዳግም ለማንሰራራት ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሯል፡፡

በመሆኑም ***ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ*** ወቅታዊውን የአገራችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታን በሚመለከት ***ዲሞክራሲያዊ የለውጥ ጉዞ በኢትዮጵያ፡- የለውጥ ዕርምጃዎች፣ አንድምታዎቻቸውና አማራጮች*** በተሠኘ ርዕስ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን ቀርጾ አካሂዷል፡፡ የውይይት መድረኮቹ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተገኝተው በተመረጡ ወቅታዊ ርዕሶች ላይ የሚነጋገሩበት፣ ሀሳብ የሚለዋወጡበትና አማራጮችን የሚፈልጉበት መድረክ ለመፍጠር አስችሏል፡፡ በእያንዳንዱ የውይይት መድረክ ላይም ለውይይቶቹ በመነሻነት የሚያገለግሉ ጥናታዊ ጽሑፎች በየመስኩ በተሰማሩ ባለሙያዎች የቀረቡ ሲሆን፤ በነዚሁ ጥናታዊ ወረቀቶቹ ላይ ተመርኩዘው ተሳታፊዎች ሰፊ ውይይቶችን አካሂደዋል፡፡ የተካሄዱት ውይይቶችም በተለያዩ የሬድዮ ጣቢያዎችና ማሕበራዊ ሚዲያ አማካይነት ለሕዝብ እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ጥናታዊ ጽሑፎቹን በሕትመት ለህዝብ ለማድረስ ባለን ዕቅድ መሠረት ከተካሄዱት የውይይት መድረኮች መካከል በሁለቱ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች በመጽሐፍ መልክ ታትመው እነሆ ቀርበዋል፡፡ በተቀሩትም አራት መድረኮች ላይ የቀረቡት ጽሑፎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ታትመው ለሕዝብ የሚቀርቡ ሲሆን፣ በነዚህ መድረኮች ላይ ጥናታዊ ጽሑፎችን በማቅረብ፣ በአወያይነትና በተሳታፊነት የተሳተፉትን ባለድርሻ አካላትን በሙሉ ለማመስገን እወዳለሁ፡፡ በተለይ ይህን ሕዝባዊ የውይይት መድረክ እና ህትመት ለማዘጋጀት ያስቻለንን ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዲሞክራሲን (National Endowment for Democracy-NED) የተሰኘውን መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ከልብ አመሠግናለሁ፡፡

የራስወርቅ አድማሴ (ዶ/ር)

ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ

## መግቢያ

በኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ፖለቲካዊ ለውጦች ተካሂደዋል፡፡ እነዚህ ለውጦች በአመዛኙ በአገሪቱ በየወቅቶቹ በሠፈኑት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ሳቢያ የተከሰቱና የተሻለ ህይወት ለማስፈን የታለሙ ነበሩ፡፡ በእርግጥም ለውጦቹ በሕዝቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ልማታዊ ሁኔታዎች ውስጥ የተሻለ ሁኔታዎች አሳይተዋል፡፡ የቅርብ ጊዜ ለውጦች እንኳን ብንመለከት በ1983 ዓ.ም የደርግ መንግስት መውደቅን ተከትሎ የተካሄደው ለውጥ በአንፃራዊነት የተሻለ የፖለቲካ ስርዓት፣ የልማት ዕድገትና የኢኮኖሚ መሻሻል አስመዝግቧል፡፡ በኢኮኖሚ ረገድ አገሪቱ ባለፉት ሁለት ዓስርተ-ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ከማዝመግቧ በላይ ከ1998 እስከ 2008 ባሉት አስር ዓመታት የአገሪቱ ኢኮኖሚ የ10.3 ዕድገት ማሳየቱን የአለም ባንክ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ይሁን እንጂ ይህ እጅግ አመርቂ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ እንዲሁም ሠፊ የመሠረተ-ልማትና የማኅበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት ኢትዮጵያን በዓለም እጅግ ደሀ ከሚባሉት አገራት ተርታ አላወጧትም፡፡ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በኋላ-ቀር የአመራረት ዘዴ፣ በአየር ንብረት መዛባት እና በተለያዩ መዋቅራዊ ችግሮች በተተበተበው የግብርናው ክፍለ-ኢኮኖሚ ላይ የተንጠለጠለ ሲሆን፤ ክፍለ-ኢኮኖሚው ከግማሽ በላይ የሚሆነውን የአገር ውስጥ ምርት (Gross Domestic Product-GDP)፣ 83% የወጪ ምርትና 80% የስራ ዕድል ይሸፍናል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የገጠር መሬት እጥረትና መሬት አልባነት በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች በከፍተኛ ደረጃ ይስተዋላል፡፡

ተመሳሳይ ሁኔታ በአገር ውስጥ ካፒታልና የውጭ መዋለ-ንዋይን በመሳብ የኢንዱስትሪውን ክፍለ-ኢኮኖሚ ለማሳደግ የተደረገው ጥረት በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ የስራ ገበያውን ለሚቀላቀለው ስራ ፈላጊ የህብረተሰብ ክፍል በቂ ስራ ለመስጠት የሚችልበት ደረጃ ላይ ገና አልደረሰም፡፡ በዚህ ሳቢያ ስራ አጥነት በከተማም ሆነ በገጠር በከፍተኛ ደረጃ ይስተዋላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከቅርብ አመታት ወዲህ አንዳንድ ለልማት ተብለው የተወሰዱ ዕርምጃዎች በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የቅሬታ ምንጭ በመሆን ተቃውሞ አስነስተዋል፡፡ ለምሳሌ በከተሞች መስፋፋት፣ በኢንቨስትመንትና በልማት ሰበብ የእርሻ መሬቶቻቸውን የተወሰደባቸው ገበሬዎች የኑሯቸው መሠረት በነበረው መሬት መወሰድና የተሰጣቸው ካሣ አነስተኛ መሆን ለተነሳው የህዝብ ተቃውሞ አንዱ ዋና ምክንያት እንደነበር መጥቀስ ይቻላል፡፡

በፖለቲካው ረገድም አገሪቱን ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ሲያስተዳድር የቆየው ኢህአዴግ የተለያዩ ገዳቢ ሕጎችን በማውጣት፣ ለተቃዋሚ/ተፎካካሪ ድርጅቶች ማነቆ

በመፍጠርና የፖለቲካ ፉክክር መድረኩን በማጥበብ ሲወነጀል መስማት የተለመደ ነበር። እነዚህ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ከፍተኛ ሕዝባዊ ተቃውሞ በማስነሳት በአገሪቱ ከፍተኛ ቀውስ እንዲፈጠር ምክንያት ሆነዋል። የቀውሱ አሳሳቢነት በአስራ ስምንት ወራት ውስጥ ሁለት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እዲታወጅም ምክንያት ሆኗል። ችግሩ ስር ነቀል ዕርምጃ የሚፈልግና በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ ገዢው ፓርቲ የተለያዩ ስር ነቀል የፖሊሲ ዕርምጃዎችን ለመውሰድ ተገድዷል። በሂደቱም የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ስልጣናቸውን ለቅቀው ዶ/ር ዐቢይ አህመድ በቦታቸው ተተክተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይም ወደስልጣን ከመጡ ጀምሮ የተለያዩ እርምጃዎችን የወሰዱ ሲሆን ቀደም ሲል የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች ያሏቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ወደአገር ውስጥ ገብተው እንዲንቀሳቀሱ እርምጃ መወሰዱ፣ ከኤርትራ ጋር የሠላም ስምምነት ሒደት መደረጉ፣ እንደ ምርጫ ቦርድና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመሳሰሉት ተቋሞች ላይ ተቋማዊ ማሻሻያዎች መጀመሩ እና የተለያዩ መብት ገዳቢ የነበሩ ሕጎች ላይ ማሻሻያ መደረጋቸው የለውጡ ዓቢይ ዕርምጃዎች ተደርገው ይጠቀሳሉ።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ምናልባትም ከዚህ ቀደም ባልተለመደ ሁኔታና መጠን በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የለውጥ ሒደት ውስጥ ትገኛለች። አገሪቱ ባለፉት ሁለት አስርተ-ዓመታት ያስመዘገበችው ኢኮኖሚያዊ ዕመርታ እንደተጠበቀ ሆኖ በተቃራኒው የመልካም አስተዳደር ዕጦት፣ እየተስፋፋ የመጣው የከተማና የገጠር ስራ አጥነት፣ ፍትኃዊ የሀብት ክፍፍል አለመኖርና የፖለቲካ ምኅዳር መጥበብ የለውጥ ሒደቱ እንዲመጣ ካስገደዱት ምክንያቶች መካከል በዋናነት ይጠቀሳሉ። ይሁን እንጂ ለውጡ ወዴት አቅጣጫና በምን ፍጥነት መጓዝ ይኖርበታል? ምን ምን ጉዳዮችን ማካተት ይገባዋል? እንዲሁም የአገሪቱ የወደፊት ሁኔታስ ምን መምሰል ይኖርበታል? በሚሉ ኃሳቦች ላይ ገና ሙሉ በሙሉ አገራዊ መስማማቶች ተደርሷል ተብሎ አይገመትም። በመሆኑም የተጀመረው አገራዊ ለውጥ የበለጠ ፍሬያማ እንዲሆን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃሳቦች የሚንጸባረቁባቸው የጋራ መድረኮች የማዘጋጀትና ውይይት የማካሄድ አስፈላጊነት አያጠያይቅም።

በመሆኑም ***ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ*** የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ተገኛኝተው የሚወያዩባቸው፣ የሚመክሩባቸውና አማራጮችን ላይ የሚከራከሩባቸው ሕዝባዊ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀትና በማካሄድ ለአገራዊ የፖለቲካ ሪፎርሙ መሳካት የበኩሉን ለመወጣት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። የውይይት መድረኮቹ ከግንቦት ወር 2011 ጀምሮ እስከ ሕዳር ወር 2012 ዓ.ም ድረስ ባሉት ስድስት ወራት የዘለቁ ሲሆን ውይይቶቹም በሦስት አቢይ ክፍሎች የተከፈሉ

ነበሩ። እነዚህም 1) ***ፖለቲካ፣ ሕገ መንግስትና ሕገ-መንግስታዊ ተቋማት ግንባታ***፣ 2) ***አገራዊ ኢኮኖሚ ፖሊሲ*** እና 3) ***የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ*** ነበሩ። በእያንዳንዱ ዓቢይ ርዕስ ስር ሁለት ሁለት የውይይት መድረኮች ተካሂደዋል። በእያንዳንዱ መድረክም በመስኩ የጠለቀ ዕውቀትና የስራ ልምድ ያላቸው ሁለት ሁለት ምሁራን የውይይት መነሻ ጽሑፎች እንዲያቀርቡ ተድርጓል። አቅም በፈቀደ መጠን የሚቀርቡት ጽሑፎች የሁሉንም ባለድርሻ አካላት አቋሞች የሚያንጸባርቁ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል።

በመድረኮቹ የቀረቡት ጽሑፎችም ከመወያያ አዳራሽ ባሻገር በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለሕብረተሰቡ እንዲደርሱ ጥረት ተደርጓል። በተለያዩ የኤሌክትሮኒክና ህትመት ሚዲያዎች እና ማኅበራዊ ሚዲያዎች በተከታታይ ከሚቀርበው በተጨማሪ ጥናታዊ ጽሑፎቹ አርትዖት ተደርጎባቸው በሕትመት በየዐቢይ ርዕሶቹ ዘርፍ በሦስት ተከፍለው እንዲቀርቡ ታቅዷል። በዚህ መሠረት የመጀመሪያው ዐቢይ ርዕስ በሆነው ***ፖለቲካ፣ ሕገ መንግስትና ሕገ-መንግስታዊ ተቋማት ግንባታ*** ስር በሁለት የውይይት መድረኮች የቀረቡት ጽሑፎች በዚህ ቅፅ ቀርበዋል። ***ሕገ-መንግስት፤ ብሔር-ተኮር ፌዴራሊዝም እና ፖለቲካዊ ሪፎርም በኢትዮጵያ*** በሚል ርዕስ በግንቦት 29 ቀን 2019 ዓ.ም በተካሄደው የውይይት መድረክ በዶ/ር አሰፋ ፍስሀ እና ዶ/ር ዘመላክ አይተነው የቀረቡት ሁለት ጽሑፎች በዚህ ቅፅ ከተካተቱት መካከል ሲሆኑ፤ ዶ/ር አሰፋ በጽሑፋቸው በኢትዮጵያ የፌዴራል ስርዓትን ታሪካዊ መሠረት፣ የዜግነት መብቶችና የሀገር ግንባታ ሂደትን በመዳሰስ አሁን ያለው በብሔር ማንነት ላይ የተመሠረተ የፌዴራል ስርዓት አወቃቀርን ይተነትናል። እንዲሁም የዚህን ስርዓት አተገባበር፣ ያሉበትን ተግዳሮቶች እንዲሁም ተግዳሮቶቹን ለማቃለል መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች ያትታል። በማጠቃለያውም አሁን በመተግበር ላይ ያለው የፌዴራል ስርዓት ከታሪካዊ ፖለቲካዊ ችግር የመነጨና ውጤታማነቱን ባለፉት ሁለት አስርተ-አመታት በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መስኮች ያስመሰከረ በመሆኑ ወደኋላ ለመመለስ የማይቻል መሆኑን አጽንኦት በመስጠት፤ ነገር ግን አሁን ላለው የፖለቲካ ችግር የፌዴራልና የክልል መንግስታት የእርምት እርምጃዎችን በመውሰድ የዜጎች ህገ-መንግስታዊ መብቶች ሳይሸራረፉ የሚከበሩበትን መንገድ መቀየስ እንደሚገባቸው ያሳስባል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ዶ/ር ዘመላክ *ፌዴራሊዝም እንዲሰራ ስለማድረግ* በሚለው ጽሁፋቸው የፌዴራላዊ ስርዓት አወቃቀር በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ባለፉት ሀያ አመታት ውስጥ እጅግ አከራካሪ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋናው መሆኑን በማውሳት፤ ነገር ግን እንዚህ ክርክሮች አንድም በዕውቀት ላይ ባለመመስረታቸው

ወይም በጭፍን አመለካከት የተሞሉና የሌላውን የመከራከሪያ ነጥብ መመልከት የተሳናቸው በመሆናቸው ክርክሩ እምብዛም ፊቅ ማለት አለመቻሉን ያብራራሉ። ይሁን እንጂ ዛሬ የሚስተዋሉት አለም አቀፋዊና አገራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች የፌዴራል ስርዓትን አማራጭ የለሽ በማድረጋቸው ጥያቄው ምን አይነት የፌዴራል ስርዓት የሚለው ላይ ማጠንጠን ይኖርበታል በማለት ያስረዳሉ። በመጨረሻም በኢትዮጵያ የፌዴራል ስርዓቱ ላይ የሚታዩ ተቋማዊ ግድፈቶችን በመዘርዘር ሊወሰዱ ይገባቸዋል የሚሏቸውን እርምጃዎች ያብራራሉ።

በመጪው ግንቦት ወር 2012 ይካሄዳል ተብሎ በሚታሰበው አገራዊ ምርጫ ላይ ትኩረቱን ያደረገው ***የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሕዝባዊ ምርጫና የህዝብ ውክልና በኢትዮጵያ*** በሚል ርዕስ ሠኔ 27 ቀን 2019 በተካሄደው የውይይት መድረክ ላይ ፕሮፌሰር ካሳሁን ብርሃኑ ባቀረቡት ጥናዊ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ ከዳሰሱ በኋላ በኢትዮጵያ የህዝብ ውክልና በተለያዩ ስርዓተ-መንግስታት ስር ምን መልክና ይዘት እንደነበራቸው ይተነትናሉ። ቀጣዩ አገራዊ ምርጫ ለማካሄድ ሊሟሉ ይገባቸዋል የሚሏቸውን ድርጅታዊና ተቋማዊ ቅድመ-ዝግጅቶችን ይዘረዝራሉ። በማጠቃለያቸውም አሁን በሚታዩት ተቋማዊና ድርጅታዊ ችግሮችና በተለያዩ ቦታዎች በሚስተዋሉት አንፃራዊ አለመረጋጋቶች ሳቢያ፣ ተፎካካሪ ድርጅቶች በቂ ዝግጅት ለማድረግ ጊዜ ባለማግኘታቸውና በመሪው ኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል እየተካሄደ ባለው ለውጥ አካሄድ ላይ ገና መስማማት ላይ ባለመደረሱ ምርጫው በስምምነት ቢራዘም የተሻለ ነው የሚል ሀሳብ ይሰነዝራሉ።

በአንጻሩ ዶ/ር ዮናስ አሽኔ በጽሁፋቸው የውክልና ፖለቲካ፣ ምርጫና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ምንነትና ሚና፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አወቃቀር፣ አሰራርና ተግዳሮቶች ከተነተኑ በኋላ መጪውን ምርጫ በተመለከተ ‹‹ምርጫው መካሄድ አለበት፤ የለበትም›› የሚለው ክርክር ከሕግ፣ ከሕገ-መንግስት፣ ከፖለቲካ ዐውድና ከአስተዳደራዊ ጉዳዮች አንፃር መታየት እንዳለበት ያስገነዝባሉ። በማጠቃለያቸውም ከፕሮፌሰር ካሳሁን በተቃራኒ አሁን ምርጫውን ለማራዘም እንደሠበብ የሚቀርቡት መዋቅራዊና ተቋማዊ ችግሮች ውስብስብና በሂደት የሚፈቱ በመሆናቸው ምርጫውን ለማራዘም ምክንያት መሆን እንደሌለባቸውና ምርጫው በተያዘለት የጊዜ ሠሌዳ ቢካሄድ የተሻለ እንደሚሆን ያስገነዝባሉ።

በሚቀጥሉት ሁለት ቅፆች *አገራዊ ኢኮኖሚ ፖሊሲ* እና *የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ* በሚሉት ዐቢይ ርዕሶች ስር በተካሄዱት ህዝባዊ የውይይት መድረኮች ላይ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች በተከታታይ ታትመው የሚቀርቡ መሆናቸውን መግለጽ እንወዳለን፡፡

አርታኢዎቹ

# ሕገ-መንግሥት፣ ብሔር-ተኮር ፌደራሊዝም
# እና ፖለቲካዊ ሪፎርም

# የኢትዮጵያ ፌዴራል ስርዓት አመሠራረት፣ መነሻ ዕሳቤው ችግሮቹና የዜግነት መብት

አሰፋ ፍስሀ

ይህ ጽሁፍ የአገራችን የፌዴራል ስርዓት ታሪካዊ መሠረቱና ዕሳቤው፡ የፌዴራል ስርዓቱ ባህርያት፡ የተለያዩ ማንነቶች ከማዋሀድ/ከማቀፍ/ከማስተናገድ ረገድ ያሉትን የተለያዩ አማራጮች፣ ከዜግነት መብትና ከአገር ግንባታ ጋር (አንድ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ማህበረሰብ ከመፍጠር) ጋር ያለውን ትስስርና ሚና፣ ያጋጠሙ ችግሮች እንዲሁም ማጠቃለያና ምክረ-ሀሳብ የያዘ ነው።

## 1. የአገራችን ፌዴራል ስርዓት አመሰራረት ታሪካዊ መሠረቱ፡- የዜግነት መብትና ሀገር ግንባታ

አገራችን ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ለበርካታ ሺ ዓመታት የቆየች መሆኗ የሚያከራክር አይደለም። የዚህ በርካታ ሺ ዘመን ታሪክን መዳሰስ የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ባይሆንም የቆመበት ፖለቲካዊ መሠረትና የአገር ግንባታ ዕይታውን ባጭሩ መዳሰስ የግድ ይላል። ምክንያቱም እንደ አንድ አማራጭ ተደጋግሞ ስለሚነሳና አሁን ላለንበት ሁኔታም መሠረት ስለሆነ ነው። አሁን ያለንበት ሁኔታም ልናሻሽለውና ወደፊት መሄድ ይቻል ዘንድ መነሻውን ማየቱ የግድ ይላል። መነሻ መሠረቱ ጋር በተያያዘ አከራካሪና የተለያዩ እይታዎችም ስላሉ ወደ ክርክሩ ከመግባታችን በፊት የሀገር ግንባታ መሠረቱ ችግሮችና መፍትሔዎችንም ማየት የግድ ይላል።

እስከ ሀያኛው ክፍለ ዘመን መጀመርያ ድረስ የነበረው የአገራችን መንግስት የቆመበት የፖለቲካ ቅርጽ አንዳንድ ፀሀፊዎች እንደሚሉት ያልተማከለ ፊውዳል ስርዓት (devolved autocracy)[1] ብለው ይገልጹታል። ይህ ስርዓት በማዕከል ደረጃ የንጉሠ ነገሥት ስርዓትን ያቀፈ ሆኖ በስሩ የክፍለ ሀገር ነገስታትን ያቀፈና ይነስም ይብዛ እነዚህ የአካባቢ ነገሥታት ለንጉሠ ነገሥቱ ግብር በመክፈልና ታማኝ በመሆን የአካባቢያቸውን ጸጥታ፣ ሰላም፣ የንግድ ስርዓት ለመጠበቅ የተወሰነ ስልጣን የነበራቸው ነበሩ። እነዚህ የአካባቢ ነገሥታት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ልል የሆነ የፖለቲካ፣ የግብር፣ የጋብቻ ወዘተ ግንኙነት የነበራቸውና፤ አገር በውጭ ወራሪ ሀይል ሲወድቅና ንጉሠ ነገሥቱ የክተት ጥሪ ሲያቀርብም በስራቸው የሚገኘውን

---

[1] Christopher Clapham, 'The Ethiopian Experience of Devolved Government' *Ethiopian Journal of Federal Studies* v. 1 No. 1 (2013) p.18

የገበሬ ጦር በመምራት አገር ለማዳን በጦር ሜዳ መስዋዕት እስከመሆን ድረስ ለአገራቸው የተዋደቁ ናቸው። የንጉሡ ነገሥቱ ሥርዓት ሲታይ በአብዛኛው ከሰሎሞናዊ ስርወ መንግሥት የዘር ሀረግ (ትክክል ሆነም አልሆነ) የሚመዘዝ እንደሆነ እስከ 1966ቱ አብዮት የሥርዓቱ መሠረት ሆኖ ለረዥም ዘመን ቆይቷል። እንደ ንግስት ዮዲት ጉዲትና አህመድ ግራኝ የመሰሉ አልፎ አልፎ ሥርወ-መንግስቱን እስከ መቆጣጠር የደረሱ እንደነበረ የሚታወቅ ቢሆንም በዋናነት ንጉሠ ነገሥት ለመሆን የሠለሞናዊ የዘር ግንድ መጥቀስ፣ የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታይና (እስከ 1966 ዓ/ም ድረስ) ወንድ መሆን የግድ እንደሚል ከታሪክ ማየት ይቻላል። ስለዚህም የአገር ግንባታ ስርዓቱ ምሰሶ የሠለሞናዊ ዘር ግንድ ከክርስትና ኃይማኖት ጋር ተዳብሎ እንደነበረ ማየት ይቻላል። ይህ እንዳለ ሆኖ ከንጉሠ ነገሥቱ ስር በየአካባቢው የነበሩ ነገሥታት እንደ ሁኔታው የተለየ እምነትና የተለየ የዘር ግንድ እንደነበራቸው በምስራቅ (የሐረር፣አፋርና ሶማሌ፤ በምእራብ አምስቱ የጊቤ ነገሥታት፣ የጅማና ከፋ ስልጣኔ፤ በደቡብ የሲዳማ፣ ሀድያና ወላይታ የነበሩትን ስልጣኔዎች ማየት ይቻላል።

የዚህ ስርዓት ሌላው የአገር ግንባታ ምሰሶ የመሬት አስተዳደር፣ የጦርና የግብር ስርዓቱ ነው። የመሬት አስተዳደር ስርዓቱ ከቦታ ቦታ የሚለያይ ቢሆንም ግልጽ ስርዓትና የመንግሥት፣ የእምነት ተቋማት፣ የቤተሰብ፣ የማህበረሰብ፣ ወዘተ ይዞታ የሚለይ እንደነበረ ከታሪክ ሰነዶች ማየት ይቻላል። ይህ ስርዓት ከነችግሩም ቢሆን አገሪቱ ለዘረዥም ዘመን ነጻነቷንና አንድነቷን ጠብቃ እንትኖር የራሱን ሚና ተጫውቷል።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያና የ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ አካባቢ፣ በተለይም የዳግማዊ አጼ ምንሊክ ስርወ-መንግስት ወደ ስልጣን መምጣት ጋር ይህ ስርዓት በመሠረቱ ይቀየራል። ማዕከላዊ መንግሥት በየአካባቢው የነበሩትን ነገሥታት ከሞላ ጎደል በሀይል በመደፍጠጥ የነበራቸውን ውስን የፖለቲካ ነጻነት በማሳጣት በአብዛኛው ህዝብ የገባር ስርዓት (ማለትም በሀይል የተያዙት አካባቢዎች የነበረውን መሬት በመቀማት የሥርዓቱ አገልጋይ ለሆኑት ፊውዳል ታጣቂ ሀይሎች በመስጠት ነዋሪው ከመሬቱ ተነቅሎ የነሱ አገልጋይና ጪሰኛ እንዲሆን በማድረግ) በማወጅ ከሌሎች ነገሮች ጋር ተዳምሮ በሂደት በየአካባቢው ለተነሱት የገበሬ አመጾች (ትግራይ፣ ጎጃም፣ ባሌ) መነሻ ሆኗል። ከገባር ስርዓቱ ጋር ተዳምሮ 'አንድ ኃይማኖት (እስከ 1966 ዓ/ም ድረስ) አንድ ብሔራዊ ቋንቋ' (እስከ 1983 ዓ/ም ድረስ)[2] የሚል የማዕከላዊው መንግስት አገር የማቅናት ቅኝት ገዢው መደብ በተለያየ

[2] እንደኛ ባለ በርካታ ቋንቋዎች በሚነገሩበት አገር አንድ ቋንቋ ከሌሎች ተመርጦ ብሔራዊ ሲደረግ ሌሎች ቋንቋዎች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ወረዱ ማለት ነው። ከዚያም ባለፈ ቋንቋ ከመግባቢያነት ባለፈ ከባህልና ታሪክ ጋር የተያያዘ

አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ በሂደት 'የመደብና የብሔር ጭቆና' አድርሶብናል ለሚለው ትርክት መሠረት ጥሏል። እንደሚታወቀው በ1960ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ብቅ ያሉትና በማህበረሰቡ ዘንድ በስፋት የሚታወቁት የተማሪዎች ንቅናቄ በአፈታቱ ላይ መግባባት ላይ ባይደርሱም[3]፣ ካነገቡት ጥያቄዎች አንዱ የኢትዮጵያ የብሔርና የመሬት ጥያቄ መልስ ያግኝ የሚል ነበር።[4]

ማዕከላዊ መንግሥት እነዚህን በየአካባቢው የነበሩትን ነገሥታት ሲደፈጥጥና ሲያስገብር በሀይል ከመሆኑ ባሻገር የአገር ግንባታ ሥራው በህዝብ ፍቃድና ዛሬ እንደምናውቀው በዴሞክራሲያዊ መንገድ ስላልነበረ በበርካታ ወገኖች ዘንድ አወዛጋቢ ነገሮችን ጥሎ አልፏል። ከነዚህ አወዛጋቢ አመለካከቶች ጥቂቶቹን ለመግለጽ ያህል አንዳንዶቹ ሌሎችም ሀገሮች ሲመሠረቱ (ለምሳሌ ጀርመን በ19ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት በርካታ ያልተማከሉ የአካባቢ ገዢዎች ኦቶማን ቢስማርክ በሀይል በማዋሀድ 'through iron and blood' የዛሬዋ ጀርመን እንደ መሠረተች ሁሉ) በሀይል ስለሆነ አጼ ምንሊክ የሠሩት ነገር በተመሳሳይ መልኩ የተከናወነ፣ ምንም ስህተት ያልነበረበት 'የተለመደ አገር የማቅናት ስርዓት' ነው ሲሉ፤ በሌላ ወገን ይህ ሂደት ውስንም ቢሆን የፖለቲካ ነጻነት የነበራቸው አካባቢዎች በሀይል የመቆጣጠሩና የማስገበሩ ሂደት በአካባቢው ህዝብ ዘንድ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የባህል መገለል፤ በተጨማሪም ብዙ መስዋዕትነት ያስከፈለ ስለነበር 'ከቅኝ ግዛት'[5] ተለይቶ መታየት የለበትም የሚሉ ጸሀፊዎች ፈጥሯል። ሌሎችም ዕውነት ነው፣ በርካታ ሀገሮች ሲመሰረቱ አገር የመገንባት ሂደቱ እንደኛው በሀይል የተኪያሄደ ቢሆንም በጊዜ ሂደት ግን የፖለቲካ ስርዓቱን ዴሞክራሲያዊ በማድረግ በዜጎችና በመንግሥት መካከል የነበረውን የጌታና ሎሌ ግንኙነት በአዲስ የመንግስትና የዜጎች የፖለቲካ ቃል ኪዳን፣ ማለትም መንግሥት መሠረታዊ የሆኑትን አገልግሎቶችን (ለምሳሌ ጸጥታ፣ ገለልተኛ ፍትህ፣ የትምህርትና መሠረታዊ አውታሮች መዘርጋት የመሳሰሉትን) ሊሰራና የዜጎች መብት ሊያከብር፤ ዜጎች ደግሞ በበኩላቸው በየጊዜው በሚደረግ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ መንግስት ስልጣን ላይ እንዲቆይ ፈቃድ እንዲሰጡ በፊት በሀይል የተመሰረተው አገር በአዲስ መልክ ግንኙነቱ ወደ ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ ቃል ኪዳን ቀይረውታል። ከዚያም ባለፈ ከ1960 እስከ 1990ዎቹ አካባቢ፣ የአገር

በመሆኑ በዚያ ልክ ታሪካቸውና ባህላቸውም ወደ ሁለተኛ ደረጃ መውረድና በሂደቱም ወደ የመክሰም አደጋ ያስከትላል።

3 የተማሪዎቹ ማህበር የ1966 አብዮት ከመፈንዳቱ ጥቂት ዓመታት በፊት የብሔርና የመደብ ጭቆና መኖሩን ቢስማሙም፥ አፈታቱ በተመለከተ ገሚሶቹ ገገርውን መደብ በመደብ ትግል ይወገድ ሲሉ፥ ሌሎቹ ደግሞ በብሔር በመደራጀት ስርዓቱን እናስወግድ በሚሉ መሀል ልዩነት ፈጥረዋል።

4 በዚህ ዙርያ ዝርዝር ለሚፈልግ Bahru Zewde, The Quest for Socialist Utopia: The Ethiopian Student Movement 1960—1974 (James Currey 2014) ማየት ተገቢ ነው።

5 ለምሳሌ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የዚህ አስተሳሰብ ዋና አቀንቃኝ እንደነበር ይታወቃል።

ግንባታ ሂደቱ በሀይል የተደረገና እኛ አልነበርንበትም፣ የዚያም ሂደት ሰለባ ነን ለሚሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የፖለቲካ ስርዓቱን ክፍት በማድረግ በመንግስትና በነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል አዲስ አቃፊና ዴሞክራሲያዊ ግንኙነት እንዲመሠረት አድረገዋል (ለምሳሌ ስፔይን ከካታሎኛ፣ ካናዳ ከኩቤክ፣ እንግሊዝ ከሰሜን አየርላንድና ስኮትላንድ፣ ቤልጀም ከደች ተናጋሪ ማህበረሰብ)። የአገራችንም መሪዎች ይህን ማድረግ ነበረባቸው ከሚል እይታ አስተያየት ይሰጣሉ።

ስለዚህም የአገራችን የአገር ግንባታ ሂደት በርካታ ክርክሮች የሚያስነሳ ሆኖ እናገኘዋለን። እላይ ከተገለጹት ክርክሮች አኳያ በአገሪቱ የትምህርት ስርዓት ውስጥ የታሪክ ትምህርትና የማስተማሩ ሂደት በአብዛኛው የማዕከላዊ መንግሥትና ተቋሞች ትርክት ስለሚከተልና በየአካባቢው የነበሩት የተለያዩ ከፊል ራስ ገዝ ስልጣኔዎችና ህዝቦች ታሪክ፣ ባህል፣ ጀግኖች፣ አኗኗር የመሳሰሉትን በተሟላ መልኩ ስለማያካትት፤ ታሪኩም እንደ ፖለተካው አግላይ ነው በሚል የአገሪቱ ታሪክም ሲያወዛግብ ይታያል። ይህም ለአገር ግንባታ እንደ አንድ እንቅፋት ሲሆን ያታያል። ለዚህም ነው ታሪክ ሲጻፍም ሆነ ለትምህርት ሲውል፣ የሁሉንም ታሪክ ባቀፈ መልኩ ቢሰነድና ለትምህርት አገልግሎት ቢውል ሁሉም ዜጋ የኔ ነው ብሎ የሚቀበለው ስለሚሆን የጋራ ባለቤትነት ስሜት በመገንባት ለአገር ግንባታ የራሱን አወንታዊ ሚና ይጫወታል።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የነበረው የሀገር ግንባታ ቅኝት በሰለሞናዊ ስርወ-መንግሥት ትርክትና በክርስትና ኃይማኖት እንዲሁም በአንድ ብሔራዊ ቋንቋ የተቃኘ፣ በአንድ ፖለቲካ ማዕከል (extremely centralized unitary system) የተመሰረተ ስለነበር፣ በበርካታ የአገሪቱ አካባቢዎች ቅሬታ በመፍጠር በመጀመርያ የገበሬ አመጽ ቀጥሎም በአገራችን በስፋት በሚታወቀው የተማሪዎች ንቅናቄ አንግበውት የተነሱትን ህዝቦች ራሳቸውን የማስተዳደር መብት ይከበር፣ ህዝቦች በአገራቸው ጉዳይ ባይተዋር መሆን የለባቸውም፣ መሬት ላራሹ ወዘተ በሚሉ መፈክሮች የአገሪቱን ፖለቲካ ማነቃነቅ የጀመሩት። ስረዓቱም ለነዚህ መሰረታዊ የፖሊተካ ጥያቄዎች ተገቢና ወቅታዊ መልስ መስጠት ስላልቻለ የ1966 አብዮት በሀይል ገረሰሰው። የ1966 አብዮት በሠለሞናዊ ዘር ግንድና ክርስትና ኃይማኖት የተመሰረተውን የንጉሠ ነገሥቱን ስርዓት በመገርሰስ የመሬት ላራሹ ጥያቄም በመመለስ አዲስ ተስፋ መፍጠር ችሎ ነበር። ይህ በወታደራዊ መንግሥት የተመራው አዲሱ ስርዓት ይዞት የመጣው የአገር ግንባታ ስርዓት፣ የሁሉም ኃይማኖቶች እኩልነትን የሚቀበል፣ በአገሪቱ ሶሻሊስታዊ የፖለቲካ ስርዓት በመገንባት መደብ አልባና ሁሉም በእኩልነት በማስተናገድ፣ “ኢትዮጵያ

ትቅደም" በሚል መርህ መቃኘት ጀመረ::[6] ሆኖም በሂደት በአገሪቱ በየአቅጣጫው የሚነሱትን የፖለቲካ ጥያቄዎች (ለምሳሌ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም፣ የዜጎች መብትና ነጻነት ይከበር፣የህዝቦች ራሳቸውን የማስተዳዳር ጥያቄ መብት ይከበር) ተገቢ መልስ መስጠት ባለመቻሉና በተቃራኒው ለሚነሱት ጥያቄዎች ሰላማዊ ፖለቲካዊ መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ ሀይልና ወታደራዊ መፍትሄ መስጠት በመምረጡ፣ የእርስ በርስ ጦርነትና የበርካታ ህይወት ጥፋት ካስከተለ በኋላ በሀይል በ1983 የደርግ ውድቀትን አስከትሏል:: ስለዚህም በሶሻሊስታዊ ቅኝት የተመሰረተው የአገር ግንባታም የተወሰነ ጊዜ ከተንገዳገደ በኋላ መቀጠል አልቻለም:: የጋራ ባለቤትነት ስሜት መገንባት ይቅርና በሂደት የእርስ በርስ ጦርነቱ አካሄድ የአገሪቱንም ዕጣ ፈንታ አደጋ ውስጥ ከትቶት ነበር:: አደጋውን አስፈሪ የሚያደርገው ደግሞ መንግሥት ለውድቀት የዳረጉት ሀይሎች በብሔር የተደራጁና የታጠቁ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ የመገንጠል ዓላማም ያነገቡና ስርዓቱም መፈረካከሱ ነው::

በድህረ 1983 እየተተገበረ የሚገኘው አዲሱ አማራጭ (ከንጉሠ ነገሥቱን ስርዓትና ከሶሻሊስታዊ ስርዓት ሌላ ማለት ነው) የፌዴራል ስርዓት ነው:: በእንግሊዘኛው አገላለጽ nation building ተብሎ የሚታወቀው ጽንሰ-ሀሳብ፣ ታሪካዊ ምንጩና ይዘቱ በደንብ ሳይፈተሽ በደፈናው ወደ አማርኛ ተተርጉሞ አንዳንዴ 'አገር ግንባታ'፡ 'ብሔረ አገር'፡ 'ብሔረ መንግስት' ወዘተ የሚል አገላለጽ ጥቅም ላይ ሲውል ያታያል:: አጠቃቀሙ ላይ ያለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ በይዘት ደረጃም ጽንሰ-ሀሳቡ ራሱ ምንድነው የሚለውም በበርካታ ሰዎች ዘንድ ግልጽ አይደለም:: ስለዚህም የአማርኛው አጠቃቀምና ትክክለኛ ትርጉም ጥያቄ ከማንሳት በፊት የጽንሰ-ሀሳቡን ጉዳይ እንመልከት:: ዋናው ጥያቄ በርካታ ባህል፣ አመለካከት፣ ቋንቋ፣ ብሔር ብሔረሰብና ህዝብ እንዲሁም ማንነትን መሠረት ያደረገ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ወዘተ ባለበት አገር ውስጥ ሁሉንም ያቀፈ ብሔር ወይም ሌላ ማንነት ሳይደፈጥጥ፣ ለሀገርና ህዝብ አንድነትም አደጋ ሳይሆን፣ ፍትሀዊ የሆነ፣ የተዋሀደና ሰላማዊ ህዝብና አገር መፍጠር ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚል ጥያቄ ነው:: በሌላ አገላለጽ ሁሉም ዜጋ በአገሩ ላይ የባለቤትነት ስሜት ኖሮት፣ የኔ መንግስት ነው፣ የኔ ሰንደቅ አላማ፣ መዝሙር፣ ተቋም፣ ነው የሚለውን ስሜት ገንብቶ፤ የጋራ እሴቱን ጠብቆና ተንከባክበን ከብሔርና ሐይማኖት ማንነት በላይ (እነሱ ሳይደፈጠጡ) ሓገራዊ/ኢትዮጵያዊ/ዜግነት ማንነቱ መገንባትና በዚህ ሂደት ውስጥ ውጣ ውረድ ሲያጋጥም የማስተካከያ ስርዓት አበጅቶ የተሳሰረና የተዋሀደ ህዝብ መፍጠር ማለት

[6] የደርግ ስርዓት መጀመሪያና ወደ ማብቂያው አካባቢ በወቅቱ አንገብጋቢ ለነበሩት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ሲባል የብሔረሰቦች እኩልነት፡ እንዲሁም የራስ-ገዝ ስርዓት አውጆ የነበረ ቢሆንም ስርዓቱ ለሚነሱት ጥያቄዎች ከውይይትና ፖለቲካዊ መፍሔት ይልቅ የሀይልና ወታደራዊ አማራጭ የሚመርጥ ስለነበረ ውደቀቱን አቀላጥፎታል::

ነው። ከዚህ ሂደት ጋር የሚቀራረብ ግን ራሱን የቻለ ሌላ ጽንሰ ሀሳብ አለ፡ በእንግሊዘኛው አገላለጽ state building ተብሎ የሚታወቅ ወደ አማርኛው ሲተረጎም የተቋሞች ግንባታ ልንለው እንችላለን። በአንድ አገር ውስጥ አገሪቱን ከጠላት የሚጠብቅ ጠንካራ መከላከያ፣ የህዝቡን ሰላምና ጸጥታ የሚያረጋግጥ ጠንካራ ፖሊስ፣ ስርዓት በተቀየረ ቁጥር የማይናጋ የመንግስትን ፖሊሲ የሚፈጽምና ጥራት ያለው አገልግሎት ለህዝብ የሚሰጥ በብቃት ላይ የተመሰረተ የሲቪል ሰርቪስ ወዘተ ለአንድ አገር ወሳኝ ናቸው። የእነዚህ ተቋሞች መኖር በራሱ ለዜጎች እኩልነት መረጋገጥ ትልቅ ሚና እንዳለው የሚታወቅ ቢሆንም የሀገር ግንባታ ጽንሰ-ሀሳብ ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ከተቋሞች ግንባታ በላይ የሚሄድ ፤ በህዝብ ስነ ልቦናና አመለካከት ላይ በተለያዩ ፖሊሲዎች ተደግፎ (የቋንቋ፣ ባህል፣ ትምህርት፣ ሚድያ፣ ገንዘብና ሳንቲም ላይ በሚቀመጡ ምልክቶች፣ ብሔራዊ መዝሙር፣ ሁሉንም ያቀፈ ታሪክ ወዘተ- እነዚህ ፖሊሲዎች አቃፊ እንዲሆኑ በማድረግ) ህዝቡን የማስተሳሰርና የጋራ ባለቤትነትን ስሜት የመገንባት ሥራ ነው።

የሀገር ግንባታ ሥራ በተለይም እንደኛ ሕብረ ብሔር በሆኑ ሀገሮች ለረዥም ዘመን ሲያወዛግብና ሲያነጋግር ከመቆየቱ ባሻገር ይህ አይነት አገርና ህዝብ ለመፍጠርም ወጥ የሆነና ሁሉም የሚቀበለው አንድ አይነት መልስ ማበጀትም ከባድ ነው። ከፈረንሳይ አብዮት ጀምሮ እስከ 1970ዎቹ ድረስ nation building በሚል ቅኝት ሲተገበር የቆየው አካሄድ በኋላ እንደሚገለጸው ውጤቱ ተገልለናል ብለው በሚያስቡ ሀይሎች የመጨፍለቅና የመገለል አደጋ ስለፈጠረ በሂደት አመለካከቱ ተከልሶ ተገለናል የሚሉ ማህበረሰቦችንም በሚያቅፍ እና መልኩና ማንነታቸውንም በሚያስተናግድ መልኩ በአገር ደረጃ ተመጣጣኝ ውክልና አግኝተው በክልል ደረጃ ደግሞ ራሳቸውን የሚያስተዳደሩበትን ዕድል በማረጋገጥ የመጨፍለቁና የመዋጥ አደጋ በunity in diversity ተክተው አዲስ የአገር ግንባታ ስርዓትና ቅኝት መፍጠር ችለዋል። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በአሀዳዊ ስርዓት የሚኖረው የአገር ግንባታ ቅኝትና ባልተማከለ አልያም ፌዴራል በሆነ ስርዓት ውስጥ የሚኖረው የአገር ግንባታ ቅኝት የሚለያይ መሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል። በአሀዳዊ ስርዓት ውስጥ nation building ሲተገበር አውራ የሆነው ብሔር የራሱን መንግሥት፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ ግዛትና አሰራር በሌሎች ላይ የመጫንና አሀዳዊነትንና አንድ አይነትነትን መፍጠር ዓላማ ያደረገ ስለሚሆንና ይህ ደግሞ በርካታ ማንነቶችና በፖለቲካ የተደራጀ የብሔር እንቅስቃሴ ባለበት ሁኔታ የእርስ በርስ ጦርነት የመፍጠር አደጋ ስላለው አንዳንዶቹ እንደሚሉት( nation building becomes nation destroying).[7] "ሀገር ግንባታ ሀገር መናድ ሆናል" በሀገር ግንባታ ስም ዘር ማጥፋትን፣አንድን ብሔረሰብ ነጥሎ

[7] Walker Connor, 'Nation Building or Nation Destroying?' *World Politics* 24:3 (1972) pp. 319-355

የማጥቃት፣ በሀይል ወደ ሌላ ብሔር ማንነትና ባህል የመለወጥ እና የመቀየጥን የመሳሰሉ አያሌ ወንጀሎች በአነስተኛ ብሔረሰቦች ላይ ሲፈፀሙ ታይተዋል ። ዘመቻ ባንጻሩ ባልተማከለ አልያም በፌዴራል ስርዓት የሚኖረው የሀገር ግንባታ ስርዓት ሕብረ-ብሔራዊነትና በልዩነት አንድነት (unity in diversity) የሚያቅፍ ስለሚሆን በኢትዮጵያዊ/በሀገራዊ ማንነትና በብሔር አልያም ሌሎች ማንነቶች መካከል መኖር የሚገባውን ግንኙነት በህገ-መንግስት ወይንም በሌሎች ፖሊሲዎች ግልጽ በማድረግ ሁሉን ያቀፈና የሁሉም ባለቤትነት ስሜትን በማሳደግ ላይ ያለመ የሀገር ግንባታ ሥርዓት ይኖራል ማለት ነው። ለዚህም ብሔረ አገር፣ ብሔረ መንግሥት፣ nation building የሚሉት አገላለጾች ሁኔታውን በትክክል የመግለጽ ሀይል የላቸውም። በአንጻሩ የአሀዳዊውን አመለካከት መልዕክት ስለሚያስተላልፉ ህብረ-ብሔር በሆነ ማህበረሰብ የሀገር ግንባታ የሚለው የተሻለ ሁኔታውን ይገልጸዋል።

## 2. ኔሽን ስቴትና ጦሱ (The Nation State and Its Underlying)

ከፈረንሳይ አብዮት ጀምሮ እስከ 1960ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ገዢ የነበረው የአገርና ህዝብ ግንባታ ቅኝት ኔሽን ስቴት እና እ.አ.አ በ1950-1970ዎች መጀመሪያ አካባቢ ገዢ የነበረው አመለካከት ዘመናዊነት (modernization) እያደገና እየተስፋፋ ከሄደ ማለትም የከተሞች መስፋፋት የኢንዱስትሪ ዕድገት የመንግስትና የኃይማኖት መለያየት የዘመናዊ ትምህርትና ሳይንስ መስፋፋት ካለና የዜጎች መብት (በግለሰብ ደረጃ) ከተከበረ እንዲሁም በኢኮኖሚ ዕድገት ከተደገፈ ቋንቋ፣ ኃይማኖት፤ ባህል ወዘተ መሠረት ያደረጉ የማንነት መገለጫዎች ይከስማሉ አልያም ቀስ በቀስ ይጠፋሉ የሚል ነበር።[8] የዚሁ የዘመናዊነት ማስፈፀምያ ዋና ኃላፊነት ደግሞ "nation-state"[9]

---

[8] Cyril Black, The Dnamics of Modernization, a Study in Comparative History (New York: Harper and Row, 1966).

[9] The "nation-state" is widely associated with the rise of the European system of states, which began in Westphalia in 1648 and continued for the next 150 years, particularly so during the nineteenth century, when the emergence of popular sovereignty and self-determination led to the birth of nation-states. The nation-state replaced the different kinds of loose imperial and confederal political units that existed in Europe. Apart from insisting that there can only be one centre with undivided sovereignty and that it has to be homogeneous, this model prescribes that the nation and its political boundaries should match each other so that states can be nation-states. Genevieve Nootens, 'Can Non-Territorial Autonomy Bring an Added Value to Theoretic and Policy Oriented Analysis of Ethnic Politics?' in Malloy, Tove, and Francesco Palermo eds. *Minority Accommodation through Territorial and Non Territorial Autonomy* (Oxford: Oxford University Press, 2015) p.38. It claims 'the territorial boundaries of the state must coincide with the perceived cultural boundaries of a nation.' It required every state must contain within itself one and not more than one culturally homogenous nation, that every state should be a nation and that every nation should be a state.' Alfred Stepan, Juan Linz, Yogendra Yadiv, *Crafting State Nations: India and Other Multinational Democracies*, (Baltimore: The Johns Hopkins University Press, 2011), p 1. This political framework (with a few exceptions such as Switzerland, Belgium and the United Kingdom) remained as hegemonic regime and framework that many developing countries had to replicate. Yet it was largely a coercive process and the dominant nation imposed its norms on ethno national minorities, those left out of the process challenged it. As McGarry et al, argued, 'The coercive policies to achieve linguistic and cultural homogeneity in France to create a single French nation attests to the fear and concern that cultural difference would translate into political difference and thus has to be eliminated.' John McGarry, Michael Keating and Margaret Moore, 'Introduction: European Integration and the nationalities question' in John McGarry and Michael Keating eds., *European Integration and the Nationality Question*, (London: Routledge, 2006) pp.1-2. See also

ተብሎ በአውሮፓ የተፈለሰፈና ወደ ሌላዉ የዓለም ክፍል የተቀዳ ሞዴል ስርዓት ነው፡፡ ይህ ስርዓት "አንድ ብሔር (ተመሳሳይ ቋንቋ የሚናገር፣ ተቀራራቢ ባህል የያዘ፣ የራሱ ድንበር፣ መንግስትና የፖለቲካ ዓላማ ያለው) አንድ አገር" የሚለውን መፈክር ያነገበ ሆኖ በስሩ ሌሎች አናሳ ህዝቦች ቢኖሩ በዚሁ የዘመናዊነት ፍልስፍና በሂደት እየተዋጡ (ለምሳሌ በአሜሪካ) እየተመሳሰሉ (ለምሳሌ በፈረንሳይ) (Assimilate) በዋናው እየተዋጡ ይሄዳሉ የሚል ነው፡፡ ጥቂት ሌሎች አብነቶችን ትተን (ካናዳ፣ ህንድ፣ ስዊዝ፣ ቤልጂም ወዘተ) እነዚህ ሁለቱ ዋና ሞዴሎች ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ እጅግ በጣም ገራሚው ነገር፣ በርዕዮተ-ዓለም እጅግ የሚጻረሩ ሀይሎችም የርዕዮተ ዓለም ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በ1960ዎቹ አካባቢ አንድ ነገር ላይ ይስማሙ ነበር፡፡ ሶሻሊስቶች የብሔር ጥያቄን በጊዜያዊነት ቢቀበሉም፣ ቡርዥዋ ያሉት ስርዓት ከተገረሰሰና አለማቀፋዊ ሶሻሊዝም ከተገነባ በኋላ የማንነትና የብሔር ጉዳይ ጊዜያዊና የሽግግር ጊዜ ችግር በመሆኑ ይከስማል ብለው ያስቡ ነበር፡፡ እውነታው ግን ሌላ ሆኖ ብሔርተኝነት በሶሻሊዝም ውድቀት ላይ የተጫወተውን ሚና በቀድሞ ሶቭየትና ዩጎዝላቭያ ማስታወስ በቂ ነው፡፡ በሊብራልና ዘመናዊነት አቀንቃኞችም፣ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ የዜጎች መብት ከተከበረና አድልዎ ከጠፋ የአናሳ ማንነት በዋናው ብሔር እየተዋጠ መሄድ ያለቀ ጉዳይ ተደርጎ ተወስዶ ነበር፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ በምዕራቡም ዓለም ቢሆን በአገር ግንባታው ሂደት ተገለለናል የሚሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች መዋጥ ቀርቶ ለሀገሮች መፍረስ ምክንያት መሆን ሲጀምሩ ባለፉት 40 ዓመታት ህገ መንግስቶቻቸውን በማሻሻል የራስ ማስተዳደርን እና የተመጣጣኝ ውክልና ስርዓት ማወጃቸው አልቀረም (ለምሳሌ፦ በእንግሊዝ የስኮትላንድና ሰሜን አየርላንድ፣ ካናዳ ኩቤክ፣ በስፔን ካታሎኛ፣ ቤልጂም ደች ቋንቋ ተናጋሪዎች)፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ በአገር ግንባታ ሂደቱ ስልጣኑን የተቆጣጠረው ሀይል የአገሪቱ ብሔራዊ ቋንቋ፣ ዋና ዋና ምልክቶቹ፣ የሚድያና ሌሎች ፖሊሲዎች፣ ብሔራዊ መዝሙሩ፣ ታሪክ፣ ወዘተ ሌሎችን ባገለለ መልኩ የተቃኙ ስለነበሩና ተገልለናል ብለው የሚያስቡ የህብረተሰብ ክፍሎች ከስልጣንና ከኢኮኖሚ ከመገለልም በተጨማሪ የማንነት መገለል ደረሰብን ብለው ስለሚያስቡ፤ የአገር ግንባታ ሂደቱ እንደ አዲስ በመቃኘት በነዚህ ሀገሮች ሊብራል ስርዓቱ የግለሰብ መብት ከማክበርም ባለፈ የእነዚህ ተገለናል የሚሉትን ህዝቦች ለማክበርም የቡድንና ራስ ማስተዳደር መብት

Will Kymlicka, *Multicultural Odysseys: Navigating the New International Politics of Diversity (*Oxford: Oxford University Press, 2007) p.42.

ባካተተ መልኩ እንደ አዲስ ተቃኝተዋል::[10] እርግጥ ነው የሊበራል ስርዓቱ በዚህ ሂደት ውስጥ ቢያንስ በዚህ ጉዳይ ላይ ለሁለት መሰንጠቁ አልቀረም:: አንደኛው ክንፍ፣ ተገልለናል የሚሉ ማህበረሰቦች ጥያቄያቸው አሁንም በግለሰብ መብት ብቻ ይታይ ሲል፤ አዲሱ የሊብራል ቅኝት ግን ከዚያ ከፍ ባለ መልኩ እንዚህ ተገልለናል የሚሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እንደ ማህበረሰብ ራሳቸውን ማስተዳደር የሚችሉበትን ስርዓት እንዲሁም በማዕከል በሚኖሩ ተቋሞች ውክልና እንዲኖራቸው ማድረግ ወሳኝ ነው ሲል ያሰምራል::[11] ከዚያም ባለፈ የሊብራል ስርዓቱ በራሱ በአሜሪካና (አሜሪካ ትቅደም America First እና የፕሬዚዳንት ትራምፕ ወደ ስልጣን መምጣት ተከትሎም ከብዙ የአለም-አቀፍ ስምምነቶች መውጣትዋን አንዳንድ አውሮፓ ሀገሮች (BREXIT) ወደ ቀኝ አክራሪነትና ብሔርተኝነት መዞሩ ጉዳዩ የበለጠ አሳሳቢ አድርጎታል::[12] ስለዚህም 'ኔሽን ስቴት' አደጋ ላይ ነው እንኳን ባይባል በፊት ከነበረበት ይዘት ተሻሽሎ በአገር ግንባታው ሂደት ተገልለናል የሙሉ ማህበረሰቦች በሚያቅፍ መልኩ መቃኘት ከጀመረ 40 አመታት አልፎታል:: የአገር ግንባታ ቅኝቱ ዴሞክራሲያዊ በማድረግ በአዲስ ቃል ኪዳን ተገለናል የሚሉ ማህበረሰቦች ፍላጎት ለማቀፍ ዕድል በመስጠት የሀገሮችን ሰላም ማስቀጠል ችለዋል:: ለዚህም ነው የፌዴራል ወይም ያልተማከለ ስርዓት በአግባቡ ስራ ላይ ከዋለ፡-

1ኛ ስልጣንና ሀብት በሕገ-መንግስቱ በፌዴራልና በክልል በመከፋፈል፣

2ኛ ተገልለናል የሚሉ ወገኖችም ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ በማድረግ እና

3ኛ ህዝቦች በፌዴራል ደረጃ በሚኖሩት ተቋሞች ውስጥ ተመጣጣኝ ውክልና በመስጠት ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መሳተፍና ተጽዕኖ ማሳረፍ እንዲችሉ

---

[10] Sujit Choudhry ed. *Constitutional Design for Divided Societies* Oxford University Press (2009); See also Will Kymlicka, Multiculturalism (1995)፤ Kymlicka, Will, (2007), *Multicultural Odysseys: Navigating the New International Politics of Diversity.* Oxford: Oxford University Press.

[11] The new liberal camp has come up with many alternative options. Some like Arend Lijphart depending on the nature of the mobilized diversity (if found territorially dispersed) proposed a parliamentary system with a proportional electoral system where the different groups depending on the number of votes they secure in a democratic election will establish a coalition government. This approach further allows minority ethno national groups to have veto power over issues such as culture and language to reduce threat of majority tyranny. Others such as Donald Horowitz have proposed a presidential system where the president must win not only popular majority but as is the case in Kenya (since 2010) must also secure 25% of the votes in at least half of the 47 counties. A charismatic President (which is a rare commodity in Africa) that is popular beyond his ethnic base is hoped to serve as a unifying figure who also reaches out to minority concerns. This approach as seen in the constitutions of Nigeria and South Africa, recognizes the country as diverse but does not empower ethno national groups. There is as such one public identity. Yet this approach after being tried in Iraq post Sadam era failed because a Shite Presidential nominee could not get support from the Kurds and Sunni. So this model becomes a problem if there is deeply entrenched division and mistrust among the different communities. A more acceptable option when there are politically mobilized ethno national groups in the form of national liberation fronts has been the ones practiced in Belgium and to some extent in India, also Ethiopia where regional states are reorganized in such a way that the groups are granted political autonomy with representation in federal institutions. This approach also recognizes more than one public identity.

[12] Ghia Nordia, 'The End of the Post National Illusion' *Journal of Democracy* v.28 No. 2 (2017)፡ Francis Fukuyama, Why National Identity Matters, *Journal of Democracy* v.28 No. 4 (2018)

በማድረግ፣ የባለቤትነት ስሜት በማሳደግ ግጭትን በመቀነስ ለአገር ግንባታ ወሳኝ መሣርያ ተደርጎ የሚወሰደው፡፡

በዚህ ረገድ በአገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚሰማውን 'የዜግነት ፖለቲካ ብቻ' የሚለው አስተሳሰብ የዜግነት ፖለቲካ ለረዥም ግዜ ተረስቶ የነበረ በመሆኑና ክልሎችም በራስ ማስተዳደር ስም የዜጎች መብት አደጋ ውስጥ በማስገባታቸው እንዲሁም የፌዴራል መንግሥትም በዚህ በኩል ለሚታዩት ችግሮች ፖለቲካዊና ተቋማዊ መፍትሔ መስጠት ባለመቻሉ ጉዳዩ እንደ አጀንዳ መምጣቱ በጎ ነገር ቢሆንም እሱ ብቻውን ግን መፍትሄ ይሆናል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡

ከእላይ የገለጽነውን ሁኔታ ወደ አፍሪካ ስናመጣው በተለይም አፍሪካ ከቀኝ ግዛት ማብቃት በኂላ የተመሰረቱት መንግስታት ‹‹አንድ ቋንቋ፣ አንድ ፓርቲ፡ አንድ አገር" በሚል ቅኝት በመመራታቸው፣ ከሌላው ዓለም በከፋ መልኩ የዜጎች መብትም ሳይከበር፣ የኢኮኖሚ ዕድገትም ሳይመጣ ፖለቲካውም ሳይረጋጋ ህዝቦች መዋጥ/መመሳሰል ቀርቶ በማዕከላዊ መንግስት ላይ አመፅ በማንሳት የአፍሪካ አገራት በረዥም የእርስ በርስ ጦርነት ሲታመሱ መቆየታቸው (አሁንም ቢሆን) የሚታወቅ ነው፡፡ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኂላ ያልተማከለ አስተዳደርና የፌዴራል ስርዓት ለመተግበር ቢሞከርም በአምባገነን መሪዎችና በአውራ አልያም አንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት ስርዓት መውጣት ባለመቻሉ ሊሳካ አልተቻለም፡፡

በተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮች (ኢትዮጵያን ጨምሮ) ይታይ ለነበረዉ ግጭት መባባስ ምክንያት የሚሆነው አንድ ብሔር ብቻውን "50+1" የሚያሟላ አለመሆኑና የተለያዩ የፖለተካ ልሂቆች ሰፊ መሠረት ያለው መንግስት ከመመስረት ይልቅ አንዱ ለብቻው የፖለቲካ ስልጣን፤ ሀብት ለመቆጣጠር እና የዚሁ ልሂቅ ማንነት መገለጫ የሆኑትን ቋንቋ፤ ባህልና ኃይማኖት ወዘተ (አንዱ ወይም በጋራ) በሌላው ላይ መጫን ነው፡፡ ሆኖም ግን ‹ዘመናዊነት› ያልደረሰባቸው ሀገሮችና የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻ ሳይሆን ዘመናዊነትን ጥግ ድረስ ሄደውበታል በሚባሉት ሀገሮችም (ለምሳሌ አሜሪካ፤ ፈረንሳይና ካናዳ) ቢሆን ማንነትን መሠረት ያደረገ እንቅስቃሴ እየጠፋና እየተዋጠ ሳይሆን በተቃራኒው እየጎለበተ ለብዙ ግጭቶች ምክንያት መሆኑ ተስተውሏል ፡፡ በዚህ ረገድ ባለፉት 40 ዓመታት የተደረጉ ተደጋጋሚ ጥናቶች በዋናነት ይዘውት ብቅ ያሉት ነገር ቢኖር ማንነት በአግባቡ ካልተያዘና ተቋማዊና በፖሊሲ የተመሠረተ ፖለቲካዊና ኢኪኖሚያዊ መፍትሔ ካለተበጀለት ለብዙ ሀገሮች የግጭት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ተረጋግጧል፡፡[13]

[13] Kymlicka, Will, (2007), *Multicultural Odysseys: Navigating the New International Politics of Diversity.* Oxford: Oxford University Press; among others prominent figures predicted 'the end of history and the last man' and the triumph of liberalism but as later events proved the wave of democratization (Samule Huntington's third wave of

## 3. የአገራችን ፌዴራል ስርዓት

የፌዴራል ወይም ያልተማከለ ስርዓት ለአንድነትና ለአገር ግንባታ (ማለትም የተለያየ ማንነት፣ ባህል፣ ቋንቋ ፣ኃይማኖትና ፖሊተካዊና ኢኮነሚያዊ ጥያቄ ባለበት ሁኔታ ልዩነትን አቻችሎና እነዚህ የተለያዩ ፍላጎቶች አስተናግዶ፤ የብሔርና ሌሎች ፍላጎቶች ባንድ በኩል፤ ሀገራዊ አንድነትና የተሳሰረ ማንነት በሌላ በኩል ሚዛኑን ጠብቆ እንዲሄድ ማድረግ) ያለው ጠቀሜታ ብዙ የተባለለት ነገር አይደለም። እስከ አሁን ድረስ በተደጋጋሚ የሚሰማው ፌዴራሊዝም በሀገራችን ለነበረው በተማከለ ስርዓት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ችግር የእርስ በርስ ጦርነት ለመፍታት መሣርያ ነው ከሚለው በዘለለ ለህዝቦች ራስን የማስተዳደር ስልጣን ከማጎናጸፍ ባለፈ በህዝቦች ዘንድ የተሳሰረ ግንኙነት በመመስረት ለአንድነትና ለአገር ግንባታ ያለው ፋይዳ በደንብ አልተዳሰሰም። ይህም የሚባልበት ዋና ምክንያት ባለፉት ሁለት አስርተ አመታት የፌዴራል ስርዓቱ ዋና ትኩረት የህዝቦችን ራሳቸው የማስተዳደር ስልጣን ላይ በማተኮር ባህላቸውን፣ ማንነታቸውን፣ ታሪካቸውን ወዘተ በማሳደግ የባህልና የማንነት ተሀድሶ (ህዝቡ በየአካባቢው ባህሉንና ማንነቱን ከማሳደግ ባለፈ እንደ ሲዳማ ጨምበላላ ያሉትን በዩኔስኮ እስከ ማስመዝገብ ደርሰዋል) በአገሪቱ ላይ እንዲሰፍን ትልቅ ሚና የተጫወተ ቢሆንም አንዳንድ ታዛቢዎች እንደሚሉት 'ክልሎች የራሳቸውን ሙዚቃ ነው የሚያዳምጡት ስለ ሌላው ህዝብና ስለ ኢትዮጵያ የሚፈለገውን ያህል እያዜሙና እየሰሩ አልነበረም' የሚለው በተወሰነ መልክ እውነታ አለው።

ሆኖም ግን ፌዴራሊዝም በአግባቡ ስራ ላይ ከዋለ ስልጣንና ሀብት በህገ-መንግስቱ መሠረት በፌዴራልና በክልል በመከፋፈልና ተገልለናል የሚሉ ወገኖችም ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ በማድረግና የራሳቸው ማንነት ከሀገራዊ/ኢትዮጵያዊ አንፃር ሚዛኑን በጠበቀ መንገድ በመቅረጽና በመምራት፤ እንዲሁም ህዝቦች በፌዴራል ደረጃ በሚኖሩት ተቋሞች (ለምሳሌ በአስፈጻሚው፡ በፌዴሬሽን ምክር ቤት፡ በሲቪል ሰርቪሱ ወዘተ) ተመጣጣኝ ውክልና እንዲኖራቸው በማድረግ ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በጋራ በመሳተፍና ተጽእኖ ማሳረፍ እንዲችሉ በማድረግ በአገራቸው ጉዳይ የባለቤትነት ስሜት በማሳደግና ብዝሃነትን በማስተናገድ እና ግጭትን በመፍታት መሳርያ ከመሆን ባለፈ የጋራ ቤቱን በጋራ በማሳደግ የጋራ ባለቤትነት ስሜት ከፍ እንዲል በማድረግ የአገር ግንባታ ወሳኝ መሣርያ ነው።

democracy) promised turned into wave of ethnic conflicts (Arend Lijphart 1998) in Former USSR, Yugoslavia and some 27 (three of them –Eritrea, South Sudan, Somaliland- from the Horn) new states were created since then.

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የአገራችን የፌዴራል ስርዓት ዋና መነሻ በገባር ስርዓቱና በአንድ 'ብሔራዊ ቋንቋ፣ አንድ ኃይማኖት' ቅኝት አሀዳዊ ስርዓቱ ያስከተለውን የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማንነት መገለል ለረዥም ዘመን በተለይም በ20ኛው ክፍለ ዘመን የርስ በርስ የጦርነት ምክንያት የነበረውን ህዝቦች ራሳችን እናስተዳደር፡ በሀገራችን ጉዳይ የመሳተፍና የመወሰን ስልጣን ይኑረን፣ ማንነታችን፣ ቋንቋችን ይከበር የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ያለመ ነው። ይህ ለመመለስ ሲባልም በ1987 የጸደቀው ሕገ-መንግስት የህዝቡን ማንነት መሠረት በማድረግ በዘጠኝ ክልሎችና ሁለት ከተሞች የተዋቀረ ነው።

የአገራችን የፌዴራል ስርዓት ከሌሎች በአፍሪካ ከሚገኙ የፌዴራል ስርአቶች ጋር በምን ይገናኛል በምንስ ይለያል የሚል ጥያቄ ይነሳል። የአገራችን የፌዴራል ስርዓት በህዝቦች ራስን የማስተዳደር ዓላማ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ አንድ ብሔር አንድ ክልል (በተለይም ኦሮምያ፣ አማራ፣ ሶማሌ፣ ትግራይ፣ አፋር፣ ሀረሪ፣ እንዲሁም በዞንና ልዩ ወረዳ መልክ በደቡብ ክልል[14] ፤ (አሁን እየተቀየረ ቢሆንም) አማራ ክልል የብሔረሰብ ዞኖች እንዲሁም ጋምቤላ ዞንና ልዩ ወረዳ ወዘተ) በሚል የተቃኘ ነው። ዋና መሠረቱም ለረዥም ጊዜ የቆየውን ጥያቄ፤ ማለትም ህዝቦች ራሳቸውን የማስተዳደር ስልጣን ማረጋገጥ ቀዳሚ ዓላማ አድርጎ የተነሳ ነው። እሳቤውም በርካታ የታጠቁ የብሔር ነጻ አውጭ ድርጅቶች በነበሩበት እና አገሪቱ በሽግግሩ ግዜ የነበረችበት ሁኔታ አሁን ስራ ላይ ያለውን የፌዴራል ስርዓት እንዲኖር አስገድዷል የሚል ነው። ባጭሩ በተማሪዎች እንቅስቃሴ አወዛጋቢ የነበረውን የብሔር ጥያቄ ለመመለስ ያለመ ነው። ይህ ከህገ መንግስቱ መግብያና አንቀጽ 8፣ 39 እና 46 በግልጽ ማየት ይቻላል።

በዚህ ረገድ በአገራችን ከቅርብ ግዜ ወዲህ የሚሰማውን (ዜጎች ምንም ቋንቋ ይናገሩ፡ የትኛውን እምነት ይኑራቸው፡ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ይኑሩ፣ የእኩልነት መብታቸው ተረጋግጦ፡ ያለምንም አድልዎ በአገራቸው ፖለቲካዊ፡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳይ የመሳተፍ መብትን ያረጋገጠ ስርዓት) የሚለው አስተሳሰብ የዜግነት ፖለቲካ ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው የነበረ በመሆኑና እንዲሁም ክልሎችም በራስ ማስተዳደር ስም የዜጎች መብት አደጋ ውስጥ በማስገባታቸው (ክልሉም፣ መሬቱም፣ በክልሉ የሚገኙ ተቋሞችም የዛ ብሔር የሞኖፖል ንብረት ብቻ አድርገው

[14] አንዳንድ ታዛቢዎች እንደሚሉት እስከ አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ዶ/ር አብይ አሕመድ መመረጥ ድረስ ክልሉ የተለያያዩ ማህበረሰቦችን ፍላጎት በማቻቻል ከሌሎች ክልሎች በተሻለ በርካታ የልማት መዕከሎች (ለምሳሌ ሀዋሳ፡ ሶዶ፣ ሆሳዕና፣ አርባ ምንጭ፣ ወራቤ ወዘተ) መፍጠር ችሎ ነበር። ይህ ማለት ግን ሁሉም የክልሉ ማህበረሰብ ደስተኛ ነበሩ ማለት አይደለም። ለምሳሌ አሁን በፍጥነት እየጋለ የሚገኘው የሲዳማ የክልልነት ጥያቄ በጥንቃቄና አንዳንዴም በሀይል ታፍኖ የነበረ ጉዳይ ነው። የሲዳማ የክልልነት ጥያቄ መመለስ ለሌሎቹም ማህበረሰቦች የሚከፍተው ተመሳሳይ ጥያቄ ሲታሰብ ደቡብ እንደክልል መቀጠሉ ያበቃለት ይመስላል።

በማሰባቸው) እንደ አጀንዳ መምጣቱ በጎ ነገር ቢሆንም ፤እሱ ብቻውን ግን መፍትሔ ይሆናል ብሎ ማሰብ ዓለምንና የአገሪቱን ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ በትክክል ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑ ያጠራጥራል። የዜግነት ፖለቲካ አስተሳሰብ ዋና መነሻ በእንግሊዝኛው civic nationalism የሚል ሆኖ ከፈረንሳይና አሜሪካ የተወሰደ ነው። ሀሳቡ የተለያዩ ትናንሽ ማንነቶች በትልቁ ብሔር እየተዋጡ ይሄዳሉ ከሚል ግምት የሚነሳና የዜጎች መብትና እኩልነት ከተረጋገጠ የቡድን መብት አያስፈልግም ወይም የለም የሚል ነው።[15] የአዲሱ ሊብራል አስተሳሰብ አራማጆች እንደሚሉት፣ ዜጋ ያለ ማህበረሰብ ዕሴት (ጎሳ፣ ብሔር ወዘተ) ራቁቱንና ብቻውን አይኖርም፤ በተለይም ደግሞ አግላይና ተገላይ ባለበት ሁኔታ የማይታሰብ ነው። የዜግነት ፖለቲካ አስተሳሰብ አንዳንዴ የፌዴራል ስርዓት[16] የሚቀበል ቢሆንም (ለምሳሌ አሜሪካ)፤ የፌዴራል ስርዓቱ ዋና ዓላማ የሕዝቦች ራሳቸውን ማስተዳደር የማይቀበል ሆኖ ስልጣን ባንድ ማዕከል ሲከማች የሚፈጠረውን የአምባገነንነት አደጋ ለመቀነስ ሲባል በጎንዮሽ እና (በሶስቱ የመንግስት አካላት) ከላይ ወደታች (በፌዴራልና የታችኛው መዋቅር) የተለያያ ማዕከል የመፍጠር ዓላማ የያዘ ነው። ዓላማው ከብዙ ማንነቶች አንድ ማንነት መፍጠር የሚያስብና ብሔርና ብሔረሰቦች ቢኖርም ለከፋፍለህ ግዛ[17] እንዲመች አንዱን ብሔር በሁለትና ከዛ በላይ በሆነ ክልል/ክፍለሀገር መክፈል ዓላማ ያነገበ ሆኖ፣ ወደኛ አገር ነባራዊ ሁኔታ ስናመጣው 'ኢትዮጵያና ዜግነት ይቅደም፣ የብሔር ማንነት ይውደም' የሚል ዕሳቤ የተሸከመ ነው። ለምሳሌ አፋር ክልልን እንደ ድሮው በወሎ፣በትግራይና ሀረርጌ ክፍለ ሀገሮች መበተን፣ ሌሎችም እንዲሁ ማድረግ ማለት ነው። ብሔርን መሠረት ያደረገ ሳይሆን ጂኦግራፊን መሠረት ያደረገ የፌዴራል ስርዓት ይኑር የሚለውም ከዚሁ የተያያዘ ነው። ይህ እንደኛ ባለ አገርና አንድ ማንነት ሳይሆን በርካታ ማንነቶች አለን በሚባልበት ሁኔታ ይሳካል ወይ ለሚለው ጥያቄ በተለይም ብሔር ማንነት ነፍጥ ባነገቡ ሀይሎች ወደ አደባባይ የመጣ ከመሆኑ ጋር ተዳምሮና አሁንም እነዚህ ሀይሎች፡ ያነሰ ሳይሆን የበለጠና ሰፊ የራስ መስተዳደር ስልጣን ይረጋገጥ በሚሉበት ሰአት (ለምሳሌ፡ የኦሮምያ ክልል በአመጹ ግዜ ጎልቶ ይነሳ የነበረው ጥያቄ፡ ክልሉ ራሱን የማስተዳደር ስልጣን ይከበር፡ የፌዴራል መንግስት ጣልቃ ገብነት ይቁም የሚል እንደነበር ይታወቃል) የብሔር መብቶችን በመደፍጠጥ የዜግነት ፖለቲካ ብቻ ለመጫን መመኮር የበለጠ አደጋ

15 በእንግሊዘኛው አገላለጽ አንዳንድ ጸሀፊዎች እንደሚሉት 'create one public identity out of many, not many identities.'

16 አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲ አመራርና ልሂቃን ፌዴራሊዝም እንቀበላለን ሆኖም ግን አከላሉ በጅኦግራፊ መሆን አለበት የሚባለው አስተሳሰብም የዚሁ አካል ነው።

17 ለምሳሌ በናይጀርያ ሀውሳ ፍሎኒ ተብሎ የሚታወቀው ህዝብ በአስር ክፍለሀገሮች የተከፋፈለ ነው። ዩርባው በሰባት ክፍለ ሀገር የተከፈለ ነው፡ ኢቦ በአምስት ክፍለ ሀገር የተከፈለ ነው። በደቡብ አፍሪካና በኬንያም ተመሳሳይ ዓይነት የአከላለል መርህ የተመሰረተ የፌደራል ስርዓቶች ይገኛሉ። ባንጻሩ ቤልጅየምና፡ ህንድ፡ የህዝቡን አሰፋፈርና ራሱን የማስተዳደር ጥያቄ መሰረት ተደርጎ የተዋቀረ ነው።

ሊያስከትል ይችላል። ከዚያም በከፋ የዜግነት ፖለቲካ አራማጆች በአብዛኛው አስተሳሰቡ ፋቅ ሲደረግ የተወሰነ ማህበረሰብ አመለካከትና ማንነት ብቻ የሚወክሉ በመሆናቸው ጉዳዩ የበለጠ አሳሳቢ ያደርገዋል። ለዚህም ነው ይህን አስተሳሰብ የሚተቹ የህብረተሰብ ክፍሎች የዜግነት ፖሊተካ በዜግነት ወይም በኢትዮጵያ ስም የተወሰን የህብተረሰብ ክፍል አመለካከትና ዕሴትን (ለምሳሌ ባህልና ቋንቋ) በሌላው ላይ ለመጫን የሚደረግ ሴራ ነው ሲሉ የሚሰሙት።

የአገራችን የፌዴራል ስርዓት ስራ ላይ መዋል ከጀመረ ጀምሮ በርካታ ስኬቶች ማስገኘት ችለዋል። አገራችን በ1983 የነበረችበትን የሰላምና የድህነት ደረጃ ሁሉም የሚገነዘበው ነው። በነበረው የርስ በስር ጦርነት ምክንያት ማዕከላይ መንግስት ተዳክሞ በብሔር የተደራጁ የተለያዩ ሀይሎች አዲስ አበባ ሲጠጉና የጎረቤታችን ሶማልያ መንግስት አልባ እየሆነ መምጣት እንዲሁም የወታደራዊ መንግስት ዋና አጋዥ የነበረው የቀድሞ ሶቭየት ህብረት መፈረካከስ አገራችንም የዚህ ዕጣ ፈንታ ለያጋጥማት ነው ወይ የሚል የበርካታ አገር ወዳድ ዜጎች ስጋት እንደነበረ ይታወሳል። አሁን ምንም እንኳ ባለፉት አራት አመታት ጠንከር ያሉ ችግሮች በመከሰታቸው የዚያ ዘመን ሁኔት ቢያስታውሰንም፤ አመጹ እስከ ጀመረበት ጊዜ ድረስ አንጻራዊ ሰላም ያላት አገር ማድረግን፣ ከ10 ዓመት በላይ የቆየ ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት ማረጋጋጥ መቻልን፡ በርካታ ትላልቅ የልማት ስራዎች ለምሳሌ ከፍተኛ ትምህርትና ጤና መስፋፋት፣ ትላልቅ የአስፋልት፣ የባቡር፣ አውሮፕላን ማረፊያ፤የኢንዱስትሪ ፓርክ ግንባታ ስራ መከናወን መቻልን ስናይ አገሪቱ በተሻለ ተስፋ መንገድ መጓዝ ጀምራ እንደነበር ያሳያል።

ከዚህም ባለፈ የርስ በርሱ ጦርነት ምክንያት የነበረውን የህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ጥያቄ ፡ ህዝቦች በአገራቸው ጉዳይ የመሳተፍና የመወሰን ጥያቄ፡ ለዘመናት ተዘንግቶ የነበረውን ማንነታችን ይከበር (የቋንቋ፡ የባህል፡ የኃይማኖት ወዘተ እኩልነት) በአገራችን ጉዳይ የመሳተፍና ፍትሀዊ ውክልና የማግኘት መብት በህገ መንግስት ደረጃ በመመለስ ከፍተኛ የሆነ የባህልና የማንነት ተሀድሶ በአገሪቱ እንዲረጋገጥ በማስቻል፡ ክልሎች የዛሬ 27 ዓመት የነበራቸውን አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ተቋሞች አቅም በከፍተኛ ሆኔታ ማሳደግ ተችሏል።

የአገራችን የኂላ ታሪክ እንደምናውቀው አንድ ጠንካራ መሪ ሲመጣ በዚያ ልክ ደህና እድገትና ሰላም ይመጣል ። በግልባጩ ደግሞ ደካማ መሪ ሲመጣ የርስ በርስ ጦርነትና የኂልዮሽ ጉዞ ይጀመራል። ታሪካችን እንዲህ ወጣ ገባ የበዛበትና ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር፤ እንዲሁም መሪዎች ተቀየሩም አልተቀየሩ ሳይናጉ የሚሰሩ ተቋሞች መፍጠር አልተቻለም። በዚህ ረገድም ቢሆን ምንም እንኳ የነጋናን ያህል ስልጣን ከአንድ ፓርቲ ወደ ሌላ ፓርቲ ሰላማዊና በምርጫ በሚደረግ ስልጣን ሽግግር

ማስተላለፍ የሚቀረን ቢሆንም፣ ከ1983 ጀምሮ ሁለት ጊዜ (ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ ህልፈት ተከትሎና የጠቅላይ ሚንስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ በፈቃደኝነት ከስልጣን መውረድ ተከትሎ) በሰላማዊ መንገድ ስልጣን ማስተላለፍ መቻል ዘመናዊ ኢትዮጵያ ብለን በምናውቀው ዘመን ለመጀመርያ ጊዜ የተደረገ መሆኑ አንድ ምዕራፍ ማለፍ መቻላችንን የሚያሳይ ነው። ጠንካራ ተቋሞች የመገንባት ስራ እንደተጠበቀ ሆኖ ገዢው ፓርቲ ይህ ማከናወኑ በአፍሪካ ውስጥ አሉ ከሚባሉት ጠንካራ ፓርቲዎች አንዱ ያደርገዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ የሚነሳው ነጥብ የፌዴራል ስርዓቱ ስልጣን በፌዴራልና በክልል በመዘርዘር በማከፋፈልና የሁለቱም አካላት በተሰጣቸው ስልጣን መወሰን መቻልን የሚያረጋግጥ ከሆነ ለምንድነው በየአካባቢው ከፌዴራል ስርዓቱ ጋር በተያያዘ አቤቱታና ቅሬታ የሚበዛው የሚለውን ማንሳት ተገቢ ነው። እንደሚታወቀው ህገ-መንግስቱ የሁለቱንም የመንግስት አካላት ስልጣን ይዘረዝራል። ለምሳሌ የውጭ ጉዳይ፣ መከላከያ፣ የውጭ ንግድ፣ አገር አቀፍ የሆኑ ፖሊሲዎችና ስታንዳርድ መቅረጽ ወዘተ ለፌዴራል መንግስት የተሰጠ ስልጣን ነው። በዚህ ረገድ ክልሎች በተሰጣቸው ስልጣን በፌዴራል ደረጃ ለአገሪቱ በጠቅላላ የሚወጡትን ሰታንዳርድ ሳይጥሱ ለአካባቢያቸው የሚመጥን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንዲሁም የልማት ፖሊሲ እስከ መቅረጽ የሚሄድ ስልጣን ተረጋግጦላቸዋል ። ሆኖም ግን ያለፉት ሁለት አስርተ አመታትን ልምድ ስናይ የፌዴራል ስርዓቱ ከዴሞክራሲዊ ማዕከላዊነት፡ ከልማታዊ መንግስትና ከአውራ ፓርቲነት ጋር ተዳምሮ ይፈጸም ስለነበር የራሱ የሆነ በጎና አሉታዊ ውጤት ፈጥሯል። በልማታዊ መንግስቱ መርህ አገራችን ለረዥም ዘመን የቆየውን የድህነት ችግር ለመውጣት ሲባል ፌዴራል መንግስት የልማት አቅጣጫውን በመቅረጽና በመምራት ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወት ስለነበር በኢኮኖሚው በኩል ተከታታይ እድገት ማምጣት ቢቻልም የክልሎችን የመወሰን ስልጣን ግን አደጋ ውስጥ ከትቶታል። አንዳንዴም ፌዴራል መንግስት ከሚገባው በላይ በመሄድ የክልልን ስልጣን ይወስድ ስለነበረ (ለምሳሌ መሬትን በተመለከተ ከትላልቅ እርሻ ልማት ጋር በተያያዘ ከ5000 ሄክታር የበለጠ እንደሆነ ማስተዳደሩ የክልል ስልጣን ቢሆንም በፌዴራል መንግስት መወሰዱ፣ በኃላ ቢሰረዝም) በክልሎች በዚህ ረገድ የነበረን ራስን የማስተዳደር ስልጣን በተወሰነ መልኩም ቢሆን ተደፍጥጧል የሚል ስሜት መፍጠሩ አልቀረም። የፌዴራል ስርዓቱ ሲጀመር ክልሎች ገና በአዲስ መልክ እየተዋቀሩ ስለነበር በሰው ሀይልና በሀብት በኩል ሰፊ ክፍተት ስለነበራቸው የተሰጣቸው ስልጣንም ቢሆን ተግባር ላይ ለማዋል ብዙ ጊዜ ወስዶባቸዋል። ከምንም በላይ ግን በርካታ ብሔር መሠረት አድርገው የተደራጁ ፓርቲዎች በነበሩበት ሁኔታ ከላይ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ

ፖለቲካዊ አመለካከት ተጠርንፈው ይንቀሳቀሱ ስለነበር የብሔር እንቅስቃሴው እንዳይገነፍል አስሮት ቆይቷል። ከላይ ወደታች የሚፈስ የውሳኔ ስርዓት ስለነበረም የክልሎችን የመወሰን ስልጣን አዳክሞታል። በዚህም ምክንያት የፌዴራል ስርዓቱ በሕገ-መንግስቱ የተገባውን ቃል በማያከብር መልኩ እውነተኛ ራስ መስተዳደር መረጋገጥ አለበት የሚል ጥያቄ መነሳት ከጀመረ ቆይቷል።[18] ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዚህ በኩል የተወሰነ የመሻሻል ምልክት ቢታይም ብዙም ሳይሄድ ተመሳሳይ ችግር የመድገም ሁኔታዎች ታይተዋል። የፌዴራል መንግስት የክልሎች ራስን በራስ ማስተዳደር አደጋ ውስጥ በሚከት መልኩ በአምስት ክልሎች መሪዎች እንዲቀየር አድርገዋል። እንደሚታወቀው ራስ ማስተዳደር ስልጣን የክልሉ ህዝብ መሪዎችን መምረጥና መሻር ስልጣን ያካትታል። ይህ አስገራሚ የሚያደርገው አዲሱ አመራር ወደ ስልጣን የመጣበት አንዱ ምክንያት የፌዴራል መንግስት በክልሎች የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት ያቁም በሚለው ሀይል ግፊት መሆኑ ነው። እዚህ ላይ መገለጽ ያለበት ነጥብ በአመጹ ጊዜ ጎልቶ የወጣው መልእክት ክልሎች ራሳችን የማስተዳደር ስልጣን እስከአሁን የነበረው ሁኔታ ትክክል ስላልሆነ በራሳችን ጉዳይ ለመወሰን ያነሰ ሳይሆን የበለጠ ነጻነት ያስፈልገናል የሚል የነበረ መሆኑ ነው።

በሌላ መልኩም ክልሎች ራሳቸውን በማስተዳደር ስልጣን ሰበብ ከላይ እንደተገለጸው የዜጎችን መብት ሲደፈጥጡ ይታያል። ከዚያም ባለፈ የስልጣን ክፍፍሉን በሚንድ መልኩ ክልሎች በውጭ ጉዳይም ከሌሎች መንግስታት ጋር ሲደራደሩና ሲዋዋሉ ይታያል። ባጭሩ በሁለቱም ጎራ (በፌዴራልም በክልልም) ስልጣን ክፍፍሉን የመጣስ አደጋ ይታያል ። ሲጣስም ገለልተኛ አካል ሕገ-መንግስቱ የበላይነቱን በሚያረጋግጥ መልኩ ብይን በመስጠት አካል ሲያስተካክል አይታይም። ከሌሎች የፌዴራል ስርዓቶች ልምድ ማየት እንደሚቻለው እንዲህ አይነት የስልጣን ክፍፍሉን አደጋ ውስጥ የሚከት ነገር ሲኖር ገለልተኛ በሆነ አካል የማስተካከያ ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል። በዚህም መንገድ የህግና የህገ መንግስቱ የበላይነት ይረጋገጣል። ይህን ሀላፊነት በብዛት በተለይም በአውሮፓ የሚወጡት ተቋሞች የሕገ-መንግስት ፍርድ ቤቶች ናቸው።

ከፌዴራል መርሁ ጋር በተያያዘ የሚነሳው ሌላው ነጥብ ክልሎች ራሳቸውን ከማስተዳደር በተጨማሪ በፌዴራል በሚኖሩ ተቋሞችም ተመጣጣኝ ውክልና የማግኘትን በፌዴራል ደረጃ በሚወሰኑ ጉዳዮችም ላይ የመሳተፍ መብት ያረጋግጣል ። በዚህ ዙርያም የውክልናው ስርዓት በፓርቲ ደረጃ የሚወሰን ስለነበር ፓርቲዎቹና

[18] **ለዝርዝሩ** Assefa Fiseha Federalism and Development: The Ethiopian Dilemma, *International Journal of Minority and Group Rights* v.25 No. 3 (2018) https://doi.org/10.1163/15718115-02503004; Assefa Fiseha "Theory versus Practice in the Implementation of Ethiopia's Federalism," in David Turton ed., *Ethnic Federalism: The Ethiopian Experience in Comparative Perspective* (Oxford: James Currey, 2006).

ተሿሚዎቹ እንወክልሀለን የሚሉትን ማህበረሰብ ፍላጎት ምን ያህል ይወክሉ ነበር የሚለው ጉዳይ አወዛጋቢ መሆኑ አልቀረም። በዚህም ይመስላል በበርካታ ክልሎች ከፖለቲካ ሂደቱ ተገልለናል የሚል ስሜት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣው። ስለዚህም ክልሎች በፌዴራል ደረጃ የሚወክላቸውን አመራር በነጻነት የሚመርጡበትን አሰራር ዳግም መፈተሽ ያስፈልጋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጥያቄ በሀገራዊ (ኢትዮጵያዊ ዜግነት) ስሜትና ማንነት ላይ ተመሥርቶ የሚነሳው የብሔርተኝነት ስሜት (sub state identityበኢትዮጵያዊነት) እና ብሔርተኝነት መካከል መኖር ስለሚገባው ግንኙነት ነው። አንዳንዶቹ ኢትዮጵያዊነት ወይም ሞት (Ethiopia first) በሚል መፈክር ለኢትዮጵያዊነት (ዜግነት) 100% በመስጠት ቋንቋ/ኃይማኖት/ክፍለ ሀገር፡ የትውልድ ቦታ ወዘተ የመሳሰሉት የማንነት መገለጫዎች ከፋፋይና ቦታ ሊሰጣቸው የማገባ ነው በማለት 0 (ዜሮ) ሲሰጡ ይታያሉ፤ ሌሎች ደግሞ ለብሔርተኝነት 100 ለኢትዮጵያዊነት ደግሞ 0 ይሰጣሉ ። ሆኖም ግን እነዚህ ሁለት ጽንፍ የያዙ የማንነት መገለጫዎች ናቸው። በአደጉት የፌዴራል ስርዓቶች (ስዊዝ፣ ካናዳ፣ ቤልጅም፤ ህንድ ወዘተ) ማየት እንደሚቻለው በኢትዮጵያዊነትና የብሔርተንነት መካከል የዜሮ ድምር (Zero sum) ግንኙነት የለም። በሌላ አገላልጽ ለአንዱ ዜሮ ለሌላው 100 ሲሰጡ አይታይም። በአንፃሩ የብሔርተኘነት ስሜት ራስነ የማስተዳደር መብትን (self rule in a federal state) በማክበር፤ የኢትዮጵያዊነት ስሜቱ ደግሞ በማዕከል በሚኖሩ የፌዴራል ተቋሞች (ህዝብ ተወካዮች ም/ቤት፤ ፌዴሬሽን ም/ቤት፤ ሲቪል ሰርቪስ፤ ፖሊስ፤ ወታደራዊ ተቋሞች አስፈፃሚ ወዘተ) ተመጣጣኝ ውክልና በመስጠት (Shared rule) ሁለቱም የማንነት መገለጫ ስሜቶች ተቻችለውና ሚዛናቸውን ጠብቀው በሰላም የሚኖሩበት ሥርዓት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በዚህ ጽሁፍ ሌላ ክፍል በግልጽ እንደተገለጸውም የተለያዩ የመንግስት ፖሊሲዎችም (የትምህርት፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ ሚዲያ፣ ታሪክ፣ መዝሙር፣ ሙዝየም፣ ብርና ሳንቲም ላይ የሚካተቱ ምልክቶች፡ ሀውልቶችና ጀግኖች ወዘተ) የተሳሰረ ማንነት በመገንባትና ሀገራዊ ምንነትንና የብሔር ማንነት ሚዛኑን ጠብቆ እንዲሄድ በማድረግ መሳርያ ሆነው መቀረጽና ማገልግል ይገባቸዋል። የብሔር ወይም ሌላ ማንነት በጋራውና በኢትዮጵዊ/ዜግነት ማንነት ጥላ ስር መቃኘት ያስፈልጋል። እስከ አሁን የመጣንበት መንገድ ይህን አማካይ መንገድ በግልጽ ቁልጭ አድርጎ አላስቀመጠም። በዚህ ላይ መግባባት ካለ የቅኝቱ ስራ ቀጥሎ የሚመጣ ይሆናል። የፌዴራል ስርዓት ዋና መገለጫ ባህሪ ተደርጎ የሚወሰደው እነዚህን ሁለት ስሜቶች/ማንነቶች በአግባቡ ማስተናገድ የሚችል መሆኑ ነው። በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችም ይህን ሁለት ማንነት ተቻችሎና ሚዛኑን ጠብቆ እንዲሄድ የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው። ዋናው

መታወቅ ያለበት ነጥብ የብሔር ወይም ሌላ ማንነት ከሚፈለገው በላይ አብጦ የጋራ የሆነውን ሁሉንም የሚያስተሳስረውን ኢትዮጵያዊ የጋራ ዜግነት መገፍተር ወይም መደፍጠጥ የለበትም ። የጋራ ዕሴቶችንም ማጎልበትና በጋራ ማራመድ እንጅ እሱን በሚያዳክም መንገድ እንዳይሄድ መስራት ያስፈልጋል። በተመሳሳይ መልኩ ከዚህ በፊት እንደነበረው ስርዓት ኢትዮጵያዊ ማንነትና ዜግነት ፖለቲካ ብቻ በመተኮር ሌሎች ማንነቶች ማፈን ችግሩን መድገም ይሆናል። ይህ እንዳይሆን ትምህርት ቤቶች፣ ሚድያ፣ ሲቪል ማህበረሰቡ፣ ክልሎች እና የፌዴራል ተቋሞች የማያቋርጥ ህዝቡን የማስተሳሰርና የሀገር ግንባታ ስራ መስራት ይኖርባቸዋል። የሀገር ግንባታ ስራ በብዙ መንገድ ሊሰራ የሚችል ቢሆንም የተለያዩ መንገዶች በመጠቀም፡ ዜጎችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ በአገሪቱ ጉዳይ ላይ የባለቤትነት ስሜትን የመፍጠር፣ የማሳደግና የማያቋርጥ ስራ መስራትን ያካትታል። ይህ ዓላማ የበለጠ የተሳካ ይሆን ዘንድም የፌዴራል መንግስት በህገ መንግስቱ የሰፈሩትን የዜግነት መብቶች በአገሪቱ በጠቅላላ የሚያስፈጽምበት መዋቅርና ተቋም ያስፈልገዋል። ክልሎችም የዜግነት መብት በሚጥሱበት ጊዜ የማስተካከያ እርምጃ የሚወስድ ተቋም መኖር ይኖርበታል። በዚህ ረገድ ሰፊ ክፍተት እንዳለ ይታወቃል። የሌሎች ሀገሮች ልምድ እንደሚያሳየው ይህን ማድረግ የፌዴራል መንግስት ቁልፍና ቀዳሚ ሚና ነው።

## 4. የክልሎች ራስ ማስተዳደር ስልጣንና የዜግነት መብት፡ክፍተቱና መፍትሄው

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በርካታ የፌዴራል ስርዓትን የሚከተሉ ሀገሮች ልምድ እንደሚያሳየው ራስን በማስተዳደርና በዜግነት መብት መካከል በፌዴራል ሕገ-መንግስቱና በተግባር በግልጽ በተደነገጉ መርሆች የተመሰረተ ነው። አገሮቹ በመጀመርያ በአንድ ገዢ ብሔርና ሊብራል ስርዓት ስር ለረዥም ግዜ የቆዩ በመሆናቸው (ለምሳሌ ስፔይን፣ ቤልጀም፣ ህንድ፣ ካናዳ፣ እንግሊዝ) ከቡድን/ብሔር መብት በፊት የግለሰብ መብት ተረጋግጦ የቆየባቸው ሀገሮች ናቸው። በሂደት ግን በዚያ ገዢ ብሔር ስር የአገር ግንባታው ሲካሄድ ማእከላዊ መንግስት አግላይ ስለነበረ፡ ተገለናል የሚሉ ማህበረሰቦች (ለምሳሌ ካታላን ከስፐይን ፣ ኩቤክ ከካናዳ ፣ ደች ተናጋሪዎቹ በቤልጀም፡ ስኮትሽ በእንግሊዝ) ባካሄዱት ረዥም ትግል፡ የእነዚህ ህዝቦች ራስን የማስተዳደር ስልጣንና በፌዴራል ደረጃም ተመጣጣኝ ውክልና የማረጋገጥ ስርዓት (ከአገር አገር የሚለያይ ቢሆንም) በማበጀት ሁሉንም ለማቀፍ የሚችል ስርዓት ማበጀት ቻሉ። ስለዚህም እነዚህ ማህበረሰቦች ራሳቸውን ማስተዳደር ስልጣን ሲፈቀድላቸው በቅድመ ሁኔታ ታጅቦ እንደነበረ ማየት ይቻላል። ቅድመ ሁኔታውም፡ ክልሎች ራሳቸውን ሲያስተዳድሩ የዜጎች መብት በሚያረጋግጥ መልኩ

መሆኑ ነው፡፡ የብሔር መብት የዜጎችን መብት መሠረት ከተጣለ በኋለ ተከትሎ የመጣና የዜጎችን መብት ብቻውን ግን በቂ ስላልነበረ የጎደለውን ለመሙላት ተጨመረ እንጂ የዜግነት መብትን ለመደፍጠጥ የተተከለ ስርዓት አልነበረም፡፡

ክልሎች ራሳቸውን በማስተዳደር ሽፋን በሌላው ወገናቸው ላይ እያስከተሉት የሚገኙትን የማግለልና የ“ውጡልን” በሽታ በግዜ መታረም ይኖርበታል፡፡ ራስ ማስተዳደር ዴሞክራሲያዊ ጽንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ የህዝብ ራስን የማስተዳደር ስልጣን ሌላውን ባገለለ መንገድ ከሆነ ዴሞክራሲያዊነቱ እዚያ አበቃ ማለት ነው፡፡ አሁን ባለው አካሄድ በየደረጃው የሚገኘው አመራር ይህ ክልል፡ ተቋሞችና መሬቱ የዛው ብሔር ብቻ ነው በሚል በተግባር ተተርጉሞ እየተሰራ ስለሆነ በተግባር ክልሎች አንደኛ ዜጋና ሁለተኛ ዜጋ ፈጥረዋል፡፡ ይህ ደግሞ በየአካባቢው ለበርካታ ህዝብ ለመፈናቀል ምክንያት ሲሆን ያታያል፡፡ በአገራችን በአሁኑ ሰአት 2.5 ሚልዮን የሚሆኑ ዜጎች ተፈናቅለው ይገኛሉ፡፡ ክልሎች በስራቸው የሚገኙትን ወገኖችና ዜጎች ማቀፍ፡ ማሳተፍና ውክልና ማግኘት የሚያስችል ስርዓት ሊገነቡ ይገባቸዋል ፡፡ ራስ መስተዳደር የራስን ማንነት፣ ታሪክ፣ ቋንቋ፣ ወዘተ ማሳደግ የሚያካትት ቢሆንም ከዚያ ባለፈ ትርጉም ያለውና የሌሎችን ማንነት ማወቅና ማክበር፣ ከሌሎች ወገኖች ጋር ጤነኛ ግንኙነትና ትብብር በመመስረት፣ የተሳሰረ፤ የተገመደ አገር መገንባትንም ያካትታል፡፡ የአንዱ ወገን ህመም ለሌላውም ህመም፣ የአንዱ ወገን ደስታም ለሌላው ደስታ መሆን ይኖርበታል፡፡ እንደ አንድ ዜጋ የወንድማማችነት መንፈስም ሊፈጠር የሚችለው በዚሁ መንገድ ሲታሰብ ነው፡፡ በተጨማሪም በፌዴራል ሕገ-መንግስቱ የተካተቱት የዜጎች መብትና ነጻነቶች ፣ ዜጎች ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስና ንብረት የማፍራት እንዲሁም በአገራቸው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ መብት ባለፉት ዓመታት ብዙ ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ ስለሆነ ብዙ ችግር ተፈጥሯል፡፡

በብሔረሰብ በተደራጁበት ክልሎች ውስጥ የሚኖሩ የሌላ ብሔረሰብ አባላት እንደ ሌላ አገር ዜጋ በአገራቸው ጉዳይ እንደ ባይተዋር መታየት ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡ ስለዚህም በመጀመርያ ደረጃ ብሔር ብሔረሰብ ማለት የክልሉን ስራ ቋንቋ ማስቻልን እንጂ የዘር ግንድ እንዳልሆነ ማስተካከልን፣ ክልሎች በውስጣቸው የሚገኙትን ዜጎችና ሌሎች ህዝቦች በተመጣጣኝ ውክልና ስርዓት ውክልና ማረጋገጥ ያለባቸው መሆኑን፣ የዜጎች መብት በአገሪቱ ባጠቃላይ ምንም ሳይሸራረፍ ማረጋጋጥ የፌዴራል መንግስት ስልጣንና ግዴታ መሆኑን፣ ክልሎች በዚህ በኩል ክፍተት ሲያሳዩ ከማስተማርም ባለፈ ራስ ማስተዳደር ስልጣናቸውን የሚነሳ ወይም ሊገደብ የሚችል መሆኑን በግልጽ ማወጅና ማስተካከል ይገባል፡፡

የበርካታ የፌዴራል ስርዓቶች ልምድ እንደሚያሳየው የፌዴራል መንግስት መስራት ካለበት ስራዎች በቅድሚያ ከሚጠቀሱት አንዱ የዜጎች መብትና ነጻነት በአገሪቱ ከጫፍ ጫፍ ያለ ምንም ልዩነት ማክበርና መስፈጸም መቻል ነው። ክልሎች ራሳቸውን በማስተዳደር ሽፋን ይህን መብት መሸራረፍና አደጋ ላይ መጣል አይችሉም። ይህ ክፍተት ግን በርካታ ዜጎችን አደጋ ላይ ጥሏል፡ የአገር ግንባታ ሂደቱንም ችግር ውስጥ ከቶታል። የሚገርመው ይህ ችግር እየተከሰተ ባለበት ሁኔታ አገሪቱ በፌዴራልም ይሁን በክልሎች በርካታ ገንዘብ በማፍሰስ ሰፋፊ መንገዶች፣ የባቡር ሀዲዶች፣ ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች እየተሰሩና ዜጎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ ዕድል እየተመቻቸ ባለበት ሁኔታ ነው። በሌላ አገላለጽ የልማት ስራው በጠንካራ ተቋሞች፡ የፖለቲካና የህግ የበላይነት ስራ ባለመደገፉ ምክንያት እርስ በርሱ የሚጋጭ ፖሊሲ እስኪመስል ድረስ አገሪቱን ችግር ውስጥ ከትቷታል። ይህ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባና አስቸኳይ መፍትሔ የሚሻ ጉዳይ ነው። ክልሎች የዜጎችን መብት ያለምንም መሸራረፍ ማክበር ግዴታቸው መሆኑን ማስተማርና ማስፈጸም፣ በክልሎች የሚገኙትን ዜጎችና ውህዳን/አናሳ ህዝቦች በክልል ተቋሞች ተመጣጣኝ ውክልና እንዲኖራቸው ማረጋገጥ፡ ዜጎች የትም ይኑሩ በአገራቸው ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ጉዳዮች የመሳተፍ መብት በሁሉም ክልሎች ማረጋገጥ፤ ይህን በማያደርጉ ክልሎችም ራስ ማስተዳደር ስልጣን እስከ መገደብና በፌዴራል መንግስት እስከማስተዳደር ሊሄድ የሚችል የእርምት እርምጃ መውሰድ እንደሚያስከትል መግባባትና ወደ እርምጃ መገባት አለበት።[19]

በዚህ ዙርያ መነሳት ያለበት አንዱ አብይ ነጥብ ይህን ጉዳይ ማን ያስፈጽመው የሚል ነው። ለዚህም ሁለት አብረው መሰራት ያለባቸውን ነገሮች መጠቆም ያስፈልጋል። አንደኛው የፖለቲካ ስራ ነው። ይህ ችግር ሀገራዊና ፖለቲካዊ ችግር መሆኑን መግባባት ላይ መድረስና ለመፍትሔ መዘጋጀት ያስፈልጋል። በዚህ ደረጃ በፖለቲካ አመራሩ በችግሩ መግባባት መድረስ የችግሩ ግማሽ መፍትሔ ነው። በፖለቲካ መድረኩ መግባባት ላይ መድረስና ፖለቲካዊ የማስፈጸምና ክትትል ስልት ማስቀመጥ ብዙ ነገሮችን ያስተካክላል። ይህን ብቻውን ግን በቂ አይደለም ምክንያቱ ተቋማዊ መፍትሔም ስለሚፈልግ።

በማንኛውም ጤነኛ የፌዴራል ስርዓት የፌዴራል መንግስቱ ቁልፍ ተብለው ከሚታወቁት ስልጣኖች አንዱና ወሳኙ ሁሉም ዜጋ በአገሪቱ ያለምንም ችግር በአገሩ ጉዳይ መሳተፍና የዜግነት መብቱ መከበሩን ማረጋገጥ ነው። አንድ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ማህበረብ ማለት ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች ቢኖሩትም በዋናነት ግን በሁሉም

[19] ለዝርዝሩ Assefa Fiseha Intra unit Minorities in a context of Ethno National Federation in Ethiopia *Utrecht Law Review* v. 13 No 1 (2017) DOI: 10.18352/ulr.402

ክልል የዜግነት መብት በእኩል ደረጃ ማስከበር መቻል የጽንሰ-ሀሳቡ ዋና ምሰሶ ነው። ለዚህ ደግሞ ተቋሞች ያስፈልጋሉ። በዚህ ረገድ በብዛት ትኩረት ያላገኘና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 13 (1) የተካተተ ወሳኝ መርህ፡ ካስፈለገም የማስፈጸሚያ ተጨማሪ አዋጅ በማውጣት ራስ ማስተዳደር ምን ማለት እንደሆና እንዳልሆነ፡ በዝርዝር በማብራራት የማስፈጸምያ ስልት ማበጀት ነው። በሕገ-መንግስቱ እንደተካተተው የዜጎች መብት ከፍተኛ ስፍራ ያለቸው መሆኑን መደንገግ/መግለጽ አንድ ነገር ሆኖ፡ በአገር አቀፍ ደረጃና በተመሳሳይ መልኩ ማን ያስፈጽም ለሚለው ጥያቄ በመደበኛው ፍርድ ቤትና በፌዴሬሽን ምክር ቤት መካከል መሳሳብና 'የኔ አይደለም፣ የኔ አይደለም' የሚል ክፍተት በመኖሩ ምክንያት በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች በዜጎች ላይ ችግር ሲያደርሱ የተበደለው ዜጋ አቤት የሚልበትና መፍትሔ ማግኘት የሚችልበት መድረክ አላገኘም። አንዳንድ ታዛቢዎች የዜጎች መብት ያካተተው የሕገ-መንግስት ክፍል ይህ ክፍተት ያለበት በመሆኑ 'ባለቤት አልባ' ምዕራፍ ሲሉ ይሰማሉ። ስለዚህም ቢያንስ በየደረጃው የሚገኙ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች (አሁን ያለውን የውክልና ስርዓት በማቆም፡ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች በአገር ደረጃ በሁሉም ክልሎች በማቋቋም) እነዚህን የዜጎች መብት የሚዘረዝሩ በምእራፍ ሶስት የተካተቱት አንቀጾች ወጥ በሆነ መልኩ በአገሪቱ ባጠቃላይ ማስፈጸም እንዲችሉ ግልጽ ስልጣን በአዋጅ መስጠት ያስፈልጋል። በዚህ መልኩ የህገ መንግስት የበላይነትና የዜጎች መብት ትርጉምና ህይወት እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል። ይህን ማድረግ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ መፍጠር የሚለውም እውን እንዲሆን መሠረት መጣልም ማለትም ነው። አለበለዚያ አሁን ባለው ሁኔታ ክልሎች የተለያየ ደረጃ ያለው ዜጋ ፈጥረው፡ ዜጎችም በክልላቸው ብቻ ታጥረው፣ የሰውና የሀብት እንቅስቃሴ ተገድቦ፡ መንገዶች ተዘግተው ወዘተ ከቀጠለ የግዜ ጉዳይ ካልሆነ በቀር እንደ አገር ያበቃለት መሆኑን ማሳያ ነው።[20]

በፌዴራልም ይሁን በክልል የሚገኙ የመንግስት ተቋማት ሁሉንም ዜጋ ያለምንም አድልዎ በእኩል ማገልገል ይኖርባቸዋል ። በዚሁ ረገድ የሚታዩ ችግሮችም መታረም አለባቸው። በየአካባቢው የነበሩ ግጭቶች እንደሚያሳዩት የመንግስት ተቋሞች ራሳቸው ጎራ ለይተው የችግሩ አካል ሲሆኑ ታይተዋል። ፖሊስ የፌዴራልም ይሁን የክልል የተለየ ቋንቋ ሊናገር ይችላል ። ነገር ግን ግን የፖሊስ ስራ ዜጋውን ከአደጋ መጠበቅ፣ ወንጀልን መከላከል እና የህዝቡን ሰላም መጠበቅ ነው ከዚህ አልፎ ጎራ ለይቶ የችግሩ አካል ሲሆን እያደረ ሌላ ችግር መፍጠሩ ስለማይቀር በጊዜ መታረም ይኖርበታል።

[20] **ከዚህ ጋር በተያያዘ ለተጨማሪ ማብራርያ** Assefa Fiseha 'Federalism, development and the changing political dynamics in Ethiopia' *International Journal of Constitutional Law* v.17 No 1 (2019) **ይመልከቱ**

## 5. ማጠቃለያና ምክረ-ሀሳብ

ለማጠቃለል ያህል የአገራችን የፌዴራል ስርዓት ባለፉት ሁለት አስርተ አመታት በርካታ የመሠረተ ልማትና የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት ማረጋገጥ ችሏል። ከዚያም ባለፈ ባለፉት ሶስት አመታት ባጋጠሙን ችግሮች በተፈጠረው የአመራር ችግር ዘግይቶም ቢሆን በሰከነና ሰላማዊ በሆነ መንገድ አዲስ መሪ መተካት መቻሉ በፖለቲካ ስልጣን ሽግግርም አንድ ትልቅ እርምጃ መሄድ መቻልን አይተናል። ከላይ የተገለጹት ስኬቶች እንዳሉ ሆነው ግን አሁንም መመለስ ያለብን በርካታ ጥያቄዎች መኖራቸው ግን አልቀረም። እዚህ መጠቀስ ያለበት አንዱ ነጥብ በየደረጃው የሚገኙ ተቋሞች በየግዜው ለሚነሱት ጥያቄዎች የሚመጥን መልስ በግዜ መስጠት አለመቻል በቀላሉ ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮች ጊዜ በወሰዱ ቁጥር እንዲወሳሰቡና ህብረተሰቡም ወደ ግጭት እንዲገባ ምክንያት እየሆኑ ስለሆነ በየጊዜው ሪፎርም ማካሄድ ግድ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። መሻሻል የሚገባቸውን ህጎች፣ ፖሊሲዎችና አሰራሮችም እንዲሁ መፈተሽና ማሻሻል ያስፈልጋል። ተቋሞችም ከድርጅት ተጽዕኖ ነጻ ሆነው ለሚያጋጥሙ ችግሮች ፖለቲካዊ መፍትሔ መስጠት መቻል ይኖርባቸዋል። በዚህ ረገድ ሊነሱ የሚችሉ ሁለት ነጥቦች አሉ። አንደኛው የፖለቲካ ሹመትንና በባለሞያ መሰራት ያለበትን ነገር መለየት ያስፈልጋል። አንድ አገር ብቃት ባለው ባለሙያ ስራውን ማሰራትና አገልግሎት መስጠት ካልቻለ ችግር ማጋጠሙ አይቀርም። አሁን በተግባር ሲታይና በርካታ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ፖለቲካ ታማኝነትና በብቃት መካከል በመንግስት ተቋሞች ላይ ከፍተኛ ሽምያና ውድድር መኖሩና ፖለቲካ ታማኝነትና የድርጅት አባልነት ብቃትን እየገፈተረ እንደሆነ ይታያል። ይህ የመንግስትን የማስፈጸም አቅም ከማዳከምም ባለፈ የልማት ስራዎች በማጓተት፡ አገልግሎት አሰጣጥን በማዘግየት በህዝብ ዘንድ ቅሬታ እንዲፈጠር እየሆነ ነው። የአመጹ አንዱ ምክንያትም ጥራት ያለው አገልግሎት ማግኘት አለመቻል መሆኑ ይታወቃል። ሌላው ጠንካራ መሪና ድርጅት ሁሌም የሚፈለግ ቢሆንም መቋጫው መሆን ያለበት ጠንካራ መሪና ፓርቲ በሌለ ጊዜ ሊሰሩ የሚችሉ ብቃት ያላቸው ተቋሞች የፈጠረ ሲሆን የበለጠ ታላቅ ይሆናል ማለት ነው።

በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚደረጉ የልማት ስራዎች ክልሎችንና የሚመለከተው ማህበረሰብ ማወያየት፣ ማሳተፍና ባለቤት ማድረግ የልማት ስራው የበለጠ ዘለቄታዊ ስለሚያደርገው በዚህ በኩል ያሉትን ክፍተቶች ማስተካከል ያስፈልጋል። የፌዴራል ስርዓቱ እስካሁን ድረስ ከሞላ ጎደል በአውራ ፓርቲ ስር እየተፈጸመ የቆየ በመሆኑ የተለየ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸው ወገኖች የማሳተፉ ዕድል በመወሰኑ ምክንያት ድምጻችን ሰሚ አላገኘም የሚለው የህብረተሰብ ክፍል ሊሳተፍ የሚችልበት አሰራርና የምርጫ ህጉን የመከለስ ነገር ግዜ የሚሰጠው መሆን የለበትም። ለአገራችን

ችግሮችም በመንግስታዊ ተቋሞች በኩል ፖለቲካዊ መፍትሔ መስጠት መቻል ገና ያልዳበረና በፓርቲ/ድርጅት ላይ ያተኮረ በመሆኑ ተቋሞች ከፓርቲ ተጽዕኖ ነጻ መውጣት ይኖርባቸዋል። በየደረጃው የሚገኙ ተቋሞች ለሚነሱት ችግሮች ፖለቲካዊ መፍትሔ መስጠት ባለመቻላቸውና ዜጎችም ከጊዜ ወደ ጊዜ በተቋሞቹ ላይ ያላቸው አመኔታ እየቀነሰ በመሄድ ብሶታቸውን ወደ መንገድ ሲወስዱ ያታያል። ስለዚህም ተቋሞች ፖለቲካዊ መፍተሔ መስጠት ይኖርባቸዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የፌዴራል ስርዓቱ ከዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት፡ በአውራ ፓርቲና ልማታዊ መንግስት ጋር ተጣምሮ ይካሄድ ስለ ነበረና ትላልቅ የልማት ስራዎች ከማዕከል ይመነጩ ስለነበር መሬትና መሬት ነክ ጉዳዮች የክልሎችን የመወሰን ስልጣን በተወሰነ መልኩ የገደበ ስለነበር ክልሎች ራሳችንን የማስተዳደር ስልጣናችን ተገፍቷል ማለታቸው አልቀረም። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው በበርካታ አካባቢዎች ከተነሱት አመጾችና መፈክሮች አንዱ የክልሎች ራስን የማስተዳደር ስልጣን ይከበር የሚል እንደ ነበረ ይታወቃል። ስለዚህም ልማትና የፌዴራል ስርዓት ሁለት ትልልቅና ወሳኝ ምሰሶዎች ስለሆኑ ሳይጋጩና የክልሎች የመወሰን ስልጣን ሳይጋፋና ህብረተሰቡን በማሳመን ቢካሄድ የተሻለ ውጤት ማምጣት እንደሚቻል እንዲሁም ልማቱን ዘለቄታዊ ማድረግ እንደሚቻል መገንዘብ ያስፈልጋል። ክልሎች በሕገ-መንግስቱ የተሰጣቸው ስልጣን ሳይጥሱና በፌዴራል መንግስት በኩል የሚወጡትን አገር አቀፍ ስታንዳርድ መሠረት በማድረግ በክልሎች በኩልም ሊመጣ የሚችል ልማት መኖሩን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በሀገራዊ ማንነትና በብሔር ማንነት መካከል ባለፉት ሁለት አስርተ-ዓመታት ያየናቸውን ልምዶች በማጤንና በመከለስ ብዝሀነትን በሚያስተናግድ መልኩ ሀገራዊ/ኢትዮጵያዊ/ዜግነት ከሁሉም ሌሎች ማንነቶች ከፍ ባለ መልኩና የሁሉም ጥላ ሆኖ ፤ ግን ደግሞ ሌሎች ማንነቶች፤ በማይደፈጥጥና በሚዛኑ በሚያቅፍ መልኩ በመንግስት ፖሊሲዎች ተቀርጾ የሚፈጸምበትና ክትትል ሊደረግበት የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋለት ይገባል። ይህ አንዱ እስካሁን ድርስ በፌዴራል መንግስት በኩል ያልተፈጸመና የተዘነጋ ቁልፍ ስልጣን ነው።

ከማንነት ጋር በተያያዘ በቋንቋ፤ በባህል፤ ክፍለ ሀገር፤ ትውልድ ቦታ እምነት በመሳሰሉት መለያየት ግጭት ለማስነሳት በራሳቸው ምክንያት አይደሉም፡ የአገራችን የኋላ ታሪክም ሆነ ከሌሎች ሀገሮች (ህንድ፣ስዊዝ፣ ከናዳ ወዘተ) ማየት እንደሚቻለው ህብረ-ብሔራዊነት/ህብረ ባህልና እምነት ውበት ሆኖ የመተባበር፣ የሰላምና ልማት መሠረት ሆኖ ሲገኝ ፤ በሌሎች ሀገሮች ደግሞ ማንነትን መሠረት ያደረገ ልዩነት አንዱን ወገን የፖለቲካ/ሀብት ተጠቃሚ እንዲሁም ቋንቋውንና ባህሉን ሀገራዊ /ብሔራዊ በማድረግ የመጀመሪያ ዜጋ ሲያደርግ ሌላውን ደግሞ ከፖለቲካና

ኢኮኖሚ ጥቅም ከማግለል በተጨማሪ ቋንቋንና ባህሉን (ማንነቱን) ወደ ሁለተኛ ዜጋ በማውረዱ ምክንያት ለእርስ በርስ ግጭት ምክንያት ሲሆን ይታያል። በዚህም ምክንያት ሰላም፣ ልማትና ትብብር ይጠፋል ማለት ነው። ይህ እንዳይሆን በየደረጃው የሚገኙ ተቋማትና ኃላፊዎች ማንነት እንደ ጉዳዩ ክብደትና የህዝቡን አሰፋፈር፤ ተቋማዊና ፖሊሲን መሠረት ባደረገ መልኩ መፍትሔ ሊሠጡት ያስፈልጋል። በተለያዩ ህዝቦች መካከል ግንኙነትን የሚያጠናክሩ ገመዶችም (social capital) ከፖለቲካውና የኢኮኖሚው መፍትሔ ጎን ለጎን ትኩረት በመስጠት ማጠናከር ያስፈልጋል ። ይህ ከሆነ ማንነት የውበት፣ የልማት፣ የሰላምና የትብብር መሠረት ይሆናል ማለት ነው።

ሌላው ክልሎች ራሳቸውን በማስተዳደር ሽፋን በሌላው ወገናቸው ላይ እያስከተሉት የሚገኙትን የማግለልና የ"ውጡልን" በሽታ በጊዜ መታረም ይኖርበታል። ራስን ማስተዳደር ዴሞክራሲያዊ ጽንሰ- ሀሳብ ነው። የህዝብ ራስ ማስተዳደር ስልጣን ሌላውን ባገለለ መንገድ ከሆነ ዴሞክራሲያዊነቱ እዚያ አበቃ ማለት ነው። አሁን ባለው አካሄድ በየደረጃው የሚገኘው አመራር ይህ ክልል፣ ተቋሞችና መሬቱ የዚያ ብሔር ብቻ ነው በሚል ተተርጉሞ እየተሰራ ስለሆነ በተግባር ክልሎች አንደኛ ዜጋና ሁለተኛ ዜጋ ፈጥረዋል። ይህ ደግሞ በየአካባቢው በርካታ ህዝብ ለመፈናቀል ምክንያት ሲሆን ያታያል። አገራችን በአሁኑ ሰአት 2.5 ሚልዮን የሚሆኑ ዜጎች ተፈናቅለው ይገኛሉ። ክልሎች ከስራቸው የሚገኙትን ወገኖችና ዜጎች ማቀፍና ማሳተፍ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት ይኖርባቸል። ራስ መስተዳደር የራስን ማንነት፣ ታሪክ፣ ቋንቋ ወዘተ ማሳደግ የሚያካትት ቢሆንም ከዚያ ባለፈ ትርጉም ያለውና የሌሎችን ማንነት ማወቅና ማክበር፡ ከሌሎች ወገኖች ጋር ጤነኛ ግንኙነትና ትብብር በመመስረት፣ የተሳሰረ፣ የተገመደ አገር መገንባት ያካትታል። የአንዱ ወገን ህመም ለሌላውም ህመም፡ የአንዱ ወገን ደስታም ለሌላው ደስታ መሆን ይኖርበታል። እንደ አንድ ዜጋ ወንድማማችነት መንፈስም ሊፈጠር የሚችለው በዚሁ መንገድ ሲታሰብ ነው። በተጨማሪም በፌዴራል ሕገ-መንግስቱ የተካተቱት የዜጎች መብቶችና ነጻነቶች ዜጎች ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስና ንብረት የማፍራት እንዲሁም በአገራቸው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ የመሳተፍ መብት ባለፉት አማታት ብዙ ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ ስለሆነ ብዙ ችግሮች ተፈጥረዋል። የበርካታ የፌዴራል ስርአቶች ልምድ እንደሚያሳየው የፌዴራል መንግስት ማድረግ ካለባቸው ስራዎች በቅድምያ ከሚጠቀሱት አንዱ የዜጎች መብትና ነጻነት በአገሪቱ ከጫፍ ጫፍ ያለ ምንም ልዩነት ማክበርና መስፈጸም መቻል ነው። ክልሎች ራሳቸውን በማስተዳደር ሽፋን ይህን መብት መሸራረፍና አደጋ ላይ መጣል አይችሉም። ይህ ክፍተት ግን በርካታ ዜጎችን አደጋ ላይ ጥለዋል፡ የአገር ግንባታ ሂደቱም እንዲሁ ችግር ውስጥ

ከቶታል። የሚገርመው ይህ ችግር እየተከሰተ ባለበት ሁኔታ አገሪቱ በፌዴራልም ይሁን በክልሎች በርካታ ገንዘብ በማፍሰስ ሰፋፊ መንገዶች፣ ባቡር ሀዲዶች፣ ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች ወዘተ እየተሰሩና ዜጎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ ዕድል እየተመቻቸ ባለበት ሁኔታ ነው። በሌላ አገላለጽ የልማት ስራው በጠንካራ የፖሊተካና የህግ የበላይነት ስራ ባለመደገፉ ምክንያት እርስ በርሱ የሚጋጭ ፖሊሲ እስኪመስል ድረስ አገሪቱን ችግር ውስጥ ከቷታል። ይህ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባና አስቸኳይ መፍትሔ የሚሻ ጉዳይ ነው። ክልሎች የዜጎችን መብት ያለምንም መሸራረፍ ማክበር ግድታቸው መሆኑን ማስተማርና ማስፈጸም፣ በክልሎች የሚገኙትን አናሳ ህዝቦች በክልል ተቋሞች ተመጣጣኝ ውክልና እንዲኖራቸው ማረጋገጥ፡ ዜጎች የትም ይኑሩ በአገራቸው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ጉዳዮች የመሳተፍ መብት ሁሉም ክልሎች ማረጋገጥ፣ ይህነ በማያደርጉ ክልሎችም ራስ ማስተዳደር ስልጣን እስከ መገደብና በፌዴራል መንግስት እስከማስተዳደር ሊሄድ የሚችል እርምት እርምጃ መውሰድ እንደሚያስከትል መግባባትና ወደ እርምጃ መገባት አለበት።

የበርካታ ፌዴራል ስርአዓቶች ልምድ ማየት እንደሚቻለው፡ በፌዴራል ሕገ-መንግስቱ የተካተቱት መብቶች በአገሪቱ ባአጠቃላይ እንደ አነስተኛ መመዘኛ (minimum standard) ተወስዶ ክልሎች ከዚያ የተሻለ እንጂ ያነሰ መብት መፈጸም አይችሉም። ስለዚህም አሁን በተግባር የሚታየውንና በአንዳንድ ክልሎች በህገ-መንግስት ደረጃም ጭምር ተካቶ የሚገኘው የዜጎችን መብት የሚሸራርፉ አንቀጾችና ተግባራት የፌዴራል መንግስት የክልሎች ራስ ማስተዳደር ስልጣን ምን እንደሚያካትትና እንደማያካትት፣ ክልሎች በውስጣቸው የሚገኙትን ዜጎችና ውህዳን ህዝቦች በአገራቸውና በክልሉ ጉዳይ የመሳተፍና ውክልና የማግኘት መብት እንዳላቸው የሚደነግግ ህግ እንዲሁም በዚሁ ሂደት በደል የደረሰበት ዜጋ መፍትሔ ማግኘት የሚችልበት ተቋም (የፌዴራል ፍርድ ቤቶች) በአገሪቱ በሙሉ በማቋቋምና የዜጎችን መብት በማስከበር ደረጃ ግልጽ ስልጣን በመስጠት መፍጠር ያስፈልጋል።

በፌዴራልም ይሁን በክልል የሚገኙ የመንግስት ተቋሞች ሁሉንም ዜጋ ያለምንም አድልዎ በእኩል ማገልገል እንዳለባቸውና በዚሁ ረገድ የሚታዩ ችግሮችም መታረም ይኖርባቸዋል። በየአካባቢው የነበሩ ግጭቶች እንደሚያሳዩት የመንግስት ተቋሞች ራሳቸው ጎራ ለይተው የችግሩ አካል ሲሆኑ ታይተዋል። ፖሊስ የፌዴራልም ይሁን ክልል የተለየ ቋንቋ ሊናገር ይችላል ግን የፖሊስ ስራ ዜጋውን ከአደጋ መጠበቅ፡ ወንጀልን መከላከል የህዝቡን ሰላም መጠበቅ ነው ። ከዚህ አልፎ ጎራ ለይቶ የችግሩ አካል ሲሆኑ እያደረ ሌላ ችግር መፍጠሩ ስለማይቀር በጊዜ መታረም ይኖርበታል።

ሌላው ወሳኝ ነጥብ የፌዴራል ስረዓቱም ይሁን የአገራችን ፖለቲካ በአጠቃላይ በሕገ-መንግስትታዊነትና በህግ የበላይነት ያልታገዘ መሆኑ ነው:: በርካታ ጸሀፊዎች እንደሚሉት የፌዴራል ስርዓት ህዝቦች በበርካታ የመንግስት እርከኖች (ፌዴራል፡ ክልል፡ ወረዳ ወዘተ) መሳተፍንና ተጽእኖ የማሳደር ዕድል ይሰጣል:: ይህ ማለት በየደረጃው የሚገኙት መሪዎች በተለያያ እርከን ተጠያቂነት ስርዓትም አብሮ ይፈጥራል ማለት ነው:: ተደጋግሞ እንደሚባለው ህዝብ ለማገልገልና ከድህነት መዋል የነበረበት ሀላፊነት ያለ ህግ የበላይነትና ተጠያቂነት ሲፈጸም ፍፁም ስልጣን ወደ ፍፁም የስልጣን ሙስና ('power corrupts and absolute power corrupts absolutely' የሚባለውን አደጋ ይፈጥራል:: በፌዴራል ስርኣት ውስጥ ሙስናውም ፌዴራል መልክ ይኖረውና - በርካታ የሙስና እርከኖች multiple centers of corruption ይፈጥራል:: በዚህ በሽታ የተለከፈ ስርዓት የህዝብና የሀገር አንድነት ሊያመጣ ይቅርና ሰላምና መረጋጋትም ሊያመጣ አይችልም:: ለዚህ ፍቱን መድሀኒት በህገ መንግስቱ የተካተቱትን የተጠያቂነትና የህግ የበላይነት ስረዓቶች ያለምንም ማመንታት መፈጸም ነው::

ለማጠቃለል ያህል የሀገር ግንባታ ስራ አንድ ሀገር፣ ህዝብና ስርዓት እስካለ ድረስ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅብብሎሽ የሚሰራ፣ የማያቋርጥና የብዙ ነገር ድምር ውጤት ነው:: በአጠቃላይ ግን ሁሉንም የህብረሰተሰብ ክፍል ያቀፈ የፖለቲካ ስርዓት፣ ፖሊሲዎች፣ ወዘተ በመጠቀም፣ በርካታ ማንነቶች ያቀፈ፤ ግን ደግሞ በአንድ ሀገራዊና ኢትዮጵያዊ ዜግነት የተገመደ፣ የተሳሰረ ህዝብ የመፍጠር ስረዓት ነው:: ፌደራሊዝም በትክክል ከተተገበረና በዚህ ጽሁፍ የተነሱትን ችግሮች ማረም ከተቻለ ለዚህ ፍቱን መሳርያ ነው::

እንደሚታወቀው አዲሱ የገዢው ፓርቲ አመራር ወደ ስልጣን ከመጣ ጀምሮ በድርጅቱ በኩል ለረዥም ዘመን አብሮት የቆየውን የፖለቲካ መስመር መቀጠል አለመቀጠል ጉዳይ በግልጽ የታወቀ ነገር የለም:: አንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች እንደሚሉት በሽግግር ላይ ያለ ይመስላል:: ይህ የፖለቲካ መስመር ክፍተት ግን የራሱ ጦስ መፍጠሩ አልቀረም:: የቆየው የፖለቲካ መስመር የተለያዩ ብሔር መሠረት አድርገው የተደራጁ ሀይሎችን በአብዮታዊ ዲሞክራሲና ልማታዊ መንግስት ስር ጠርንፎ ይንቀሳቀስ ስለነበር ምንም እንኳ በክልሎች ራስ ማስተዳደር ስልጣን ላይ የተወሰነ ችግር ፈጥሮ የነበረ ቢሆንም የብሔር ስሜቱ እንዳይገነፍል አስሮት ቆይቷል:: ካለፉት አራት አመታት ወዲህ ግን ይህ የፖሊተካ መስመር እየተዳከመ በመሄዱ፡ እንዲሁም በየክልሉ የነበረው አመጽ እየተጠናከረ በመምጣቱ ይዞት የነበረው ገመድ ሲበጣጠስና የፖለቲካ መስመሩ የተፈጠረው ክፍተት በብሔር ናሽናሊዝም ሲተካ ይታያል:: ይህ ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ ጫፍ የሄደ ብሔርተኝነትና

ወደ እርስ በርስ ግጭትና መፈናቀል እንዲያመራ አድርጎታል፡፡ ያልተገራ ቤሔርተኝነት ግጭት፣ ስርዓት አልበኝነት፣ ፋሺዝም ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለዚህም የሚቀጥለው ምርጫ በአዲስ መንግስት እስኪተካ ድረስ የፌዴራል መንግስት የሚከተለው የፖሊተካ መስመር ግልጽ አድረጎ የተፈጠረው ክፍተት ማስተካከልና ብሔርተኝነትን መግራት፡ በየቦታው እየታየ ያለውን ስርዓት አልበኝነትና የመንገድ መዘጋት፣ እንዲሁም የዜጎች መፈናቀል አስቸኳይ መፍትሔ ማበጀት ይኖርበታል፡፡ ፖለቲካዊ መፍትሄ ባልተወሰደ ቁጥር ዜጎች በመንግስት ላይ ያላቸው አመኔታ እየተመናመነ ሄዶ 'መንግስት የለም' ወደሚል ስሜት እንዲሄድና አላስፈላጊ የሆነ ህገወጥ የመሳርያ ትጥቅና ወደማንወጣው የርስ በርስ እልቂት ሊከተን ይችላል፡፡

ከዚህ በተረፈ ባለፉት አራት አመታት በአገሪቱ ያጋጠሙ ችግሮች በሙሉ ከፌዴራል ስርዓቱ ጋራ የማያያዝ ችግር በስፋት ይታያል፡፡ ለምሳሌ አዲስ አበባ አካባቢ የሚተላለፉ የኤፍ ኤም ራድዮ ስርጭቶች እንዲሁም በርካታ የግሉ ሚድያና የተወሰኑ የመንግስት ሚድያዎች ይህን መልእክት በተደጋጋሚ ሲያስተላልፉ ይታያል፡፡ አገሪቱ ባለፉት አራት አመታት ያጋጠማት ችግር እጅግ ከፍተኛ የሆነ የፖሊተካ ቀውስ፡ የፓርቲና የአመራር ችግር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡[21] ይህ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካና የፓርቲ ቀውስ መልስ ሳያገኝ የፌዴራል ስርዓቱም ሆነ ሌሎች ችግሮች በቀላሉ መፍትሔ ማግኘቱ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህም ከፌዴራል ስርዓቱ ጋር የተያያዙ ችግሮችና ከዛ ውጭ ያሉትን ፖለቲካዊና የፓርቲ የውስጥ ቀውስ መለየት ያስፈልጋል፡፡

[21] Power struggle and rivalery within the ruling party, ideological bankruptcy, mistrust within the political elite, anarchy and lawless ness, militant ethno nationalism, youth un employment and demand for political empowerment, slowing down economy, corruption and lack of accountability, international and regional actors etc are some of the examples.

# የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም እንዲሰራ ስለማድረግ

## ዘመላክ አይተነው

### 1. መግቢያ

ባለፉት ሀያ ሰባት አመታት እንደ ፌዴራል ስርዓታችን ብዙ ያከራከረ ሀገራዊ፤ህገመንግስታዊና ፖለቲካዊ ጉዳይ ያለ አይመስለኝም፡፡ ከተማሪ እስከ ፕሮፌሰር፤ ከሊስትሮ እስከ ኢንቨስተር፤ ከከተሜ እስከ ገጠሬ፤ እንዲሁም ከነጋዴ እስከ ገበሬ ሁሉም የህበረተሰባችን ክፍል በዚህ ጉዳይ ላይ ይከራከራል ሀሳብ ይቀያየራል እናም የራሱን አመለካከት ይይዛል፡፡ ነገር ግን ክርክሮቹ እና ንግግሮቹ በህብረተሰባችን መካከል መግባባት (concensus) ከመፍጠር አንጻር የረባ ፍሬ አላፈሩም፡፡ በፌዴራል ስርዓቱ ዙሪያ የሚደረጉ ክርክሮችን ፍሬ ቢስ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል አንዱ እና ምናልባትም ዋነኛው ክርክሮቹ እና ውይይቶቹ በእውቀት ላይ የተመሰረቱ አለመሆናቸው ነው፡፡ የፌዴራል ስርዓት ምን እንደሆነ፣ምን ጥቅምና ጉዳት እንዳለው በደንብ ያልተረዱ ነገር ግን ስርዓቱን በጭፍን የሚደግፉት ወይንም የሚነቅፉት ብዙዎች አሉ፡፡

ሁለተኛው ምክንያት በፌዴራል ስርዓቱ ላይ አንድ ዓይነት አመለካከት ያለው ሰው ሌላ ከእርሱ የተለየና ሊከበር እንዲሁም ሊታሰብበት (consider) የሚገባ ሀሳብ ያለ መሆኑን እውቅና የማይሰጥ መሆኑ ነው፡፡ ሶስተኛው ስለ ፌዴራል ስርዓቱ የሆነ አይነት አመለካከት ያለው ሰው ተቃራኒ አስተሳሰብ ስለያዘው ወገን ያለው ዕሳቤ (assumption) አሉታዊ መሆኑ ነው፡፡ የፌዴራል ስርዓቱን የሚቃወመው ስርዓቱን የሚደግፈውን ወገን ኢትዮጵያን የማይወድ እንዲያውም ሀገሪቱን ለመበታተን የሚታትር ከራሱ ብሔር ውጭ ያሉ ወገኖችን የሚጠላ እንዲያም ሲል ዘረኛ አድርጎ በመውሰድ ክርክሩን ይጀምራል፡፡ የፌዴራል ስርዓቱ ደጋፊ እንደማንኛውም ዜጋ የሀገሪቱ መፃኢ ዕጣ የሚያስጨንቀው እና ሀገሩን የሚወድ ነገር ግን የመጣበት ብሔር ወይንም ሌላ ቡድን የፖለቲካዊ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መገልል በአንድ ወይንም በሌላ ተቋማዊ መንገድ (institutional mechanism) መፍትሔ ማግኘት አለበት ብሎ የሚያስብ መሆኑን የስርዓቱ ተቃዋሚ ግምት ውስጥ አይወስድም፡፡ የፌዴራል ስርዓቱን የሚደግፈው ደግሞ በተቃራኒው የፌዴራል ስርዓቱ የሚቃወመውን አግላይ የሆነውን አሀዳዊ ስርዓት መልሶ ለማምጣት የሚመኝ እና የሚሰራ፣በሀገር አንድነት ስም የራሱን ወይም የሚደግፈውን የራሱን ቡድን ፍላጎት ለማስጠበቅ እንደሚጥር

እንጂ በፌዴራል ስርዓቱ ላይ ያለው አቋም እውነተኛ ከሆነ ከሀገር ፍቅር የመነጨ መሆኑን ወይንም ሊሆን እንደሚችል በአብዛኛው ታሳቢ አያደርግም።

ባስ ሲልም አንዱ ወገን ሌላኛው ጭራሹኑ እንደሌለ (non-existent) በመቁጠር ነው ክርክሮቹ የሚካሄዱት። ይህ ሁኔታ ይመስለኛል ፍሬያማ ክርክሮችና ውይይቶች እንዳይደረጉ እንቅፋት የሆኑት። በዚህ ጉዳይ ላይ ካለንበት ትንሽ ፈቀቅ እንድንል ከተፈለገ አንዳችን የሌላውን መኖር (existence) ማወቅ ፤በተቃራኒ የቆመው ሰው እንደኛው ስለአገሩ መልካም የሚያስብ ነገር ግን ሀገሪቷ ያለባትን ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች እንዴት ሊፈቱ ይችላሉ የሚለው ጥያቄ ላይ ተለየ አመለካከት ያለው መሆኑን በመቀበል መሆን አለበት። ይህ ካልሆነ ክርክሮቻችን እና ውይይቶቻችን ሁሉ ወሀ መውቀጥ አይነት እንደሚሆኑ ይሰማኛል። ይህ የዛሬውም ውይይት እና ክርክር በመልካም መንፈስ የተቃኘ እንደሚሆን፣ በሀሳቤ ባትስማሙ እንኳን የምለውን ነገር በክፋት እንደማትተረጉሙብኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

ይህ የማቀርበው ወረቀትም በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው። በመጀመርያው ክፍል የፌዴራል ስርዓት በኢትዮጵያ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን አይቀሬ (unavoidable) ጉዳይ መሆኑን ለማሳየት እሞክራለሁ። ቀጥሎ የፌዴራል ስርዓቱ ያሉበት መሠረታዊ የቅርፅ (design) ችግሮች ምንድን ናቸው የትኞቹስ እንከኖች መሻሻል ይችላሉ? የሚለውን በወፍ በረር እመለከታለሁ። በመጨረሻም አሁን የተገኘውን ዕድል በመጠቀም ምን አይነት ተቋማዊ ማሻሻያዎች ማድረግ ይቻላል ወይም ይገባል በሚለው ላይ ጥቂት ነጥቦችን አነሳለሁ።

## 2. የፌዴራል ስርዓት አስፈላጊነት/አይቀሬነት

በአሁኑ ሰዓት ለኢትዮጵያ የፌዴራል፤ ፌዴራል መሰል (quasi-federal) ወይንም ሌላ አይነት ባለብዙ እርከን መንግስታዊ ስርዓት (multi-level goverance system) ይረባታል ወይንስ አይረባትም የሚለው ጉዳይ ሙት (non-issue) እየሆነ መጥቷል። የተለያየ የፖለቲካ አቋም የሚያራምዱ ግለሰቦች እና ቡድኖች አንድ አይነት ባለብዙ እርከን የመንግስት ስርዓት (MLG) በኢትዮጵያ እንድሚያስፈልግ ጠቅላላ መግባባት ላይ እየደረሱ ያለ ይመስላል። የለም የፌዴራል ስርዓት አስፈላጊነት አሁንም ቢሆን መሠረታዊ ጥያቄ ነው ብሎ የሚያምን ካለ መልሱ 'የፌዴራል - ፌዴራል መሰል - ወይም አንድ አይነት ያልተማከለ አስተዳደር ማቋቋም በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአለም አቀፍ ደረጃ እየሆነ ያለ እና ሊያስቀሩት የማይቻል ፖለቲካዊ ሂደት ነው' የሚል ነው ። በተለይም ስለብዝሀነት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረሰበት የአስተሳሰብ ደረጃ፤ ለሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ የሚሰጠው ግምት መጨመር፤ የቴክኖሎጂ መስፋፋት እና እሱንም ተከትሎ የመጣው የክልልና የአካባቢ መንግሥታት ፖለቲካ

ዊ ድርሻ መጨመር፤ እንዲሁም በብዙ መንግስታዊ ጉዳዮች የማዕከላዊ መንግስት አስፈላጊነት መቀነስ ሀገሮችን የመንግስት ስልጣናትን ወደታችኞቹ የመንግስት እርከኖች እንዲያስተላልፉ አስገድዷቸዋል። ይህንንም ለማድረግ ሀገሮች የፌዴራል ወይንም ሌላ ተመሳሳይ ስርዓትን እንዲዘረጉ ተገደዋል። የአለም ባንክ ሪፖርት እንደሚያሳየው ባሁኑ ጊዜ ከ95% በላይ የሆኑ ሀገሮች - ብዝሀነት የሌላቸውም ጭምር ፌዴራል ወይንም ሌላ አይነት ያልተማከለ (develoved or non-centralised) ስርዓት ዘርግተዋል ፤ በመዘርጋትም ላይ ናቸው። ስለዚህ ሀገራችን ይህን ሉላዊ (global) ሂደት (trend) ለማምለጥ ትቸገራለች። ስለዚህ በሀገራችን ብዝሀነት ባይኖር እንኳን ያልተማከለ የመንግስት ስርዓት - ፌዴራልም ሆነ ሌላ ፌዴራል መሰል ስርዓት (quasi-federal system) - መዘርጋቱ የሚቀር አይመስልም። ስለዚህ የፌዴራል ስርዓት ያስፈልገናል ወይንስ አያስፈልገንም የሚለው ጉንጭ አልፋ ክርክር ላይ ጊዜ ማጥፋቱን ትተን ሶስት መሠረታዊ ጥያቄዎችን እናንሳ:

1. የ1987ቱ ህገመንግስት ሲረቀቅ የፌዴራል ስርዓቱ አሁን ካለው ቅርፅ በተሻለ ሊቀረፅ ወይንም ዲዛይን ሊደረግ ይችል ነበር ወይ?

2. አሁን ያለው የፌዴራል ስርዓት ቅርፅ (institutional design) እንከኖቹ ምንድን ናቸው? እነዚህ እንከኖች በቀላሉ የሚስተካከሉ ናቸው ወይ?

3. በቀላሉ የሚስተካከሉ ካልሆኑ በምን መልኩ አላስፈላጊ ወጤቶቹን (adverse effect) መቀነስ ይቻላል?

## 3. የኢትዮጵያ ፌዴራል ስርዓት ተቋማዊ (institutional) ግድፈቶች

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በፌዴራል ስርዓቱ አቀራረፅና አተገባበር ላይ የተለያዩ ግድፈቶች አሉ ።

- ፍርድ ቤቶች ህገ-መንግስቱን በመተርጎም በኩል ያላቸውን ድርሻ በማሳነስ ህገ መንግስቱና የፌዴራል ስርዓቱ ህይወት (dynamism) እንዲያጣ አድረጓል፤
- የፌዴሬሽን ምክር ቤትን አቋቋምና ስልጣን በተመለከተ ስህተት ተሰርቷል ፤
- በፌዴራል መንግስትና በክልሎች መካከል ያለውን የስልጣንና የሀብት ክፍፍል በተመለከተ ችግር አለ ፤
- በግለሰብ መብትና የቡድን መብት መካከል ሊኖር የሚገባውን ሚዛን ከመጠበቅ አንፃር ክፍተት አለ ፤
- ከፓርላሜንታዊ ይልቅ ፕሬዚደንታዊ ስርዓት ቢደረግ ይሻል ነበር የሚሉ አስተያየቶች አሉ ።

የፌዴራል ስርዓት ያለ ዴሞክራሲ የማይታሰብ ቢሆንም በኛ ሀገር ዴሞክራሲን ከመተግበር አንፃር ብዙ ርቀት እንዳልተሄደ ጠቅላላ መግባባት አለ ። የኢትዮጵያ የፌዴራል ስርዓት ዋና አወዛጋቢ ጉዳዮች ግን እነዚህ አይደሉም። እነኚህ ተቋማዊ እንከኖችና ከመተግበር ጋር የተያያዙ ችግሮች መሆናቸውንና ሊስተካከሉ ይገባል የሚለው ላይ ስምምነት ላይ ከተደረሰና እና ፈቃደኝነቱ (political will) ካለ በቀላሉ ሊስተካከሉ የሚችሉ ናቸው። ዋናው ችግር እና ላለፉት 27 ዓመታት የሚያነታርከን -ምናልባትም ላልተወሰነ ጊዜ አነታራኪ ሆኖ የሚቀጥለው -የፌዴራል ስርዓቱ የብሔር ብዝሀነት ላይ ያለው ትኩረት ነው። ይህም ሲባል የፌዴራል ስርኣቱ ዋና ችግር የብሔር ብዝሀነትን ለማቀፍ መሞከሩ አይደለም። በአንድ ሀገር ውስጥ ያለ ብዝሀነትን ለማጥፋት እና አንድ አይነት (homogenious) ብሔራዊ ማንነት ለመገንባት በሌሎች ሀገሮችም ተሞክሮ ያልተሳካ እንዲያውም ብዙ ጥፋት ያስከተለ ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ የብሔር ማንነትን ፖለቲካዊ ፋይዳ የሌለው (Politically irrelevant) ለማድረግም አይቻልም። በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የብሔር ብዝሀነት ጉዳይ ህገ መንግስታዊ መልስ ማግኘት ነበረበት።

ስለዚህ ዋናው የፌዴራል ስርዓቱ መሠረታዊ ችግር የብሔር ማንነትን ተቋማዊ በሆነ መልኩ ለማስተናገድ መሞከሩ አይደለም። ፕ/ር ዮናታን ተስፋዬ *The original sin of Ethiopian federalism* በሚለው ፅሁፋቸው እንዳስቀመጡት የፌዴራል ስርዓቱ ችግር ወይንም አከራካሪ ጉዳይ ብሔርን ዋነኛው ብቻ ሳይሆን ብቸኛው የፌዴራል ስርዓቱ እና ሀገረ-ስርዓት መገንቢያ መሠረት ማድረጉ ነው። ከዚህም በላይ የብሔር ማንነትን ተቋማዊ በሆነ መልኩ ለማስተናገድ በሚል አንድ ክልል ለአንድ ብሔር የሚለው መርሆ (principle) - ባይተገበርም - የፌዴራል ስርዓቱ መርሆ ሆኖ በሕገመንግሥቱ መቀመጡ ነው። ይህ መርሆ ሙሉ ለሙሉ በተግባር ሊውል የማይችል ነገር ግን በተለያዩ ብሔሮች ዘንድ የማይፈፀም ተስፋ (undue expectations) የሚፈጥር፤ ብሎም ለግጭት እና ብጥብጥ በር የሚከፍት ነው። በደቡብ ክልል የምናየው ቁጥር የለሽ "ክልል ይሰጠን" ጥያቄ የዚሁ መርሆ ውጤት ነው። ይህ መርሆ በጂኦግራፊያዊ መጠናቸው፤ በተፈጥሮ ሀብት ክምችታቸው፤ እንዲሁም በህዝብ ብዛታቸው እጅጉን የተራራቁ ክልሎችን በመፍጠር ክልሎች ከማዕከላዊ መንግስት ጋር እንዲሁም ክልሎች እርስ በርስ ያላቸው ግንኙነት በችግር የተሞላ እንዲሆን አድርጎታል።

በእርግጥ የኢትዮጵያ ፌደራሊዝም የተቀረፀበት ዕሳቤ (mindset) ሀገሪቱ የህዝቦችን ብዝሀነት አስተናግድና አቻችላ ብትኖር ብትቀጥል እሰየው፤ ይህን ማድረግ ካልቻለች ግን እንደ ሀገር መቀጠሏ እርባና የለውም፤ መፍረሷም ክፋት አይኖረውም የሚል

እንጂ ብዝሀነትን ማስተናገድ በአነድነቱዋም መቀጠል አለባት የሚል አልነበረም፡፡ ይህ መገንጠልን ከሚፈቅደው የሕገመንግሥቱ አንቀፅ (አንቀፅ 39) ግልፅ ነው፡፡

ይህን ማለት ግን የፌዴራል ስርዓቱን የቀረፁት ሰዎች የሀገሪቱ ዕጣ ፈንታ ግድ አልሰጣቸውም ለማለት አይደለም፡፡ይልቁን የዘረጉት ስርዓት ብዝሀነትን እንደሚያስተናግድ እና በህዝቦች መካከል ሊነሱ የሚችሉ ግጭቶችን እንደሚያስቀር እንዲሁም ከሀገሪቷ ለመነጠል ሊኖር የሚችለውን ፍላጎት እንደሚያጠፋ እናም የአገሪቱን ቀጣይነት አንደሚያረጋግጥ ጠንካራ እምነት ስለነበራቸው ነው፡፡ አንድ የሳቱት ነገር ይህን ስርዓት ሲቀርፁ ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን ስህተት ሊሰሩ እንደሚችሉ (human fallibility) ስህተቱም መሠረታዊና ሀገሪቷን ችግር ውስጥ ሊከታት እንደሚችል፤ የስህተቱ ውጤትም የማይቀለበስ ወይንም የማይስተካከል (irrevocable) ሊሆን እንደሚችል አለመገንዘባቸው፤ ቢገነዘቡም የሆነው ይሁን ብለው (risk) በእቅዳቸው መቀጠላቸው ነው፡፡

በእኔ እምነት የፌዴራል ስርዓቱ አንዳንድ መገለጫዎቹ (features) ሊስተካከሉ እና ሊለወጡ የማይችሉ ናቸው፡፡ በዚህም ረገድ ዋናው ለአንድ ብሔር አንድ ክልል የሚሰጠውን መርሆ በመከተል የተፈጠሩትን ክልሎች ናቸው ፡፡ እርግጥ ነው በ በ1980ዎቹ ብዝሀነትንና የሀገር አንድነትን ባማከለ መልኩ ክልሎችን መከለል ይቻል ነበር፡፡ የተወሰኑ ተቃውሞዎች ቢነሱም ኢህአዴግ በቀላሉ ሊቆጣጠራቸው ይችል ነበር፡፡ በአሁኑ ሰዓት ትልልቆቹንና በተጠቀሰው መርሆ መሠረት የተከለሉትን ክልሎች ማለትም ኦሮሚያ፣አማራ፣ትግራይ፣ሱማሌ እና አፋር ክልልን ለሁለት ወይንም ከዚያ በላይ ከፍሎ አነስ ያሉና ማዕከላዊ መንግስቶችን የማይገዳደሩ ነገር ግን ብዝሀነትን የሚያስተናግዱ ክልሎች ማቋቋም ይቻላል የሚል እምነት የለኝም፡፡ አንደኛ ክልሎቹ ባለፉት 27 ዓመታት በውስጣቸው የሚኖረውንና የሚተዳደረውን ሕዝብ ማንነት በአንድ ወይንም በሌላ መልኩ ቀርጸውታል፡፡ ስለሆነም በነዚህ ክልሎች ያሉ ህዝቦችም የክልሎቹ መከፈል ላይ ይስማማሉ፤ በበጎም ያዩታል ብዬ አላምንም፡፡ በዚህ ረገድ የሚደረግ ማንኛውም አይነት ሙከራ ከመቃወማቸው በላይ በሙከራው ከተገፋ ሀገሪቷን ወደማያባራ ብጥብጥ እንዳያስገባት እፈራለሁ፡፡

ሁለተኛ በክልሎቹ የሚኖሩ ህዝቦች ባይቃወሙ ወይንም ቢፈልጉ እንኳን በነዚህ ክልሎች እንዳሉ መቀጠል የሚጠቀሙ (entrenched interest ያላቸው) አካላት ወይንም ቡድኖች ትልቅ እንቅፋት መፍጠራቸው አይቀርም፡፡ ሶስተኛ ሀገሪቷ እንዲህ ያለ አብዮታዊ ለውጥ- ወይንም ዶ/ር አስናቀ ከፋለ በቅርቡ በተካሄደ ሴሚናር ላይ እንዳሉት (complete reversal) መቋቋም (withstand) ማድረግ ትችላለች የሚል እምነት የለኝም፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ስርዓቱን ክልሎችን በማፍረስና በመስራት

ለማስተካከል መሞከር እጅግ አደገኛ ነው። በዚህ በኩል የተሰራው ስራ በሉት ግድፈት ሊስተካከል የማይችል ስለሆነ ጥያቄው መሆን ያለበት 'ክልሎችን አፍርሶ ከመስራት በመለስ የህዝቦችን ግንኙነት የሚያስተባብሩ (harmonious) የሚያሻሽሉ ምን አይነት ተቋማዊ እርምጃዎችን መውሰድ ይቻላል?' የሚለው ነው። ከነዚህ የተወሰኑትን ለመጠቃቀስ እሞክራለሁ።

## 4. የሚያስፈልጉ ተቋማዊ ለውጦች

### 4.1. የህዝብ ለህዝብ ትውውቅ የሚያጠነክሩ ተቋማትን መገንባት

ሳሙኤል ላንግሆርን ክሌመንስ (Samuel Langhorn Clemens) - በብዕር ስሙ ማርክ ትዌይን (Mark Twain) - ተብሎ የሚታወቀው ፀሐፊ ብዙ ጊዜ የሚጠቀስለት አንድ አባባል አለ፡-

'Travel is fatal to prejudice and narrow mindedness …Broad, wholesome charitable views of men and things cannot be acquired by vegetating in one little corner of the earth all one's life'.

ምጌል ደ ኡናሙኖ (Miguel de Unamuno) የተባለ ስፔናዊ ፀሐፊም በተመሳሳይ እንዲህ ብለዋል: -

'Fascism is cured by reading and racism is cured by traveling'

የሁለቱም ፀሐፊዎች የተጠቀሱት አባባሎች ዋና መልክት ወደተለያዩ አካባቢዎች መሄድ፣ ሌሎች ህዝቦችን ማወቅ፣ አኗኗራቸውን፤ ባህላቸውን ማየትና መረዳት ቋንቋቸውን ማወቅ ስለሌሎች ያለንን አመለካከት በበጎ ይቀይራል፤ ጥላቻና ጥርጣሬንም ያጠፋል፤ ምሉዕ ሰውም ያደርጋል የሚል ነው።

ይህ በእኛም ሀገር የሚሰራ ይመስለኛል። በአንድ ሀገር ብንኖርም እርስ በርሳችን ገና በደንብ የተዋወቅን አይመስልም። እርስ በርስ ያለን በጥርጣሬ መተያየት ካለመተዋወቃችን የመጣ ይመስላል። ስለዚህ እንደህዝብ የምንተዋወቅበት የምንገናኝበት ተቋማዊ መንገድ ያስፈልገናል። ወደ አማራ ክልል የተጓዘና እዚያ ያሉ አርሶ አደሮች የሚኖሩትን ኑሮ ያየ፣ ችግራቸውን የመሰከረ ኦሮሞ እዚያ ክልል ደርሶ ከሚያውቀው ኦሮሞ እጅጉን የተለየ አመለካከት እንደሚኖረው አያጠራጥርም። ወይንም ትግራይ ውስጥ በሥራ ወይንም በትምህርት ምክንያት ጥቂት ጊዜ የቆየ አማራ የትግራይ እናቶችን ደግነት ርህሩህነት በማየት ወደዚያ አካባቢ ደርሶ ከማያውቀውና እንዲያው በሩቁ ስለ ትግራይ እንዲህና እንዲያ ሲባል ከሚሰማው በተለየ ስለትግራይ ሕዝብ ጥሩ አመለካከት እንደሚኖረው ግልፅ ነው። ስለዚህ

ጥያቄው 'ይህንን የህዝብ ለህዝብ ትውውቅ ለማዳበር ጥሩው ተቋማዊ መንገድ ምንድን ነው የሚለው' ነው።

በዚህ ረገድ ዋናው መሣርያ ትምህርት፤ ዋናዎቹ ኢላማዎችም የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መሆን አለባቸው። ይህን ስል የትምህርት ይዘቶች እርስ በርስ እንዲያስተዋውቁን ሆነው ከመቀረፃቸው ባለፈ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከክልላቸው ወጥተው ወደ አንድ የመረጡት ክልል ሄደው የተወሰነ ጊዜ እንዲያሳልፉ ቢደረግ ፣ ስለሄዱበት አካባቢ ሕዝብ ጥናት እናዲያደርጉ እና ሲመለሱም ለመጡበት ትምህርት ቤት ሪፖርት እንዲያደርጉ ቢደረግ ሁለት ዋና ዋና ጥቅሞች ይኖሩታል። አንደኛ የተማሪዎቹ ስብዕና በበጎ ይቀረፃል። በራሳቸው የሚተማመኑ እና አስተሳሰበ ሰፊ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ሁለተኛ የህዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር እርስ በርስ ለመተዋወቅ ይረዳል ብዬ አምናለሁ።

በእርግጥ በዩኒቨርስቲዎች አካባቢ የምናየው በተማሪዎች መካከል ያለ ጥሩ ያልሆነ ግንኙነት ይህ ያቀረብኩት ሀሳብ እንደማይሰራ እንደማሳያ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል። ነገር ግን ዩኒቨርሲቲ የገቡ ተማሪዎች ከሞላ ጎደል ስለሌላው ሕዝብ የተወሰነ በጎም ሆነ አሉታዊ አመለካከት (prejudice) ይዘው የሚመጡ ስለሆነ ይህንን አመለካከታቸውን ቶሎ መቀየር ሊያቅታቸው ይችላል። ስለዚህ ዋናው ስራ መሰራት ያለበት በልጆች ላይ መሆን ይገባዋል። እንዲህም ሆኖ ምንም እንኳ የተወሰኑ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ያልተገባ ፀባይ ቢያሳዩም እጅግ ብዙዎቹ ከሌላ ብሔር እና ክልል ከመጡ ተማሪዎች ጋር ጥሩ ጓደኝነት ፈጥረው ስለሌላው ሕዝብ ያላቸውንም አመለካከት በበጎ ቀይረው እንደሚወጡ ይታወቃል። ችግሩ በተማሪዎች መካከል የሚደረግ ፀብ እና ግጭት እንጂ መልካም ግንኙነት ዜና አይሆንም፤ አይዘገብምም። በተጨማሪም ከተለያዩ ብሔረሰቦች የተውጣጡ ግለሰቦችን የያዙ ተቋማት (እንደ ፌዴራል ፖሊስና የጦር ሰራዊት) በህዝቦች መካከል ትውውቅን እና መቀራረብን መፍጠራቸው አሌ አይባልም። እንዲህ በብሔር ተከፋፍለን ስንጋጭ እንኩዋን ከሞላ ጎደል ከወገንተኝነት ነፃ በሆነ መንገድ ፀቦችን እያበረዱ ያሉትም እነዚህ ተቋማት መሆናቸውን ልብ ይሏል።

ዓለም አቀፍ ተሞክሮም የሚያሳየን የተማሪዎች ልውውጥ መርሀ-ግብሮች ትልቅ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ማጠንከሪያ ተቋማዊ መንገዶች መሆናችውን ነው። የአሜሪካኖቹ Peace Corps Mission እንዲሁም የአውሮፓውያኑ Erasmus Students Exchnage Programme በዚህ ረገድ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ለምሳሌ የኤራስመስ የተማሪዎች ልውውጥ መርሀ-ግብር አንዱ እና ዋነኛው ግቡ አውሮፓውያን ወጣቶች መካከል የመገናኘት ዕድል በመፍጠር በአውሮፓ ሀገሮች ባጠቃላይ ትብብርን መፍጠር እና ጥርጣሬን ማጥፋት ነው።

በእኛም ሀገር ትምህርትን ለዚህ በጎ ጉዳይ ለማዋል ጥሩ አጋጣሚ ተፈጥሯል። እንደሚታወቀው አዲሱ የትምህርት ፍኖተ-ካርታ በመዘጋጀት ላይ ነው። ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ከላይ የጠቀስኩትን አይነት የተማሪዎች ልውውጥ መርሀ ግብር መንደፍ ያስፈልጋል።

### 4.2. የአካባቢ መንግስታትን ዴሞክራሲያዊ ማድረግ

የአካባቢ መንግስታት (local government) እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ህይወት ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ አላቸው። የመንግስት ጥሩውንም መጥፎውንም ገፅታዎች በቀጥታ የምናየው በአካባቢ መንግስታት እና ባለስልጣናት ነው። በጎ ገፅታቸውን በተመለከተ መታወቂያ የምናገኘው፣ ምግብና ሌሎች ቁሳቁሶች በቀላል ዋጋ የሚቀርቡልን፣ ሰላምና ፀጥታ የሚያረጋገጡልን እና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች የሚሰጡን የአካባቢ መንግስታት ወይንም ባለስልጣናት ናቸው። በሌላ በኩል የአካባቢ መንግስታትና ባለስልጣናት የማዕከላዊ መንግስት የጭቆና መሳሪያ በመሆንም (instrument of oppression) ለዘመናት አገልግለዋል። የንጉሱን ዘመን ትተን በደርግ ዘመን የቀይ ሽብርን በመተግበር፤ አፈሳ ተብሎ የሚታወቀውንና ወጣቶችን ከየቤቱና ከየመንገዱ ተለቅመው ወደ ጦር ማሰልጠኛ የሚላኩበትን ፖሊሲ በመፈፀም፣ እንዲሁም ሰፈራ የተባለውንና የብዙ ሰዎችን ህይወት ያመሰቃቀለውን የደርግ መርሀ-ግብር በሀይል በመተግበር በአሉታዊ ተግባራት ይታወቃሉ። ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘም በኋላ የአካባቢ መንግስታትና ባለስልጣናት ልዩ ልዩ ጨቋኝ ህጎችንና ፖሊሲዎችን መፈፀሚያ መሳርያ ሆነው አገልግለዋል። በተለይም የፓርቲውን በስልጣን ላይ መቆየት ለማረጋገጥ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ በመገደብ፤ በፓርቲው ያልተፈቀዱ ወይንም ያልተዘጋጁ ሰላማዊ ሰልፎችና ህዝባዊ ስብሰባዎችን በመከልከልና ሌሎች ተመሳሳይ እርምጃዎችን በመውሰድ ይታወቃሉ። የሚያሳዝነው ነገር በዚህ ብዙ የህግና የፖሊሲ ለውጦች በሚደረጉበት ባሁኑ ጊዜ የአካባቢ መንግስታትን ዴሞክራሲያዊ ስለማድረግ አስፈላጊነት ከገዢው ፓርቲም ሆነ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ምንም እየሰማን አለመሆኑ ነው። በእኔ አስተያየት የአካባቢ መንግስታትን ዴሞክራሲያዊ ማድረግ ባሁኑ ሰአት እጅጉን ከሚያስፈልጉት ተቋማዊ ለውጦች መካከል አንዱ ነው።

በዚህ ረገድም የአካባቢ መንግስታት እንደሶስተኛ የመንግስት እርከን ህገ መንግስታዊ እውቅና እንዲሰጣቸው ማድረግ፤ ስልጣንና ተግባራቸውን በህገመንግስቱ ውስጥ መዘርዘር እና በቂ ውስጣዊና ውጫዊ ገቢዎች እንዲኖራቸው ማድረግ ወሳኝ ነው። በተጨማሪም የአካባቢ ምርጫዎችን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች አስቸጋሪ ለማድረግ

የወጡ ሕጎችና ፖሊሲዎችን መሰረዝ ያስፈልጋል። እንዲህ ማድረግ ሁለት ዋና ዋና ጥቅሞች ይኖሩታል

1. የአካባቢ መንግስታት በህገ መንግስቱ እውቅና እንዲሁም በቂ የፖለቲካ ስልጣንና የገንዘብ ሀብት እንዲኖራቸው ከተደረገ የፖለቲካ ቁመናቸው ይጨምራል፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በአካባቢ ምርጫ ለመወዳደር የሚኖራቸው ፍላጎትም ይጨምራል። ይህም የአካባቢ ምርጫዎችን በውድድር የተሞሉ ያደረጋል። ህዝቡም በቅርቡ ባሉና በመረጣቸው ባለስልጣናት ይተዳደራል፤ የአካባቢ መንግስታት የጭቆና መሳሪያ የመሆን ዕድላቸው ይቀንሳል።

2. ሕገ-መንግስት እውቅና ያገኙ የአካባቢ መንግስታት መፈጠር አንድ ክልል ለአንድ ብሔር በሚለው መርሆ የተፈጠሩትን ክልሎች ከማፍረስ በመመለስ ሊደረግ የሚችል ከዚህ መርሆ ጋር የተገናኙ ችግሮችን መቀነስ የሚያስችል ተቋማዊ እርምጃ ነው። ስልጣንና ሀብትን ወደ አካባቢ መንግስታት በማሸጋገር በክልሎች መካከል የተፈጠረውን የሚዛን መዛባት በመጠኑም ቢሆን ይቀንሳል። በሕገ-መንግስቱ እውቅና ያለው ሶስተኛ የመንግስት እርከን መኖሩ የየብሔረሰቡን ራስን የማስተዳደሩ መብት ሳይነካ በክልሎች አካባቢ የስልጣን መከማቸትን ያስቀራል። ይህም በክልሎችና በአካባቢ መንግስታት መካከል ፖለቲካዊ ወድድር በመፍጠር ትልልቆቹ ክልሎች የማዕከላዊ መንግስትን ለመጋፋት ያላቸውን አቅም በትንሹም ቢሆን ይቀንሰዋል።

የአካባቢ መንግስታት የተሻለ ስልጣን እና ሀብት ማንቀሳቀስ መቻል በብሔር ድርጅቶች የሚነሳውን የክልል ይሰጠን ጥያቄ ወይንም እንዲህ ያለ ጥያቄ ለማቅረብ የሚጠቀሰቱን ምክንያቶች ይቀንሳቸዋል።

### 4.3. በከተሞችና ክልል ወሰኖች አካባቢ የፌደራሉን የብሔር መርሆ ላላ አድርጎ መተግበር

የፌዴራል ስርዓቱ አንዱ ችግር (shortcoming) ለከተሞችና ወሰን አካባቢዎች ላሉ ማህበረሰቦች ምንም ቦታ የሌለው መሆኑ እንደሆነ ከዚህ በፊት ተደጋግሞ ተነገሯል። ከተሞች በባህሪያቸው የተለያዩ አይነት ማንነቶች የሚገኙባቸውና የሚዋሀዱባቸው ከብዙ ማንነቶች የተቀዱ ልዩ የሆኑ ማንነቶች የሚፈጠሩባቸው ናቸው። በክልል ወሰኖች አካባቢም እንዲሁ ከአጎራባች ህዝቦች የተጨለፉ ማንነቶችና ልዩ ልዩ ባህሪያት እንዲሁም ባህሎች የሚፈጠሩባቸው ናቸው። ከተሞችና በክልል ወሰኖች አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች በተለያዩ ብሔሮች መካከል ያለውን የቋንቋና የባህል ልዩነት ለመሻገር የሚያስችሉ ድልድዮች ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። ስለዚህ የብሔር ፌዴራል ስርዓቱን መርሆዎች በከተሞችና የክልል ወሰኖች አካባቢ በሚገኙ ማህበረሰቦች ላይ ጥንክር ባለ (strict) በሆነ መልኩ መተግበር ተገቢ አይሆንም።

እንደሚታወቀው ከተሜዎችንና በወሰን አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦችን አንድ አይነት (homoginse) ለማድረግ በሚደረግ ጥረት ብዙ ግጭቶች ተከስተዋል፡፡ በኦሮሚያና ሶማሊ ክልሎች ወሰኖች አካባቢ፤ በኦሮሚያና በቤኒሻንጉል ክልሎች ወሰኖች አካባቢ፣ በአማራና ትግራይ ክልሎች ወሰኖች፤እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አካባቢ ያሉ ውጥረቶች የወሰን ወይም የከተሞች አካባቢ ማህበረሰቦችን የዚህ ወይንም የዚያ ክልል ናቸው በሚል በሚደረግ ሽኩቻ እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡ እንዲህ ያለውን ችግር ለመፍታት የክልል ወሰኖችን መለየቱ (delineate) ላይ ከማተኮር ይልቅ ክልሎች ተቀራርበው በመነጋገር እነዚህን ማህበረሰቦች ያላቸውን ልዩ ባህሪ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ተቋማዊ ስልት እንዲነድፉ ቢደረግ ጥሩ ነው፡፡ እንዲህ ያሉ ማህበረሰባት የግጭት ሳይሆን የአንድነት እና የመቀራረብ ምክንያት ሊሆኑን ይችላሉ፡፡ በዚህ ረገድ ለእንዲህ ያለ ማህበረሰብ የሚሆኑ የትምህርት ካሪኩለሞችን ለመቅረጽ፤ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማቀላጠፍ፤ የፀጥታ ጥበቃ ሁኔታዎች ላይ ለመነጋገር የበይነ መንግስታት ግንኙነት (IGR) መድረኮችንና የመሳሰሉትን ተቋማት መፍጠሩ ይመረጣል፡፡

### 4.4. ሁለትና ከዚያ በላይ ቋንቋዎች ተናጋሪ ትውልድ መፍጠር

የብዙ ቋንቋዎች መኖር ለብሔራዊ አንድነት መገንባት እንቅፋት እንደሚሆን በብዙ ሀገሮች - በኢትዮጵያም ጭምር - ይታመን ነበር፡፡ ስለሆነም የተለያዩ ሀገሮች የቋንቋ ብዝሀነትን ለማጥፋት ሞክረዋል፡፡ ባይሳኩም ሙከራዎቹ ራሳቸው ለብዙ ግጭቶች ምክንያቶች ሆነዋል፡፡ አሁን አሁን ግን የብዙ ቋንቋዎች መኖርን እንደ ፀጋ መቁጠር ተጀምሯል፡፡ ቋንቋዎች ፀጋ የሚሆኑት ግን በቋንቋዎቹ ባለቤቶች ብቻ የሚነገሩ ሲሆን ሳይሆን ሌላው ማህበረሰብም የሚጋራቸው ሲሆኑ ጭምር ነው፡፡ በዚህ ግዜ የብዙ ቋንቋዎች መኖር ሀገራዊ አንድነትን ለመገንባት ለሚደረግ ጥረት እንቅፋት መሆኑ ይቀራል፡፡ እንዲያውም ለጠንካራ ሀገራዊ አንድነት መሠረት ይሆናል፡፡ ይህ እንዲሆን በአገራችን ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ ቋንቋዎች የሚናገር ትውልድና ህብረተሰብ የመፍጠር ፖሊሲ መቅረጽ እና መተግበር ያስፈልጋል፡፡ ትምህርት ደግሞ የእንዲህ ያለ ፖሊሲ ማስፈጸሚያ ዋናው መሳሪያ ነው፡፡ እርግጥ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማር አለባቸው፡፡ ግን ደግሞ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ከራሳቸው ቋንቋ ውጭ የሆኑ የሀገር ቤት ቋንቋዎችን እንዲማሩ መሆን አለበት፡፡ ለመማር የሚፈልጉትን ቋንቋ የመምረጥ መብት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ አንዱን ወይንም ሌላውን ቋንቋ መማራቸው ግን የምርጫ ጉዳይ መሆን የለበትም፡፡

እንዲህ ያለ ፖሊሲ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ሌሎች ፌዴሬሽኖች ተግብረውታል፡፡ በስዊዘርላንድ ተማሪዎች ከአፍ መፍቻቸው ሌላ አንድ ወይንም የበለጠ ቋንቋ

እንዲማሩ ይደረጋል። ለምሳሌ ጀርመንኛ ቋንቋ ተናጋሪ ፈረንሳይኛ ወይንም ጣሊያንኛ እንዲማር ይደረጋል። ስለሆነም አንዳንድ የስዊስ ፌዴራል መስሪያ ቤቶች አንዱ የሌላውን ቋንቋ እንደሚረዳ ግንዛቤ በመውሰድ ነው የሚሠሩት። ስለሆነው አንዱ በጀርመንኛ የላከውን ኢሜል ተቀባዩ በፈረንሳይኛ ሊመልስ ይችላል። ነገር ግን ላኪውም ተቀባዩም የትርጉም አገልግሎት ይሰጠን ማለት አይችሉም። እንዲሁም በደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቋንቋ እንዲማሩ ይደረጋል። ስለሆነም ደቡብ አፍሪካውያን ብዙ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች ናቸው። ስለሆነም አንዱ በዙሉ ቋንቋ ሲናገር፣ ሌላው ጦሳ ሲመልስ፣ ሶስተኛው በሴትጽዋና ጣልቃ ሲገባ ማየት የተለመደ ነው።

እኛም በሀገራችን የሚነገሩ ቋንቋዎች - ከመጀመሪያ ደረጃ ጀምሮ - በትምህርት መልክ እንዲሰጡ ቢደረግ በአስር አመት ጊዜ ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ ቋንቋዎች ተናጋሪ ትውልድ ማፍራት እንችላለን። ይህ በራሱ ጥሩ የብሔራዊ አንድነት መፍጠርያ መንገድ ነው። ከዚህም በላይ ሁለትና ከዚያ በላይ ቋንቋዎች የሚናገር ትውልድና ህብረተሰብ መፍጠር ሌሎቹን ከላይ የተጠቀሱትን የህገ መንግስት ግቦች እንድንፈፅም ይረዳናል። በክልሎች መካለል ያለውን የንግድ እንቅስቃሴ በማሳለጥ አንድ ምጣኔ ሀብታዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያስችለናል። የዜጎችን ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ መኖር መብት በትክክል ለመተግበር የዜጎች ብዙ ቋንቋ መቻል የራሱ እንድምታ አለው ። የተዛቡ ታሪካዊ ግንኙነቶችን ለማረምም ይረዳናል፣ አንዱ የተዛባ ታሪካዊ ግንኙነታችን መግለጫው በቋንቋ ላይ የተመሰረተ መገለል ስለነበር። ኢትዮጵያውያን የትም ሲገናኙ በአንድ ወይም በሌላ ቋንቋ የመግባባት ዕድል ይኖራቸዋል። ይሄ ደሞ ብሔራዊ አንድነትን ለማጠናከር ያለው ጥቅም ግልፅ ነው።

### 4.5. የፌዴራል መንግስቱን ቢያንስ በሁለት ቋንቋዎች የሚሠራ ማድረግ

የፌዴራል መንግስቱን ቢያንስ በሁለት ቋንቋዎች የሚሠራ፣ ከተቻለ ደግሞ ከሁለት በላይ በሆኑ ቋንቋዎች የሚሠራ ማድረግ ይገባናል እላለሁ። ይሄ ሀሳብ ከላይ ከተነሳውና ብዙ ቋንቋ የሚናገር ማህበረሰብ መፍጠር ከሚለው ሀሳብ ጋር በቀጥታ ይገናኛል። ብዙ ቋንቋ የሚናገር ማህበረሰብ መፍጠር ከቻልን የፌዴራል መንግስቱን ቢያንስ በሁለት ቋንቋዎች የሚሠራ ማድረግ አይከብደንም ።

ህገ መንግስቱ ሲረቀቅ አማርኛን ብቸኛው የፌዴራል መንግስት የጋራ ቋንቋ እንዲሆን ከተመረጠባቸው ምክንያቶች ውስጥ ቋንቋው በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚነግር መሆኑ እና ከሌሎች ቋንቋዎች በተሻለ የእድገት ደረጃ ላይ የነበረ መሆኑ ነበር። ይህ አመክንዮ ትክክል ነበር ወይንም አልነበረም የሚለውን ወደጎን ትተን በጊዜው አማርኛን የፌዴራል የስራ ቋንቋ አድርጎ የፌዴራል መንግስቱ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ - ለምሳሌ በ

10 ወይንም 20 አመታት ውስጥ- ሌላ አንድ ወይንም ሁለት ቋንቋዎች የፌዴራል መንግስቱ የስራ ቋንቋ መሆን የሚችሉበትን ሁኔታ እንዲፈጥር የሚያስገድድ አንቀፅ ማስገባት ጥሩ አማራጭ ይሆን ነበር። ያ ሆኖ ቢሆን ኖሮ በዚህ ረገድ ባለፉት 20 ዓመታት ብዙ ርቀት መጓዝ በቻልን ነበር።

የፌዴራል መንግስቱ በሁለት ወይንም ከዚያ በላይ ቋንቋዎች የሚሠራ ይሁን ሲባል ሁለት አማራጮች አሉ። አንደኛው አማርኛ፣ ኦሮምኛ ፣ትግርኛ የመሳሰሉት ቋንቋዎች ጎን ለጎን የሚያገለግሉበት ነው። የፌዴራል መንግስቱ ለአማርኛ ተናጋሪዎች በአማርኛ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሌላውም እንዲሁ በመረጠው ቋንቋ አገልግሎት የሚያገኝበትን መንገድ ያመቻቻል ማለት ነው። ይህ ማለት በእያንዳንዱ አገልግሎት ሰጪ ፌዴራል መስሪያ ቤት፤ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የቋንቋ መስኮቶች ይኖራሉ ማለት ነው። የዚህ አማራጭ ችግሩ አንዱ የሌላውን ቋንቋ እንዲያውቅ ምክንያት አይሠጠውም። ሀገራዊ አንድነት ለመፍጠርም አይረዳም። ሌላው አማራጭ የፌዴራል መንግስት ለምሳሌ በሁለቱ ቋንቋዎች በአንድ ጊዜ እንዲሰራ ማድረግ ነው። ይህም በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት የሚሠሩ ሰራተኞች ከአንድ በላይ ቋንቋ እንዲችሉ ማድረግን ይጠይቃል። በቅጥር ጊዜም ከአንድ በላይ የፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋዎችን መናገር ለሚችሉ ቅድሚያ ይሠጣል ማለት ነው። አለም ዓቀፍ መስሪያ ቤቶች እንግሊዝኛ እና ፈረንሳይኛ ለሚችሉ ቅድሚያ እንደሚሰጡት ማለት ነው።

ይህ ሀሳብ ተግባራዊ የማይሆን ወይንም ብዙ ውጪ የሚያስወጣ ሊመስል ይችላል። እኔም ለመተግበር ቀላል፤ በአጭር ጊዜም ለውጡ የሚታይ ይሆናል ብዬ አላምንም።ጊዜ እና ወጪ ይጠይቃል። ሀሳቡም ተቃውሞ ሊገጥመው ይችላል። ተቃውሞው እንዲህ ያለ የቋንቋ አጠቃቀም ለሀገራዊ አንድነት ያለውን ፋይዳ ካለመገንዘብ የመነጨ ሊሆን ያችላል ብዬ አስባለሁ። ስለሆነም፤ እንዲህ ያለ ፖሊሲ ከመተግበሩ በፊት ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል። ምንም ያህል ጊዜ ቢወስድ እና ወጪ ቢያስውጣም በሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ ቋንቋዎች የሚሰራ የፌዴራል መንግስት መፍጠር ታላቅ ሀገራዊ አንድነት የመፍጠር ችሎታ አለው ብዬ በጥልቅ አምናለሁ።

### 4.6. ከአንድ በላይ የፌዴራል መዲና

ህገ መንግስታችን አዲስ አበባን ብቸኛዋ የፌዴራል መዲና አድርጎ ሰይሟታል። የሕገ-መንግስቱ አርቃቂዎች "ተጨማሪ መዲና ይኑረን አይኑረን?" የሚለውን ምን ያህል እንዳሰበበት እርግጠኛ አይደለሁም። ለማንኛውም ተደጋግሞ እንደሚነሳው አዲስ አበባ ብቸኛዋ የፌዴራል መዲና እንድትሆን ለማድረግ የተፈለገበት ዋንኛው ምክንያት አገልግሎቶችን በቀላሉ ማድረስ ትችላለች በሚል ነው። በመሆኑም ሁሉም የፌዴራል

መንግስት አካላት በከተማዋ ከትመው ይገኛሉ። እኔ ከአዲስ አበባ በተጨማሪ ሁለት የፌዴራል መዲናዎች ያስፈልጉናል የሚል እምነት አለኝ። ከሶስቱ የፌዴራል መንግስት አካላት ሁለቱ - በተለይም ህግ አውጭውና የዳኝነት አካሉ - ወደነዚህ አዲስ መዲናዎች ቢዛውሩ ጥሩ ይሆናል። እንዲህ ምድረግ የምጣኔ ሀብት፣ የፖለቲካና የማህበራዊ ጥቅሞች ያመጣል። ከሁሉ በላይ ግን ብሔራዊ አንድነት ለመገንባት ይጠቅመናል የሚል እምነት አለኝ ።

ከምጣኔ ሀብት ጥቅሙ ልጀምር። እንደሚታወቀው በአዲስ አበባ ታላቅ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ እና የሀብት ክምችት አለ። ለምሳሌ በአገሪቷ ከሚገኙ መኪኖች 50% በላይ የሚሆኑት በመዲናዋ የሚገኙ መሆኑ በከተማዋ ያለውን የሀብት ክምችት ያሣያል። አብዛኞቹ የመሠረተ-ልማት ስራዎችም በመዲናይቱ ነው የሚካሄዱት። በሌላ በኩል የክልል ከተሞች ከአዲስ አበባ አንጻር-የረባ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ አይታይባቸውም። የከተማ ልማትና የቤቶች ጉዳይ ሚኒስትር በ2007 (በፈረንጆቹ አቆጣጠር) ያወጣው ሪፖርት እንደሚያሳየው የክልል ከተሞች ደካማ ምጣኔ ሀብታዊ መሠረት፣ ትልቅ የስራ አጥ ቁጥር፣ እና ስር የሰደደ ድህነት ይታይባቸዋል። በኢትዮጵያ ከሚደረጉት ማጣኔ ሀብታዊ ኢንቨስትመንቶች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በአዲስ አበባ ውስጥና በአካባቢዋ እንደሚደረጉ የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ። ይህም አዲስ አበባ የክልል ከተሞችን ብቻ ሳይሆን ክልሎችንም በምጣኔ ሀብት ቁልቁል እንድታይ አድርጓታል። ለምሳሌ የአዲስ አበባ 2016-17 የበጀት ዓመት በጀት 35.4 ቢልዮን ብር (1.6 ቢልዮን ዶላር) ነበር። ይህ የከተማዋ በጀት-ከኦሮሚያ በቀር - ከሁሉም ክልሎች በጀት ይበልጣል። በተጠቀሰው የበጀት ዓመት የአማራ ክልል በጀት 32.7 ቢልዮን ብር ነበር። የደቡብ ክልል በጀት ደግሞ 27.7 ቢልዮን ብር ነበር። ይህ በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባና በክልሎች ጭምር ያለውን የሀብት አለመመጣጠን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

አዲስ አበባን እንዲህ በምጣኔ ሀብት ከሌሎች ከተሞች ልቃ እንድትገኝ ያደረጋት የሀገሪቱ መዲና መሆኗ እንደሆነ ጥያቄ የለውም። እንዲህ ያለ ያልተመጣጠነ የሀብት ስርጭት የማይፈለግ ብቻ ሳይሆን ኢ-ህገ-መንግስታዊም ጭምር ነው። ስለሆነም ይህንን የሀብት ክፍፍል አለመመጣጠን ለማስቀረት አስፈላጊው እርምጃ መውሰድ አለበት። ከሚወሰዱ እርምጃዎች መካከልም ሌሎች ሁለት የክልል ከተሞች የመዲናነትን ጥቅም ከአዲስ አበባ ጋር እንዲጋሩ ማድረግ ሊሆን ይችላል። የህግ አውጭውና የህግ ተርጓሚው የፌዴራል መንግስት አካል ወደ ሌሎች የክልል ከተሞች ማዛወር ደግሞ ሌሎች ከተሞች የመዲናነትን ጥቅም የሚጋሩበት መንገድ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። እንዲህ ማድረግ ለተጨማሪ መዲናነት የሚመረጡት ከተሞችና

አካባቢዎቻቸው ላይ የታሻለ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ እንዲኖር ይረዳቸዋል፡፡ ትልቅ መዋለ-ንዋይም ወደነዚህ ከተሞች መዞሩ አይቀርም፡፡

በተጨማሪም በአሁኑ ሰአት ትልቅ ከገጠር-ወደ-ከተማ ፍልሰት እንዳለ ይተወቃል፡፡ የዚህ ፍልሰት ጫና ከበዛባቸው ከተሞች ደግሞ አዲስ አበባ የመጀመሪያዋ ናት፡፡ ከተማዋ ከጊዜ ወደ ጊዜ በህዝብ ብዛት እየተጨናነቀች፤ በአካባቢ ብክለት እየተጎዳች፤ እንዲሁም በትራፊክ እንቅስቃሴ እየታፈነች ትገኛለች፡፡ ወንጀልና የመኪና አደጋ በሚያስደነግጥ ሁኔታ በከተማዋ እየጨመረ ነው፡፡ ከተማዋ እንደ ጤና ትራንስፖርትና የመሳሰሉትን መሠረታዊ አገልግሎት ለነዋሪዎች በበቂ ሁኔታ መስጠት የማትችልበት ደረጃ ላይ ደርሳለች፡፡ በታክሲና በአውቶቡስ መጠበቂያዎች - በስራ ሰዓት ጨምሮ - የሚታዩት ረጃጅም ሰልፎች ይህንን ያሳያሉ፡፡ ሁለት ሌሎች ከተሞችን የፌዴራል መዲና መድረግ የከተማዋን ሸክም በትንሹም ቢሆን ያቀልላታል የሚል እምነት አለኝ፡፡ በሁለቱ አዳዲስ መዲናዎች በሚፈጠሩት የምጣኔ ሀብት ዕድሎች የተወሰኑት ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት የሚያስቡትን ይስባል ብዬ ስለማስብ፡፡

በተጨማሪም አዲስ አበባ ባለፉት 20 ዓመታት የግጭት ምክንያት ሆና ከርማለች፡፡ በግጭቶቹም ብዙ ሰዎች ሞተውብናል፡፡ ግጭቱ በዋናነት ቁጥሩ እያደገ የመጣው ነዋሪዋን ለማኖር ከተማዋ ወደ ጎን እየተለጠጠች በመምጣቷ እና የኦሮሚያን ወሰኖች በመጋፋቷ ነው፡፡ ሁለት መዲናዎች ቢኖሩን የከተማዋን ማደግ ማቆም ባይቻልም እንኳን የምታድግበትን ፍጥነት መቀነስ ይቻላል፡፡ በዚያውም ከከተማዋ መስፋፋት ጋር በተያያዘ የሚነሡ ግጭቶችን ማስቀረት ይቻላል፡፡

ከሁሉም በላይ ግን ተጨማሪ ሁለት የፌዴራል መዲናዎች መኖራቸው ለብሔራዊ አንድነታችን ይጠቅማል እላለሁ፡፡ የብሔራዊ አንድነት ለመገንባት የተለዩ ብሔሮች፤ የሀይማኖት ተከታዮች፤ የባህል ቡድኖች መገናኘትና መተዋወቅ አለባቸው፡፡ እንዲህ ያለው ተራክቦ ነው ወደ በለጠ መግባባት የሚያመራው፡፡ ሁለት ተጨማሪ መዲናዎች የሚኖሩን ከሆነ ካሉት የክልል ከተሞች መካከል ነው የሚሆኑ፡፡ እነኝህ ከተሞች ከላይ ያልኩትን ተራክቦ ለመፍጠር ይረዳሉ ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህም የሚሆነው ከሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች የመጡ የፌዴራል መንግስት ሠራተኞች፤ የተወካዮች ምክር ቤት አባላትና ቤተሰቦቻቸው በነዚህ ከተሞች መኖር ስለሚጀምሩ ማለት ነው፡፡ ሌሎችም አገልግሎት ፍለጋ ወደነዚህ ከተሞች የክልል ወሰኖችን አልፈው መሄድ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም በህዝቦች መካከል መገናኘትን እና መተዋወቅን በመፍጠር ብሔራዊ አንድነታችንን ያጠነክራል እላለሁ፡፡

እዚህ ጋር ማስመር የምፈልገው ሁለቱ የፌዴራል መንግስት አካላት ወደነዚህ ሁለተኛና ሦስተኛ መዲናዎች ሲዛወሩ ከተሞቹ እንደ አዲስ አበባ በፊደራል መንግስት

ስር ይሁኑ እያልኩ አይደለም፡፡ ከተሞች የሚገኙባቸው ክልሎች በከተሞች ላይ ያላቸውን ስልጣን ይዘው መቀጠል ይችላሉ፡፡ የፌዴራል መዲናነት በከተሞቹ ላይ የሚጫን መሆንም የለበትም፡፡ የሚመለከታችውን የክልልና የከተማ ነዋሪዎችን በማሣተፍ የሚወሠን መሆን አለበት፡፡ እንዲያውም የተወካዮች ምክር-ቤትን ወይንም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድቤትን በውስጣቸው እንዲሆኑ የሚፈልጉ ከተሞች እኒህን አካላት ማስተናገድ የሚችሉ መሆናቸውን ማሣየት እና ለዚህም ክብር ይመረጡ ዘንድ ለምን እንደሚገባ ማስረዳት እና መወዳደር አለባቸው፡፡

## ማጠቃለያ

የፌዴራል ስርዓቱ የተመሰረተበት መርሆ እና በዚህም መርሆ መሠረት የተበጁትን ክልሎች አፍርሶ እንደገና ለመስራት መሞከር ሌላ ያላሰብነውን መዘዝ ይዞ እንዳይመጣ እፈራለሁ፡፡ ይህን ከማድረግ ይልቅ ስርዓቱ የተመሰረተበት መርሆ ያመጣቸውን እና ሊያመጣ የሚችላቸውን ችግሮችና አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለመቀነስ የሚረዱ የተለያዩ ተቋማዊ ለውጦችን ማድረጉ ላይ ማተኮሩ ይበጃል፡፡ በዚህም ረገድ በህዝቦች መካከል መተዋወቅን መቀራረብን ሊፈጥሩ የሚችሉ ተቋማዊ ለውጦች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል እላለሁ፡፡

# የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕዝባዊ ምርጫና የሕዝብ ውክልና በኢትዮጵያ

# የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ህዝባዊ ምርጫና የህዝብ ውክልና በኢትዮጵያ

*ካሳሁን ብርሀኑ*

***መግቢያ***

በዚህ አጭር ጽሑፍ በርዕሱ ላይ የተመለከቱትን ጉዳዮች በአጭሩ ለመዳሰስ ተሞክሯል:: በእነዚህ ጉዳዮች ላይ መነጋገርና ሀሳብ መለዋወጥ እንዲሁም የጋራ ተግባራዊ ተግባቦትን መፍጠር አስገዳጅና ወቅታዊ የሚያደርጉ በርካታ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል:: በተለይም በአሁኑ ወቅት መጪውን ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ አስመልክቶ የህብረተሰብ ክፍሎችና የሚዲያ ድረ-ገጾች የተለያዩ አመለካከቶችና ዕሳቤዎች ከነደጋፊ ምክንያቶቻቸው ሲያንፀባርቁ ይስተዋላል:: እንደሚታወቀው ካለፈው አንድ አመት ጀምሮ የተከናወነውን የአስተዳደር ለውጥ ተከትሎ በብሩህ ተስፋ የታጀቡና አሳሳቢ የሆኑ የነውጥ ተግዳሮቶችን የተላበሱ ሁነቶችን በተጓዳኝ ታዝበናል:: ለውጡን ተከትሎ የተለያየ አመለካከት የሚያራምዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር በፊት ከነበረው በደርዘኖች እየጨመረ መምጣቱ እውን ሆኗል:: ስለዚህ ይህ ጽሁፍ ከላይ የተጠቀሱትን የቅርብ ጊዜ ክስተቶች እንደ መንደርደሪያ በመውሰድና በርዕሰ ጉዳዮቹ ላይ አጫጭር ታሪካዊ ዳራዎችን በማንሣት ይጀምራል :: በማስከተልም ሀገሪቱ በአሁኑ ወቅት ከምትገኝበት ተጨባጭ ሁኔታና የታሪክ ምዕራፍ አንፃር የፖለቲካ ፓርቲዎችን ቁመና፣ ሕዝባዊ ምርጫንና የህዝብ ውክልናን ገጽታ በመዳሰስ በ2012 ሊካሄድ የታሰበውን ምርጫ አስመልክቶ ሁኔታዎችን እንዴት ማስተናገድ እንደሚገባን የግል አመለካከቴን ለማካፈልና በዚህም ላይ ሀሳብ መለዋወጥና ከተቻለም ስምምነት ላይ ሊያደርሱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ለመጠቆም እሞክራለሁ::

## የፖለቲካ ፓርቲዎች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የፖለቲካ ፓርቲ ምን ዓይነት የሰዎች ስብስብ እንደሆነ፣ ለምን ዓላማና ግብ እንደሚቋቋምና እንዴት እንደሚንቀሳቀስ በማሳየት በሀገራችን የፓርቲዎች አመሠራረት በተለያዩ የፖለቲካ ሥርዓቶች ሥር ምን እንደሚመስል በአጭሩ ለመቃኘት ተሞክሯል::

በርካታ የመስኩ ፀሐፍት እንደሚስማሙበት የፖለቲካ ፓርቲ ተመሣሣይ የፖለቲካ አስተሳሰብና የርዕዮተ ዓለም አቅጣጫ የሚያስተናግዱ ዜጎች የሚሰባሰቡበት

ድርጅት ነው:: ይህ ስብስብ በተለያዩ ሀገሮች የተለያዩ ስሞችና ቅርጾችን ይዞ ወደ ሥራ ይገባል:: በሀገራችንም የፓርቲ ፖለቲካ ቅርፅ እየያዘ በቅርብ ጊዜ ብቅ እያለ ከመጣ ወዲህም እነዚህ ስብስቦች ንቅናቄ፣ ግንባር፣ ድርጅት፣ቅንጅት፣ ፓርቲ የሚባሉ ስሞችን በመያዝ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባታቸውን እንረዳለን:: በንጉሣዊው የአስተዳደር ዘመን የ1948ቱ የተሻሻለው ሕገ-መንግስት አንዳንድ የዲሞክራሲ መብቶችን (የጽሑፍ፣ ሀሳብን የመግለጽ እና የንግግር) ቢፈቀድም በተግባር ደረጃ ለእነዚህ እውን መሆን ይህ ነው የሚባል ዕድል ሳይፈጠር የይስሙላ ሆኖ ቀርቷል:: በመሆኑም የፖለቲካ ፓርቲዎች መፈጠርና ወደ ሥራ የመግባት ጉዳይ ሙሉ በሙሉ የማይቻልና የማይሞከር አደገኛ ዝንባሌ ተደርጎ ስለተቆጠረ የፖለቲካ ሥርዓቱ የፓርቲ-አልባ መገለጫነትን ተላብሶ እንዲቆይ ሁኔታዎች አስገድደዋል:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በጣም የተወሰኑ ስብስቦች እጅግ ምስጢራዊ በሆነ መንገድ አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ወደ ሥርዓቱ ማክተሚያ ገደማ ውስን ሙከራዎች ማድረጋቸው ባይቀርም የተጓዙበት ርቀት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: እንደ ብዙዎች ምልከታ ይህ ሁኔታ በ1966ቱ መጠነ ሰፊ የህዝብ እንቅስቃሴ ወቅት የተፈጠረውን ክፍተት በመሙላት የዘውዱን ሥርዓት በማስወገድና እርሱንም ተክቶ ሥልጣን ለመያዝ የሚችል የፖለቲካ ኃይልና አደረጃጀት እንዳይኖር ጉልህ ሚና ተጫውቷል::

ይህ በዚህ እንዳለ፣ የዘውዱን ስርዓት በኃይል ለማስወገድ የተደራጀ የትጥቅ እንቅስቃሴ የጀመሩ እንደ ኤርትራ ግንባሮች የመሳሰሉ በዘውግና በክልላዊነት ዕሳቤ ዙሪያ የሚሽከረከሩና የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የተገዳደሩ የፖለቲካ ቡድኖች መፈጠራቸው አልቀረም:: በንጉሣዊው አስተዳደር ዘመን ሰፍኖ የቆየውና የዜጎችን የፖለቲካ ህይወት ትርጉም-አልባ ያደረገው አጠቃላይ ድባብም፣ በአንፃራዊነት የተሻለ ቁመና የነበረው የወታደሩ ክፍል በ1966ቱ አብዮት ግለት በመጀመሪያ አስተባባሪ ኮሚቴ ቀጥሎም ደርግ ተብሎ የሚታወቀውን አደረጃጀት ፈጥሮ ሥልጣነ-መንግሥትን ለመቆጣጠር አስችሏል:: ይህ አካልም ገና ከመነሻው የተለያዩ አቋሞችን በሚያራምዱና በተፃራሪ ጎራዎች በተሰለፉ የውስጥ ኃይሎችና ተስፋፊነትና የተለያዩ ዓላማዎች በነበራቸው የውጭ ተዋንያን የተቃጡበትን ተቃውሞዎችና ግፊቶች ተቋቁሞ በ1983 እስከወደቀ ድረስ አምባገነናዊ ሥልጣኑን አስጠብቆ መቆየት ችሏል::

## የድህረ- 1966 አብዮት ሁነቶች ዳሰሳ (1967-1983)

የ1966ቱን የኢትዮጵያ አብዮት መቀጣጠል ተከትሎ የተለያዩ አቋሞችን የሚያራምዱ ተመሣሣይና ተፎካካሪ ርዕዮተዓለማዊ ዝንባሌዎችን የሚያቀነቅኑ በርካታ የፖለቲካ ቡድኖች ተደራጅተው በከፊል ህጋዊነት፣ በሕቡዕና፣ ከሕጋዊ

እውቅና ውጭ ተሰባስበው ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ገብተዋል። እነዚህም በድርጊት መርሐ-ግብሮቻቸው ላይ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በከተማና በገጠር በሰላማዊ (አምስቱ የኢማሌዲህ አባል ድርጅቶችና ሌሎች) አልያም በትጥቅ ትግል (ኢህአፓ፣ ህወሐት፣ ኦነግ፣ ኢዲህ ወዘተ…) ተሰማርተው ነበር። ይህ የመጨረሻው አዝማሚያ ቀደም ብለው ወደ ትጥቅ አመጽ የገቡትን የኤርትራ ግንባሮችንም ያካትታል።

ወታደራዊው ደርግ ገና ከመጀመሪያው ከራሱ ፈቃድና ይሁንታ ውጭ ተደራጅተው ለመንቀሳቀስ የሞከሩትን የፖለቲካ ኃይሎች በጥርጣሬ ከማየት አልፎ አስቻይ ሁኔታዎችን በመንፈግና መንግስታዊ ሥልጣኑን ተጠቅሞ የመቆጣጠር አዝማሚያ ቢያሳይም በሂደት ከአንዳንዶቹ ጋር ተቀራርቦ መሥራት ጀምሮ ነበር። ይህም በተለይ በኋላ በኢማሌድህ ጥላ ስር የተሳሰቡትን ቡድኖች ይመለከታል። እነዚህም ከትጥቅ ትግል በፀዳ ሁኔታ መንቀሳቀስን በመምረጣቸውና የደርጉን አንዳንድ ተራማጅ እርምጃዎች በመደገፋቸው እውቅና አግኝተው ወደ ሥራ በመግባት ተደራጅተው ተከታዮችና ደጋፊዎችን ለማፍራት ችለዋል።

የኢማሌዲህ አባል ድርጅቶች ከሞላ ጎደል በአብዮቱና በሀገሪቱ ዋና ዋና ጥያቄዎችና ጉዳዮች ላይ አጠቃላይ ስምምነት የነበራቸው ቢሆንም ግንኙነቶቻቸው በአብዛኛው በጥርጣሬና ፈር-በለቀቀ ሽኩቻና ጥርጣሬ የታጀበ መሆኑ አልቀረም። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ቢችሉም ዋና ዋናዎቹ በደርጉ አሠራሮች ላይ የነበራቸው ምልከታ አለመጣጣም፤ አንዳንድ አመራሮች ላይ ሰፍኖ የነበረው የዝቅተኝነት ስሜትና፣ ፈርየሳተ አድርባይነት ዝንባሌ የልዩነትና የሽኩቻ መንስኤዎች ነበሩ። እነዚህ ዝንባሌዎችም ማናቸውንም ያልጠቀሙና ይልቁንስ በየተራ የደርጉ የእመቃ ሰለባዎች በመሆን በተለያዩ ጊዜያት የሕልውናቸውን መክሰም እውን አድርገዋል።

ይህ ክስተት በደርጉ ሊቀመንበር ፈላጭ ቆራጭነት የተመራውን ኢሠፓ የተባለውን ብቸኛ ሕጋዊ ድርጅት በማስፈን ተቋጭቷል። የኢሠፓ ማቋቋሚያ አዋጅም ካለዚህ ገዥ ፓርቲ በስተቀር ሌላ የፖለቲካ ቡድን ሕጋዊ እውቅና እንደማይኖረውና ይህንን ድንጋጌ በመጣስ መንቀሳቀስ መሞከር የሚያስጠይቅና ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን በማስታወቁ በህግ ማዕቀፍ የሚንቀሳቀስ አንድም ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ እንዲኖር አላስቻለም። በዚህም ምክንያት ከንጉሣዊ ወደ ወታደራዊ አስተዳደር የተደረገው የሥልጣን ሽግግር ከፓርቲ-አልባነት ወደ አንድ ፓርቲ ህልውና መረጋገጥ ያዘነበለ የፖለቲካ ስርዓት ነው በሚል በማጠቃለል ይቻላል።

ከሕጋዊነት ክልል ውጭ በተለይም በትጥቅ እንቅስቃሴ የተሰማሩት የፖለቲካ ኃይሎች በየራሳቸው በቀየሱት ስልት በየፊናቸው ወደ ትግል ቢገቡም፣ በመካከላቸው በተፈጠሩት የአመለካከት፣ የታክቲክና ስትራቴጂ ልዩነቶች የተነሣ ደም አፋሳሽ ግጭቶችን አስተናግደዋል:: በኤርትራ የተለያዩ ግንባሮች፣ በኢህአፓና በኢዲህ፣ በትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅቶችና በሌሎችም መካከል የተከናወኑትን ለአብነት ማውሳት ይቻላል:: እነዚህም በአንድ ወይም በሌላ ወቅት እንደየ ዝንባሌና የአመለካከት ቅርበታቸው በየጎራው ግንባር በመፍጠር ተቃዋሚዎቻቸውን በመፋለምና እንደ ሁኔታውም አሰላለፋቸውን እየለዋወጡ ቆይተዋል:: በመጨረሻም በህዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይና በኤርትራ ሕዝብ ነፃነት ግንባር መካከል የተፈጠረው የትግል ትብብር እስከ 1983 ድረስ ዘልቆ የቆየውን የደርጉን ወታደራዊ አስተዳደር ለማስወገድ በቅቷል:: ከደርጉ መወገድ በኋላም ሕወሓት/ኢህአዴግ በኢትዮጵያ የመንግሥት ሥልጣንን በመቆጣጠር ለኤርትራ የነፃ ሀገርነት ጥያቄ እውቅና ሊሰጥ ችሏል:: እዚህ ላይ ማስታወስ የሚገባው፣ ደርግን በትጥቅ ትግል ሲታገሉ በነበሩት አማጽያንና ከደርጉ ጋር ለጊዜውም በትብብር ሲሠሩ በነበሩት መካከል የነበረው ግንኙነት የሻከረና በጠላትነት የሚፈረጅ ነበር:: አማጽያኑ ባላንጣዎቻቸውን የአምባገነን አገዛዝ ተባባሪዎች ናቸው ብለው ሲከሱ፣ የኋለኞቹ በፊንታቸው የፊተኞቹን ለሀገርና ለሕዝብ ሕልውና መቀጠል አደጋ የሚያስከትሉና የባዕዳን ኃይሎች መሣሪያ ሆነው የሚንቀሳቀሱ የጥፋት መልዕክተኞች አድርገው ይገልጿቸው ነበር:: ይህ አዝማሚያ እየጎለበተ መጥቶ በተለይም ኢህአፓ በተባለው ቡድንና በኢማሌዲህ አባል ድርጅቶ መካከል ግጭት አስከትሎ የበርካታ መቶዎች ዜጎችን ህይወት ያወደመውን ነጭና ቀይ ሽብር የተባሉ አሳዛኝ ክስተቶችን እውን አድርጓል::

ከላይ እንደተገለፀው፣ በጅምር ላይ የነበረው በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲ አመሠራረት ሂደት ተመሰቃቅሎና በተግዳሮቶች ተሞልቶ ተዋንያኑን በማዳከምና በመበታተን ከ1983 ጀምሮ ኢህአዴግ ወደሚመራው የፖለቲካ ስርዓት ተሸጋግሯል:: ከዚህ በመቀጠል በድህረ- 1983 የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁመናና የተግባር እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል እንመለከታለን::

## ፖለቲካ ፓርቲዎችና በኢህአዴግ የተመራው የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ

ደርግ በመባል የሚታወቀው ወታደራዊ አስተዳደርና የፈጠረው ኢሠፓ የተባለው መሪ የፖለቲካ ድርጅት ለ17 ዓመታት በብቸኝነት የመንግስት ሥልጣንን ተቆጣጥሮ ከቆየ በኋላ በግንቦት 1983 በጦር ኃይል ተወግዷል:: ደርጉን የተካውና የኢትዮጵያን መንበረ መንግሥት የተረከበው ኢህአዴግ ከ1983 ጀምሮ ተከታታይ የለውጥ እርምጃዎችን እንዲወስድ የገፋፉት በርካታ ዓለማቀፋዊና ሀገራዊ

ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። ከእነዚህም እርምጃዎች መካከል የዜጎች ሀሳብን የመግለፅ፣ የመደራጀትና በሀገሪቱ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወት ውስጥ የመሳተፍ መብቶችና ነፃነቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮች ተካተዋል። ለተቀየሰው የለውጥ አቅጣጫም በመጀመሪያ የሽግግር ወቅት ቻርተሩ ቀጥሎም የኢፌዲሪ ህገ-መንግስትና ሌሎች ተጓዳኝ ድንጋጌዎች ህጋዊ እውቅና ድጋፍ እንዲሰጡ ሆነው ተቀርፀዋል። እነዚህ በተግባር ሲተረጎሙ በተከታታይ በርካታ ዓመታት ሁኔታዎች ምን እንደሚመስሉና ያስከተሏቸው እንድምታዎች የፈጠሯቸው ዕድሎችና ተግዳሮቶች በፓርቲዎች ህልውና ላይ ያሳደሩትን ተፅእኖ ለይቶ መመልከት ያስፈልጋል።

የ1983 የመንግሥት ስርዓት ለውጥ ማዕከላዊ አውታሮች ከሚባሉት መካከል የብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን ማረጋገጥና የሀገሪቱን የፖለቲካ ሥርዓት በፌዴራላዊነት የማዋቀር ዙሪያ እንዲሽከረከር ተወስኖ አዲሱ አዝማሚያ በፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀትና አሠራር ላይ ተጽእኖ ለማሳደር በቅቷል። በሽግግር ወቅት ቻርተርም ሆነ በሕገ-መንግሥቱ በተፈቀደው መሠረትም፣ በድህረ-1983ቱ የፖለቲካ ዑደት ብሔር-ተኮርና አገር-አቀፍ የፖለቲካ ቡድኖች በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማያውቅ ዓይነትና መጠን ተፈጥረዋል። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ ከእነዚህ መካከል ብሔር-ተኮር ስብስቦች አብዛኛውን እጅ ሲይዙ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ሀገር-አቀፍ ቡድኖችም መፈጠራቸው አልቀረም። ለማስታወስ ያህልም፣ በ1983 የሽግግር መንግስቱን ለማቋቋም በኢህአዴግ በተጠራው ጉባዔ ላይ በርካታ ብሔር-ተኮርና ሀገር-አቀፍ ነን ብለው የታደሙ ቡድኖች ሲጋበዙ፣ ኢህአፓና መኢሶንን የመሳሰሉ ድርጅቶች እንዳይሳተፉ የተከለከሉበት ሁኔታ ነበር። ስለዚህም ብዙ ተስፋ የተጣለበት የሽግግር ሂደት ገና ከመነሻው የአግላይነትን ባህርይ ተላብሶ ተጀመረ። በማስከተልም ይህ የመገለል ዕጣ-ፈንታ በርካቶች በጉባዔው ላይ የተካፈሉትና ሌሎችም በየተራ እንዲደርሳቸው ሆኗል።

የ1983ቱን የመንግሥት ለውጥ ተከትሎ ሕጋዊ እውቅና አግኝተው በኢህአዴግ ቡራኬ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የገቡና በሽግግሩ መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫ የተሰጣቸው በርካቶች ሲሆኑ፣ ከእነዚህም መካከል፡-

1ኛ) አራቱ የገዥው ግንባር አባል ድርጅቶች፣
2ኛ) የኦሮሞ ነፃነት ግንባር፣
3ኛ) የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር፣
4ኛ) ሲዳማ አርነት ንቅናቄ፣
5ኛ) የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ሕብረት፣

6ኛ) የተወሰኑ የደቡብ ሕብረት አባል ድርጅቶች፣
7ኛ) የኢህአዴግ አጋር ተብለው የሚጠሩት ከቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ ጋምቤላ፣ አፋር፣ ሶማሌና ሀረሪ የተውጣጡ ቡድኖች፣
8ኛ) ኢህአዴግ ያደራጀው የነፃ መኮንኖች ንቅናቄና የመሳሰሉት ይካተታሉ

የሽግግር መንግሥቱ መሠረት የሆነው የተወካዮች ምክር ቤትም በአጠቃላይ 87 መቀመጫዎች የነበሩት ሲሆን ከዚህ ውስጥ የአንበሣውን ድርሻ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተቆጣጠረው ገዥው የኢህአዴግ ግንባር ነበር። ከቀሪዎቹ መካከል፣ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ከፍተኛ የሆነውን አሥራ ሁለት መቀመጫዎች ሲያገኝ፤ ሌሎቹ መስፈርቱ ባልታወቀ ድልድል አንድ ወይም ሁለት ወንበር እየተሰጣቸው በሽግግር መንግሥቱ ውስጥ ትርጉም-አልባ ተሳትፎ እያደረጉ ለተወሰኑ ጊዜ ቆይተዋል።

ከላይ በተጠቀሰው ወቅትም ሆነ በተከተሉት ጊዜያት ወታደራዊውን አስተዳደር በትጥቅ ትግል ያስወገደው ኢህአዴግ በድህረ-1983ቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ስርዓት የተጫወተው ሚናና የያዘው ድርሻ ከሌሎቹ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ከፍተኛ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በተለይ የ1984 አካባቢያዊ ምርጫን አስመልክቶ በተነሣው ውዝግብ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር በሽግግር መንግስቱ ውስጥ የነበረውን ተሳትፎ ማቋረጡ ሌሎችም ይህንን ፈለግ በተለያዩ ጊዜያት መከተላቸው ኢህአዴግ የፖለቲካ ምህዳሩን ይበልጥ በገዘፈ ሁኔታ ተቆጣጥሮ ሁሉ-ገብ ተፅዕኖውን እንዲያሳድር አስችሏል። በመቀጠልም የሽግግር ሥርዓቱ አባላት የነበሩት እንደ ኦሮሞ ነፃነት ግንባርና የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባርን የመሳሰሉት በህጋዊ ማዕቀፍ ውስጥ የነበራቸውን ህልውና በማክሰም እንደገና ወደ ትጥቅ ትግል የተመለሱበትና በዚህም ሳቢያ በሽብርተኝነት የተፈረጁበት ሁኔታ ተከናውኗል።

ቀደም ሲል የተነገረውና በኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች ህልውና ላይ አደጋ የጋረጠው አሉታዊ አዝማሚያ በየጊዜው ይበልጥ እየተጠናከረ በመምጣት በሀገሪቱ ውስጥ ይረጋገጣል ተብሎ የተጠበቀውን ጤናማ የፓርቲ ፖለቲካ ምህዳርን በከፍተኛ ደረጃ ማቀጨጭ ችሏል። በተለይም የ1997ቱን ብሔራዊ ምርጫ ተከትሎ የደረሰው ቀውስና በዚህም የተነሣ በኢህአዴግ የሚመራው መንግሥት የደነገጋቸው ከልካይና አፋኝ ሕጎች ተፅዕኖ የፖለቲካ ሥርዓቱ በአንድ ጠቅላይና ጨፍላቂ ፓርቲ የሚመራ እስኪመስል ድረስ ጉዳት እያስከተለ ቀጥሏል። ይህ ሁኔታም ያለምንም ከልካይ በህብረተሰቡ በአጠቃላይና በፖለቲካ ተዋናዮች ህልውና ላይ በተለይ የቀቢፀ-ተስፋ ድባብን በስፋት ዘርግቷል። ከሞላ ጎደል፣ ከገዥው ግንባር ማዕቀፍ ውጭ ያሉት የፖለቲካ ቡድኖች እንቅስቃሴና ተሳትፎ በተጠቀሰው ምክንያት ተገድቦ የፖለቲካና የአስተዳደር አመራር ለውጥ እስከተከናወነበት 2010

ድረስ ትርጉም ያለው ተጽእኖ መፍጠር በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ እየዳከሩ እንዲቆዩ አስገድዷል። ካለፈው አንድ ዓመት ወዲህ ግን፣ በተከናወኑት ዘርፈ-ብዙ የለውጥና የፖሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎች የተነሣ በሀገሪቱ የፓርቲ ፖለቲካ ሕይወት እንደገና እንዲያንሰራራ የሚያስችሉ በርካታ ምልክቶች እየታዩ ነው። የበርካታ ከልካይና አፋኝ ህጎች መሻሻልና መከለስ፣ የምርጫ ቦርድ በፓርቲዎች ተሳትፎ ጭምር እንደገና መዋቀር፣የታገዱ ድርጅቶች እውቅና ማግኘትና የበርካታ አዳዲስ የፖለቲካ ስብስቦች መፈጠርና ወደ ሥራ መግባት ለዚህ እንደመገለጫ ይጠቀሳሉ። አሁን እንደምንረዳው፣ በሀገሪቱ ህጋዊ እውቅና ያገኙ ፓርቲዎች ቁጥር ከመቶ በላይ ደርሷል። ዳሩ ግን ፓርቲዎች በተመሣሣይ መለስተኛ የድርጊት ፕሮግራሞቻቸው ዙሪያ በስፋት እየተቀራረቡ አለመሰባሰባቸውና የጋራ ቅርጽ መያዝ አለመቻላቸው በመጪው ምርጫም ሆነ በሚቀጥሉት ጊዜያት ዘርፈ ብዙ ውስንነቶችን በማጎልበት በርካታ ተግዳሮቶችን እየጋረጡ መሄዳቸው የማይቀር ነው።

## ምርጫና የህዝብ ውክልና በኢትዮጵያ

ምርጫና የህዝብ ውክልናን የሚመለከቱ ጉዳዮችና ታሪካዊና ነባራዊ መገለጫዎቻቸውና አደረጃጀታቸው በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስሉ በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር እንመለከታለን። ለአቀራረብ ያመች ዘንድም ፣ በርዕሱ የተጠቀሱትን ጉዳዮች በሶስት ዋና ዋና ዘመናት በመከፋፈል ለመዳሰስ ተሞክሯል። እነዚህም በንጉሣዊው፣ በወታደራዊና በኢህአዴግ የሥልጣን ዘመኖች አንፃር ከፋፍለን እንመለከታለን።

## ምርጫና የህዝብ ውክልና በዘውድ አገዛዝ ወቅት

አሁን በምንረዳው አግባብ፣ ዘመናዊ የምርጫና የህዝብ ውክልና አተገባበር በኢትዮጵያ የተጀመረው በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ነው። ንጉሡ ከፍተኛውን የመንግስት ስልጣን በ1923 ከተቆጣጠሩ በኋላ በተከታታይ ከወሰዷቸው እርምጃዎች መካከል ስርዓቱ የሚመራበትን ሕገ-መንግስትት ማርቀቅና ማጽደቅ እንዲሁም በራሳቸውና በሹማምንቶች አማካይነት የተመረጡ አማካሪዎችን ከመሣፍንት፣ መኳንንትና ባላባቶች የተውጣጣ ምክር ቤት ማቋቋም እንደቻሉ መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ እርምጃዎች ዘመናዊ የመንግሥት ሥርዓት ዝርጋታ ጅማሮ መሆናቸውን መቀበል ቢቻልም ተአማኒና ትክክለኛ የህዝብ ውክልና መገለጫዎች ነበሩ ብሎ ለመናገር አያስደፍርም። ምክንያቱም በክንውኖቹ ተግባራዊነት ላይ ይህ ነው ተብሎ የሚጠቀስ የዜጎች ተሳትፎና ሚና በማንኛውም

መለኪያ ስላልነበረ ነው፡፡ ይልቁንም ለእርምጃዎቹ እንደመንስኤ የሚወሰዱት ንጉሡ የተማከለ ሥልጣንን ለማጠናከር የነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎትና በውጭው ዓለም የዘመናዊነት መገለጫ የሚሆነውን የግለሰብ ተክለሰውነት ለመገንባት የተደረጉ ጥረቶች ውጤት ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ ከጥቂት ዓመታት በኋላ የእነዚህን ጅማሮዎች ቀጣይነት ያስተጓጎለው የጣሊያን ወረራ በመከሰቱ የንጉሡን መሰደድና የሉዓላዊ መንግስታቸውን መፍረስ አስከትሏል፡፡ ይህ ወረራ በ1933 ከተወገደ በኋላም ጦርነቱ ያስተከተለውን ምስቅልቅል ማቃናትና ህብረተሰቡን ማረጋጋት እንዲሁም የአስተዳደር መዋቅሮችን በአዲስ መልክ ማደራጀትና ማደላደል ዋነኛ ትኩረት ስለተሰጣቸው በምርጫና ህዝባዊ ውክልና ሥራዎች ላይ ለማተኮር ሁኔታዎች አልፈቀዱም፡፡

በ1933 የሀገሪቱ ነፃነት እንደገና መረጋገጥና የንጉሡን ከስደት መመለስ ተክትሎ ለአሥራ አምስት ዓመታት ያህል የህገ-መንግስት ማሻሻያም ሆነ ምርጫና የህዝብ ተወካይነትን የሚመለከት ስርዓት ለማዋቀር እምብዛም ጥረት ሳይደረግ ቆይቷል፡፡ በእነዚህ ዓመታት ውስጥም በሀገር ውስጥና በውጭ በርካታ ለውጦች መምጣታቸውን ተከትሎ በዚህ ረገድ አንዳንድ እርምጃዎችን የመውሰድ ጉዳይ አስፈላጊ አደርጎታል፡፡ የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ መሠረተ ልማቶች መስፋፋት፣ በዓለማቀፍ ደረጃ የተከናወኑ የኃይል አሰላለፍ ለውጦች፣ የኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀልና የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ፡፡ እነዚህና መሰል ክስተቶችና አዳዲስ ሁነቶች የ1948ቱን የተሻሻለ ህገመንግሥት ለማወጅ እንደ መነሻ ምክንያቶች ሊቆጠሩ የሚችሉ መሆናቸውን በመስኩ ተመራማሪዎች ዘንድ ስምምነት ተፈጥሯል፡፡

የ1948ቱን የተሻሻለ ሕገ-መንግሥት የማርቀቅና የማፅደቅ ሂደት ከአምስት ዓመታት የበለጠ ጊዜ በመውሰድ በንጉሠ ነገሥቱ 25ኛ ዓመት የዘውድ ኢዮቤልዩ በጥቅምት 23 ቀን 1948 ታወጀ ፡፡ ይህም የንጉሡን በላይነትና የባለሙሉ ሥልጣን ባለቤትነት በማረጋገጥና ቀድሞ በነበረው ላይ አስፈላጊ ናቸው ተብሎ የታመነባቸውን አንዳንድ ማሻሻያዎች በመጨመር የተጠናቀቀ ነበር፡፡ በዚህ መሠረትም ሕገ-መንግስትቱ የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች በማካተት ሥራ ላይ ለማዋል ተሞክሯል፡፡ እነዚህም፣

ሀ) ንጉሠ ነገሥቱ በህግ ማውጣት፣ ማስፈፀምና መተርጎም ረገድ የማይገሰስ ሙሉ ሥልጣን ባለቤት መሆናቸው፣
ለ) በሁለት ዘርፍ የተዋቀረ ማለትም ህግ መምሪያና የህግ መወሰኛ ምክር ቤቶችን ያካተተ ፓርላማ መቋቋሙ፣
ሐ) የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባላት ሕግ በሚፈቅድላቸው ዜጎች ቀጥተኛ ምርጫ የሚመረጡበት አግባብ ማካተቱ፣

መ) የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት ከመሣፍንቱ፣ መኳንንቱና ለሀገራቸው በቂ አገልግሎት በመስጠት ከሚታወቁ ግለሰቦች መካከል በቀጥታ በንጉሠ ነገሥቱ የሚሰየሙ መሆናቸው፣

ሠ) የጽሑፍ፣ የንግግር ፣ የመሰብሰብና የሰአብአዊ መብቶች ጥበቃ በሕግ መታወቁ፣

ረ) ለሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባልነት የሚወዳደሩ እጩዎች የመሬትና የሌላ ንብረት ባለቤት መሆናቸው መረጋገጥ የሚኖርበት መሆኑንና የመሳሰሉትን ያካትታሉ።

ምንም እንኳን ሕገ-መንግሥቱ አካለ መጠን ለደረሱ ዜጎች እንደራሴዎችን የመምረጥ መብት ቢያጎናጽፍም፣ በእጩነት ለመወዳደር የመሬትና የሌላ ንብረት ባለቤትነትን እንደ ቅድመ-ሁኔታ ማስቀመጡ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ይህንን መስፈርት ባለመሟላታቸው ከሂደቱ እንዲገለሉ ያደረገ ነበር። በዚህም የተነሣ የምርጫ ፖለቲካ የተወሰኑ ባለንብረት ልሂቃን ጉዳይ በመሆን እንዲወሰንና አብዛኞቹ የሀገሪቱ ዜጎች ሚና ከቀረቡት እጩዎች መካከል በመምረጥ እንዲገደብ የተደረገበትን ሁኔታ በመፍጠር ተጠናቀቀ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ የተደረጉ አንዳንድ ማሻሻያዎችም የብዙኃኑን ከምርጫ ውድድር የመገለል እውነታ ለመለወጥ ምንም አስተዋጽኦ አላደረጉም። የ1966ቱን ህዝባዊ መነሣሣት ተከትሎ የህገ-መንግስት ማሻሻያ ለማድረግ አንዳንድ ጥረቶች የተጀመሩ ቢሆንም እያደገ የመጣው የአብዮታዊ ለውጥ ግፊት ይህ ጅማሮ ከግብ ሳይደርስ የንጉሣዊው የፖለቲካ ሥርዓት እንዲወገድና በወታደራዊ አስተዳደር እንዲተካ በማድረግ ተጠናቋል።

የተሻሻለውን ሕገ-መንግሥት መጽደቅ ተከትሎ የተካሄዱት አራት ምርጫዎች በተደነገገው መሠረት የተካሄዱ ቢሆንም በትክክለኛ ይዘቱና ትርጉሙ የህዝብ ውክልናን ያረጋገጡ ነበሩ ብሎ መናገር አያስደፍርም። ምክንያቱም የፓርላማው ሁለት ምክር ቤቶች የተውጣጡት ሙሉ በሙሉ በሚል ደረጃ ንጉሣዊውን የፖለቲካ ሥርዓት በሚደግፉና የባለንብረቶችን ጥቅም ለማስከበር በተመረጡና በተሰየሙ አባላት ስለሆነ ነው። ከእነዚህ መካከልም እጅግ ጥቂት ግለሰቦች አንዳንድ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ተሻሽለው እንዲለወጡ ፍላጎት ቢኖራቸውም የብዙኃኑን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞች የሚያስጠብቁ እርምጃዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ የተጫወቱት ሚና እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ተመራጮች ምንም እንኳ የሕዝብ እንደራሴ የሚል ስያሜ ይዘው ወደ ምክር ቤት ቢገቡም፣ አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ድምጽ የሰጣቸው ከቀረቡለት ተወዳዳሪዎች መካከል ብቻ መምረጥ በመገደዱ ነበር።

## ምርጫና የህዝብ ውክልና በወታደራዊ አስተዳደር ዘመን፤

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በየካቲት 1966 የተቀጣጠለው ህዝባዊ እንቅስቃሴ ንጉሣዊውን የፖለቲካ ሥርዓት በማስወገድ በወታደራዊው ደርግ ለተመራውና በወቅቱ ጊዜያዊ በተባለው አስተዳደር እንዲተካ ሁኔታዎችን አመቻቸ።

ደርጉ መንግሥታዊ ስልጣንን ከተቆጣጠረበት ከመስከረም 1967 ቀጥሎ ባሉት ዓመታት የ1948ቱን ሕገ-መንግሥት በማገድና ምክር ቤቱን በመበተን በአዋጆችና በተለያዩ ድንጋጌዎች ላይ ተመርኩዞ ሀገሪቱን መምራት ቀጠለ። በመቀጠልም የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ የተባለውን ብቸኛ ሕጋዊ ድርጅት በመመሥረትና የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት የተባለ ተቋም አዋቅሮ አዲስ ሕገ-መንግሥት የማርቀቅ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ጀመረ። በዚህ መልክ የተጀመረው ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላም በ1980 ላይ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት የተሰኘውን ሰነድ አጽድቆ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ሥራ ላይ ለማዋል ሞክሯል። ይህንን ሕገ-መንግሥት ለማጽደቅም በርካታ ሚሊዮን ዜጎች የተሳተፉበትን ሕዝበ ውሳኔ አካሄዶ ሰማንያ በመቶ የሚሆን ድጋፍ ማግኘቱን ማስታወቁም ይታወሳል። በማንኛውም መልኩ ሕገ-መንግሥቱን የማርቀቅ የማጽደቅና ሕዝበ ውሣኔ የማካሄድ ሂደቱ ተጀምሮ የተጠናቀቀው ገዥው ፓርቲና ለመክሰም እየተቃረበ በመጣው በወታደራዊ ደርጉ ፍላጎት ዙሪያ መሆኑን መናገር ይቻላል።

የኢህዲሪ ሕገ-መንግሥት በተለያዩ አንቀጾች ሥር ያካተታቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል።-

1ኛ) የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ የአጠቃላይ ፖለቲካ ሥርዓቱ ዋና መሪና ተዋናይ መሆኑ፣
2ኛ) ሦስቱ ዋና ዋና የመንግሥት ተቋማት የሚመሩበትን አካሄድ መሪው ፓርቲ የሚቀይስና ተግባራዊ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል የተማከለ ሥልጣን እንደሚኖረው፣
3ኛ) የተማከለ መንግሥታዊ ሥልጣን በብሔራዊው ሸንጎ፣ በመንግሥት ምክር ቤት፣ በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንትና በአካባቢያዊና ራስ -ገዝ ሸንጎዎች መካከል እንደሚከፋፈል፣
4ኛ) የብሔራዊና የአካባቢያዊ/ራስ-ገዝ ሸንጎዎች አባላት በሕግ በተደነገገ መሠረት በሰርቶ አደሩ ሕዝብ እንዲመረጡ፣
5ኛ) ብሔራዊው ሸንጎ የመጨረሻው የመንግሥት ሥልጣን አካል መሆኑ እንደተጠበቀ የመንግሥት ምክር ቤትን፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤትና የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን፣ ኮሚሽኖችና ባለስልጣን ተቋማትን እንዲሁም የጠቅላይ ፍርድ ቤትን የጠቅላይ ዐቃቤ ህግና ኦዲት መሥሪያ ቤቶችንና የሠራተኞች ብሔራዊ ቁጥጥር ኮሚቴን እንደሚያዋቅር፣

6ኛ) የሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የሀገሪቱ ርዕሰ-ብሔር ፣የመንግስት ምክር ቤትና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ሆኖ እንደሚሠራ፣
7ኛ) ዜጎች በሙሉ በህግ ፊት እኩልና በዚህም መሠረት በሀገሪቱ የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳትፏቸው እንደሚረጋገጥ፣
8ኛ) መንግሥትና ኃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውና አንዱ በሌላው ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንደሌለባቸው ወ.ዘ.ተ እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

የኢህዲሪ ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ በቆየበት አጭር ጊዜ አንድ የብሔራዊና የአካባቢያዊ/ራስ-ገዝ ሸንጎዎች ምርጫ የተካሄደ ቢሆንም እጩዎች በገዥው ፓርቲ ለውድድር ተመርጠው የተሰየሙበት አካሄድ ተግባራዊ ስለሆነ በማንኛውም መመዘኛ የህዝብ ውክልና መስፈርትን ያሟላ ነበር ብሎ መናገር አይቻልም። ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በደርጉ የተመራው የፖለቲካ ሥርዓት ላይ በየአቅጣጫው የተነሣው ተቃውሞ እየተፋፋመ በመሄድ በግንቦት 1983 ለአሥራ ሰባት ዓመት የቆየው ዘመነ ሥልጣን አክትሞ በኢህአዴግ በሚመራው አዲስ ሥርዓት ለመተካት በቃ።

## ምርጫና የህዝብ ውክልና በኢህአዴግ-መር የፖለቲካ ሥርዓት

በደርግና በኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ቁጥጥርና በላይነት ሥር የነበረው የፖለቲካ ሥርዓት በኢህአዴግ በተመሩት ኃይሎች የጦር ግፊት በግንቦት 1983 ከሥልጣን መወገዱን ተከትሎ ሀገሪቱና ህብረተሰብ የሚመሩበት አዲስ አቅጣጫ ተቀይሶ ሥራ ላይ መዋል ጀምሮ በዚሁ ዓመት በሐምሌ ወር ኢህአዴግ በዋናነት የጠራው የሰላምና የዲሞክራሲ ጉባዔ በመሪው ግንባር ተመርጠው የተሳተፉትን የፖለቲካ ቡድኖች በማካተት የሽግግር ወቅት ቻርተር በማጽደቅና የሽግግር መንግሥት በማቋቋም ተጠናቀቀ። በዚህ ጉባዔ ላይ የታደሙት ቡድኖች ከፊሎቹ ወታደራዊውን መንግሥት ለማስወገድ በትጥቅ ትግል ሲሳተፉና በብሔር-ተኮር የፖለቲካ ፕሮግራም ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሲሆኑ ቀሪዎቹ በአብዛኛው የደርግን መውደቅ ተከትሎ በችኮላና በተለያዩ መስፈርቶች የተሰባሰቡና ቀደም ሲል እምብዛም እውቅና ያልነበራቸው አዳዲስ ድርጅቶችን የመሠረቱ ኃይሎች መሆናቸው በስፋት ይታወቃል። በመሆኑም ጉባዔው አሸናፊው ግንባር ከአካሄዱ ጋር የሚስማሙት ቡድኖች እውቅና እንዲሰጡትና ለጊዜው ስምምነታቸውን እንዲገልጹለት የጠራው የመተማመኛ መድረክ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል። ለዚህም ቀደም ሲል ተመሥርተው በየፊናቸው ተከታዮችን ያፈሩና በደርጉም ሆነ በኢህአዴግ የርዕዮተ ዓለምና የድርጊት መርሐግብር ላይ የተቃውሞ አቋም የያዙት

ሀገር-አቀፍ የፖለቲካ ኃይሎች ሆን ተብሎ የተገለሉበት መሆኑ እንደ ማሳያ ይጠቀሳል።

የሽግግር መንግሥት ተብሎ በቻርተሩ ላይ ተመስርቶ የተፈጠረው ተቋም በተለይ ሁለት ዋና ዋና አካላትን ተመርኩዞ በጉባዔው ተሳታፊዎች ይሁንታ ለመቋቋም በቃ። እነዚህም የሥራ አስፈጻሚው አካልና የተወካዮች ምክር ቤት ተብለው ይታወቃሉ። በሁሉም መመዘኛ አሸናፊው የኢህአዴግ ድርጅት በእነዚህ ውስጥ ትልቁንና ወሣኙን ድርሻ ለመያዛቸው ማረጋገጫ የሚሆኑ ነጥቦችን እንደሚከተለው መግለጽ ይገባል። ከእነዚህም መካከል፤

1ኛ) በሥራ አስፈጻሚው ውስጥ ወሣኝ የሆኑ ማዕከላዊ የኃላፊነት ቦታዎች ማለትም፣ የሽግግር መንግሥቱ ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የሀገር ውስጥ፣ የውጭ ጉዳይና የመከላከያ ሚኒስትሮች ሥራዎች በኢህአዴግ መሪ አባላት ቁጥጥር ሥር መዋላቸው፣

2ኛ) የኢህአዴግ የጦር ኃይል የሽግግር መንግሥቱ ሠራዊት ሆኖ መሰየሙ፣

3ኛ) የተወካዮች ምክር ቤት በግንባሩ ሊቀመንበር እየተመራ ኢህአዴግ ከ87 መቀመጫዎች ውስጥ 32ቱን መያዙና የግንባሩ ተባባሪዎች በተለያየ ስም ከቀሪዎቹ ውስጥ በርካታ ወንበሮችን እንዲይዙ መደረጉ፣

4ኛ) በተለያዩ የሀገሪቱ ዋና ዋና ክልሎች ውስጥ አንዳንድ የግንባሩ መሪ አባላት በበላይነት ሁኔታዎችን እንዲቆጣጠሩ መሠማራታቸውን መጥቀስ ይቻላል።

በ1984 በወጣ አዋጅ ብሔራዊ ክልላዊ ራስ-ገዝ መስተዳድሮች መቋቋማቸው ተከትሎ በዚሁ ዓመት የድህረ- ደርግ የመጀመሪያው አካባቢያዊ ምርጫ ተካሄደ። በይፋ እንደተነገረው ይህንን ምርጫ የማካሄድ እርምጃ የተወሰደው በመቋቋም ላይ የነበሩትን ክልላዊና የወረዳ መስተዳደሮችን በዴሞክራሲያዊ አግባብ እንደገና ለማዋቀር ታስቦ ነው። ይህ ምርጫ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ተቀባይነትና ተአማኒነት እንዲያገኝ በሚል ዕሳቤ ቁጥራቸው 250 ያህል የሆነ ዓለማቀፍ ታዛቢዎች የተጋበዙ ቢሆንም፣ በርካታ ታዛቢዎች ይህ ክንውን የተለያዩ አማራጮችን በማቅረብና በማመቻቸት አልተካሄደም የሚል ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ሁኔታዎች አስገድደዋል። በምክንያትነት ከተጠቀሱት ውስጥም፣ ኢህአዴግ ያለማመንታት ለድርድርና ለሠፊ ተሳትፎ ዕድል ከመንፈጉም በላይ መንግስታዊ ሥልጣኑን በመጠቀም ሌሎች ተፎካካሪዎችና ደጋፊዎቻቸውን የማስፈራራት፣ የማሠርና የማንገላታት እርምጃዎችን በስፋት በመውሰድ

አሸናፊነቱንና በላይነቱን ለማረጋገጥ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረጉ ተወስቷል። በመጨረሻም ኢህአዴግና የቅርብ ተባባሪዎቹ ሙሉ-በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ የ1984ቱን ምርጫ ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ማሸነፋቸውን በማስታወቅ ሌሎች ተወዳዳሪዎችን ከጨዋታው ሜዳ በማሰናበቱ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን በሀገሪቱ የማስፈን ተስፋ ገና ከጅምሩ እንዲጨናገፍ አድርጓል። ይህንን ተከትሎም የኦሮሞ ነፃነት ግንባር፣ የመላ አማራ ህዝብ ድርጅትና የኦሮሚያ ነፃነት እስላማዊ ግንባርን የመሳሰሉ የሽግግር ምክር ቤቱ አባላት ከአጠቃላይ ሂደቱ ራሳቸውን ለማግለል ተገደዋል። ስለዚህም ይህ ምርጫ በማንኛውም መለኪያ ተአማኒነት ያለው የህዝብ ውክልናን ማረጋገጥ አልቻለም።

የ1984ቱን ምርጫ ተከትለው በመጡት ቀጣይ ሁለት ዓመታት ኢህአዴግ ያገኘውን የበላይነት ለማጠናከርና መጪውን ሕገ-መንግሥት የማርቀቅ ቅድመ ዝግጅት ለራሱ በሚያመቸው መንገድ በማጠናቀቅ ሥራ ላይ ተጠምዶ ቆየ። ይህንን በሚመለከት ግንባሩ ያጋጠመው ተግዳሮት ቢኖር በሀገር ውስጥና በውጭ የሚንቀሳቀሱ ሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ትችት፣ የተፎካካሪ ፖለቲካ ቡድኖች ተቃውሞና አልፎ አልፎ በያዝ-ለቀቅ የሚደረግ የተወሰኑ የዓለምአቀፍ ህብረተሰብ ክፍሎች የተለሳለሰ ተግሣጽ ብቻ ነበር። የእነዚህ ድምር ውጤትም ኢህአዴግ በሁሉም መስክ የሚያደርገውን በላይነት የመጎናፀፍ ጥረትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሊገታውም ሆነ ሊያለዝበው አልቻለም። በመሆኑም ይህ ሂደት ያለብዙ ችግር ቀጥሎ የህገ- መንግሥት አጽዳቂ ጉባዔ አባላት ምርጫ በ1986 ተከናወነ። በእውቅ የተመለመሉ 500 ያህል የዚህ ጉባዔ አባላትም በዚሁ ዓመት ተደጋጋሚ ስብሰባ በማድረግ በግንባሩ የበላይ አስተባባሪነት የተረቀቀው ሕገ መንግሥት ይህ ነው ሊባል የማይችል ማሻሻያ ሳይደረግበት እጅግ ከፍተኛ በሆነ አብላጫ ድምጽ አፀደቁ። እንደ ብዙዎች ምልከታ በጉባዔው የፀደቀውና ቀጥሎም ሥራ ላይ የዋለው የ1987 ሕገ-መንግሥት በአብዛኛው የኢህአዴግ ፕሮግራም ነፀብራቅ እንደሆነ ይታመናል። የሕገ-መንግሥት ጉባዔው አባላት ምርጫም ከላይ በተነሱት ምክንያቶች ትክክለኛ የህዝብ ውክልና ገጽታን የተላበሰ አልነበረም።

በፀደቀው ሕገ-መንግሥት አግባብ የመጀመሪያ የድህረ-ሽግግር ወቅት የመጀመሪያው ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ በግንቦት 1987 ተካሄደ። ቀደም ሲል በተቀናጀ ሁኔታ የመሪውን ግንባር የበላይነት ለማረጋገጥ በተደረገው ጥረት በርካታ ተፎካካሪ ድርጅቶች በሰበብ አስባቡ ባለመሣተፋቸውና ከሂደቱ በመገላለቸው የውድድሩ ውጤት ኢህአዴግና ተባባሪዎቹ ከዘጠና አምስት በመቶ በላይ የፌዴራልና የክልል ምክርቤቶችን መቀመጫ ማሸነፋቸው ተነግሮ ጉዳዩ በዚህ

ተጠናቀቀ። በዚህም ግንባሩና ተባባሪዎቹ በየደረጃቸው መንግሥት የማቋቋም ህገ-መንግሥታዊ እውቅና አግኝተው ይህንኑ ተግባራዊ የሚያደርጉበት ሁኔታ ተፈጠረ።

ከዚህ በመቀጠልም በተከታታይ አራት ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫዎች በ1992፣ በ1997፣ በ2002 እና በ2007 ተካሂደዋል። በ1992 ተፎካካሪ ፓርቲዎች ከቀድሞ በተሻለ ሁኔታ የፌዴራልና የክልል ምክር ቤቶች መቀመጫዎች ማግኘት የቻሉበት ሁኔታ ቢፈጠርም፣ አሁንም ኢህአዴግ በአጠቃላይ ውጤቱ ጉልህ አሸናፊ በመሆን የመንግሥት ሥልጣንን በሁሉም ደረጃ መቆጣጠሩን አረጋግጧል። ይህም በብሔራዊው ምርጫ ቦርድም ሆነ ክርክርና ተቃውሞ በቀረበባቸው ፍርድ ቤቶች እውቅና አግኝቷል። በስፋት እንደሚታመነው፣ እነዚህ ሁለት ተቋማት አደረጃጀታቸው የሰው ኃይል ምልመላና ስምሪታቸው እንዲሁም አጠቃላይ የአሠራር ዝንባሌያቸው መሪውን ግንባር ኢህአዴግን ያለምንም ጥያቄና ይሉኝታ በአብዛኛው ወደ መደገፍ ያዘነበለ ነበር። ስለዚህም፣ በሥራ ላይ ያሉትን የሀገሪቱን ሕጎች ብቻ በመከተል ሕዝባዊ ውክልና የሚረጋገጥበትን ቁመና የማራመድ ፍላጎትና ችሎታ ነበራቸው ብሎ መናገር ያዳግታል።

ከአምስት ዓመታት በኋላ በግንቦት 1997 የተካሄደው ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ ቀደም ሲል ከተደረጉትም ሆነ በኋላ ከተከናወኑት የምርጫ ሁነቶች የሚለይበት በርካታ ገጽታዎች ነበሩት። ከእነዚህም መካከል የምርጫ ምህዳሩ ባልተለመደ ሁኔታ እየሰፋ መሄዱን የሚያመለክቱ መገለጫዎች በብዛት መታየታቸው በርካታ የፓርቲና የግል ተወዳዳሪዎች ያለብዙ ችግር በሂደቱ መሳተፋቸውና የምርጫ ክርክርና ቅስቀሳ ማካሄድ መቻላቸው እንዲሁም ፕሮግራሞቻቸውን ለማስተዋወቅ የተሻለ የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን ማግኘታቸውን መጥቀስ ይቻላል። ይህ ሁኔታ በዚህ መልኩ እስከ ምርጫው እለት የቀጠለ ቢሆንም የምርጫውን መጠናቀቅ ተከትሎ በውጤቱ ላይ በተፈጠረው ውዝግብ የተነሣ መንግሥት የአደባባይ ስብሰባዎችና የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ለአንድ ወር የታገዱ መሆኑን በማሳወቅ የፀጥታ አስከባሪዎች እዝ በጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣን ሥር ሆኖ ለግዳጅ እንዲዘጋጁ የሚያደርግ ድንጋጌ አወጀ። በዚህ ምርጫ ቅንጅትና ሌሎች ተፎካካሪዎች አዲስ አበባን ጨምሮ በአንዳንድ ከተሞችና በገጠር አካባቢዎች ማሸነፋቸውን መንግሥትና የምርጫ ቦርድ አምነው በአጠቃላይ ሀገራዊ ውጤት ደረጃ ግን ኢህአዴግ የበላይነት መቀዳጀቱን ይፋ አደረጉ። የቅንጅትና የሌሎች ተፎካካሪ ቡድኖች አባላትና ደጋፊዎች የምርጫው ውጤት ተጭበርብሯል በሚል መጠነ ሠፊ የታቃውሞ እንቅስቃሴ በማድረጋቸው የህይወት መጥፋት፣ እስራትና የንብረት ውድመት ሊደርስ ችሏል። በመቀጠልም በመንግሥትና በተቃዋሚዎች

መካከል ስምምነት ለመፍጠር የተካሄዱ ድርድሮች ቅንጅት የተባለው ዋነኛ ተቃዋሚ ፓርላማ ላለመግባት በወሰደው አቋም በመጽናቱ ጥረቱ ፍሬያማ ሊሆን አልቻለም። መንግሥትም የቅንጅት መሪዎችን በሀገር ክህደትና ህገወጥነት በመፈረጅ በቁጥጥር ሥር አውሎ አዲስ አበባን ጨምሮ በሀገሪቱ በሙሉ መንግስት የመመስረቱን ሥራ ተግባራዊ ማድረግ ቻለ። ስለዚህም ህብረተሰቡ ለቅንጅት ተወዳዳሪዎች የሰጠው ሰፊ ድምጽና ውክልና ቢባክንም የሌላው ተቃዋሚ ቡድን የህብረት እጩዎች ያገኙትን የምክር ቤት መቀመጫዎች ተቀብለው በፌዴራልና ክልል ህግ-አውጭ አካላት ውስጥ ለአምስት ዓመታት ሲሳተፉ ቆይተዋል። የ1997ቱን የምርጫ ቀውስ ተከትሎም መንግሥት በወሰደው የኃይል እርምጃዎች በርካታ የሲቪል ማህበረሰብና የሚዲያ ተቋማትና ተዋንያን ሰለባ በመሆናቸው የምርጫና አጠቃላይ የፖለቲካ ምህዳሩ ተሸመደመደ። ይህም ቀጥለን እንደምናየው በሚቀጥሉት ሁለት ምርጫዎች ላይ ከፍተኛ አንድምታ አስከትሎ የኢህአዴግን ጠቅላይነት ያረጋገጠ ክስተት በመሆን ተጠናቋል።

በ2002 እና በ2007 የተካሄዱት ምርጫዎች ውጤት የኢህአዴግን ዘርፈ-ብዙ የፖለቲካ ሞኖፖል ባለቤትነት ማስከተላቸው ያልተጠበቀ ጉዳይ አልነበረም። እነዚህም ቀደም ሲል በተደጋጋሚ ባወሳናቸው ለነፃና ፍትሐዊ የብዙ ፓርቲዎች ውድድር እንቅፋት የሆኑ አስቸጋሪ ሁኔታዎች የተነሣ በሁለቱም የመጨረሻ ምርጫዎች ኢህአዴግና ተባባሪዎቹ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የፌዴራልና ክልል ምክርቤቶች መቀመጫዎችን በመቆጣጠር መንግሥትን የመምራት ሥልጣን አግኝተዋል። የኃይማኖት፣ የባህልና የብሔረሰብ ብዝኃነት ጎልቶ በሚታይበት ኢትዮጵያ አንድ የፖለቲካ አመለካከት የሚያራምድና ወጥ የሆነ ርዕዮተ ዓለማዊ አቅጣጫ የሚያቀነቅን ገዥ ግንባር በማንኛውም መመዘኛ የተሟላ የህዝብ ውክልና ባለቤት መሆን ይችላል ተብሎ ሊገመት አይችልም ።

## ፖለቲካ ፓርቲዎችና ቀጣይ ምርጫ

### መግቢያ

በደርግ የተመራው የፖለቲካ ሥርዓት ከተወገደና በኢህአዴግ ግንባር ቀደምነት አዲስ አካሄድ ተቀይሶ ተግባራዊ መሆን ከጀመረ ከ1983 ወዲህ በነበሩ በርካታ ዓመታት ተከታታይ ምርጫዎች መካሄዳቸውንና የህዝብ ውክልና ገጽታ ምን እንደሚመስል ለማሳየት ተሞክሯል። በዚህ ጽሑፍ እንደተጠቆመው፣ በመሪው ግንባር ያልተቆጠበ ሥልጣንን ለብቻ የመጠቅለል ፍላጎት የተነሣ በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ከፖለቲካ ሂደት የመገለልና ትክክለኛ ውክልና የማጣት ስሜት ሰፍኖባቸው የቆየ ለመሆኑ በርካታ ምልክቶች ሲስተዋሉ ቆይተዋል።

በተጨማሪም ለዓመታት በመላ ሀገሪቱ የተንሠራፋው ዘርፈ-ብዙ የአስተዳደር ብልሽትና በየጊዜው እያደገ የመጣው መጠነ-ሰፊ ሙስና፣የፍትህ እጦትና የስልጣን ብልግና አጠቃላይ ህዝቡን ወደ ተስፋ ቆራጭነት ገፍቶታል:: ይህም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በወጣቶች የተመራ ህዝባዊ አመጽ በማቀጣጠልና የመንግሥትን አቅም በመፈተን ለለውጥ የተዘጋጀ የአመራር ቡድን ሥልጣን እንዲቆጣጠር ሁኔታውን አመቻቸ::

ካለፈው አንድ ዓመት ለዘለለ ጊዜ ወደ ሥልጣን የመጣው አዲስ አመራር ህብረተሰቡን ለማረጋጋት ሰላምን ለማስፈንና ሀገሪቱን ወደ አዎንታዊ የለውጥ ጎዳና ለማስገባት ብዙ እርምጃዎችን ወስዷል:: በጥቅሉ፣ የፖለቲካ እሥረኞችን መፍታት፣ የምርጫ ቦርድ እንደገና በአዲስ መልክ ማዋቀር፤ አፋኝ ሕጎችን መከለስ፤ የፓርቲዎች ምዝገባና ተሳትፎ ሥርዓትን ማሻሻል፤ ለዜጎች ተሳትፎ የሚጠቅሙ መድረኮችን ማመቻቸትና በሕገወጥነት ተፈርጀው ለስደት የተዳረጉ የፖለቲካ ስብስቦች ወደ ሀገር ተመልሰው እንዲሠሩ ማስቻልን…ወዘተ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል:: እነዚህና የመሳሰሉት አዎንታዊ ሁነቶች በሰፊው የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ብሩህ ተስፋን መጫራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣በተቃራኒው ደግሞ ካለፈው አንድ ዓመት በላይ ባስቆጠረ ጊዜ የተለያዩ ወገኖች ግጭትና በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ከተለያየ ስፍራ ከየመኖሪያቸው የመፈናቀላቸው ጉዳይ ከፍተኛ የህልውና ስጋት እየፈጠረ መሄዱን ታዝበናል::

## ቀጣዩን ምርጫ በተመለከተ የግል ምልከታ

ቀጣዩ ምርጫ በግንቦት 2012 እንዲካሄድ ቀደም ሲል የተወሰነ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል:: ይህ ውሣኔ ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫዎች በየአምስት ዓመቱ እንደሚካሄዱና በምርጫው ውጤት ላይ ተመርኩዞ በፌዴራልና በክልል ደረጃ መስተዳድሮች ይቋቋማሉ ከሚለው ሕገመንግስታዊ ድንጋጌ ጋር የተጣጣመ መሆኑ ግልጽ ነው:: ዳሩ ግን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመላ ሀገሪቱ ዘርፈ-ብዙ የሆኑ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ የለውጥ ክስተቶች በተከታታይ በመድረሳቸውና የተለያዩ አንድምታዎች በማስከተላቸውና የየራሳቸውን በጎም ሆነ አፍራሽ ተጽእኖ እያሳደሩ በመምጣታቸው የቀጣዩ ምርጫ ጉዳይ በጥሞናና በሰከነ አእምሮ ሊጤን ይገባል ብዬ አስባለሁ::

**አንደኛ**፣ ቀደም ሲል እንደተወሳው አዲሱ የለውጥ አመራር ወደ ሥልጣን ከመጣ ወዲህ ሀገሪቱና ህብረተሰቡን ለማረጋጋትና ወደሚፈለገው የሽግግር ዑደት ለማስገባት የሚጠቅሙ በርካታ ጅማሮዎች መኖራቸውን እንገነዘባለን:: በተቃራኒው ደግሞ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ከግዴታ ጋር አጣጥሞ የመጠቀም

ልምድ እጥረት በአንድ በኩል እንዲሁም ሰፊ ግጭትና መፈናቀል የሰፈነበት የፖለቲካ ድባብና የለውጡ ተቃዋሚዎች አፍራሽ እንቅስቃሴ በሌላ በኩል በተረጋጋና ግልጽ አካሄድ የስምምነት አቅጣጫን በተከተለ መንገድ ተአማኒ፣ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ በታቀደለት ጊዜ የማካሄድን ጉዳይ አጠያያቂ ያደርገዋል፡፡ ለዚህም እንደ ዋና ምክንያትና መከራከሪያ ሊቀርብ የሚችለው አሁንም ግጭቶችና መፈናቀሎች እየቀጠሉ በመሆኑ አጠቃላይ ሰላምና መረጋጋት የሀገሪቱ ገላጭ ገጽታ የሚሆንበት ደረጃ ላይ ገና አልደረሰም፡፡

**ሁለተኛ**፤ ለውጡን ተከትሎ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ህጋዊ እውቅና ያገኙ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ቁጥር በፍጥነት ጨምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ 107 መድረሱ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ በችኮላ የተሰባሰቡ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በስደት ከሚኖሩባቸው ሀገሮች በይቅርታ ገብተው ለመደራጀት እየሞከሩ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ ነባርና በተለያዩ ከልካይ መንግሥታዊ ሕጎችና አሠራሮች ተፅዕኖ የተነሣ በመዳከማቸው አዲስ የተፈጠረውን አዎንታዊ ለውጥ ተጠቅመው ለማንሠራራትና ለቀጣዩ ምርጫ ለመዘጋጀት የሚያስችላቸውን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ጥረት እያደረጉ ቢሆንም የተረጋጋና ጠንካራ መደላደል ላይ ለመድረስ አሁንም በርካታ ሥራ ይጠብቃቸዋል፡፡

**ሦስተኛ**፤ የመሪው ግንባር አባል ድርጅቶች በለውጡ አካሄድና አተገባበር ላይ ያላቸውን ልዩነቶች የሚፈቱበት ደረጃ ላይ ገና ባለመድረሳቸው ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ የተረጋጋ ምርጫ በታቀደው ጊዜ ማካሄድ በተግዳሮት የተሞላ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

**አራተኛ**፤ አሁን እንደ አዲስ በመዋቀር ላይ የሚገኘው የምርጫ ቦርድ የአሠራር ስርዓት ለመዘርጋትና ወደ ሥራ በመግባት ቀጠዩን ምርጫ ለመምራት የሚያስችለው የተሟላ ሰው ኃይልና በቂ ፋይናንስ ስለሚያስፈልግ እነዚህን በአጭር ጊዜ ለማግኘት አዳጋች ይሆናል፡፡

**አምስተኛ**፤ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ተፈናቃይ ዜጎችን ወደ የመኖሪያቸው መልሶ የማቋቋም ጥረት በሂደት ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህንን አጠቃሎ ለመጨረስ ጊዜ የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህም ይህ ከመከናወኑ በፊት ምርጫን ማካሄድ እነዚህን ተፈናቃይ ዜጎች ውክልና እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡

**ስድስተኛ**፤ ቀደም ሲል ሊካሄድ የታሰበው የህዝብ ቆጠራ አመቺ የሆኑ የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው ለሚቀጥለው ዓመት እንዲተላለፍ የቀረበውን ምክረ-ሀሳብ መንግሥት ተቀብሎ በይፋ አስታውቋል፡፡ የህዝብ ቆጠራ

ባልተካሄደበት ሁኔታ ቀጣዩን ምርጫ ማካሄድ የመራጮችን ምዝገባ ስርዓት በህጉ መሠረት ለማካሄድና ሂደቱን ተአማኒ ለማድረግ አያስችልም፡፡

**ሰባተኛ፤** ምንም እንኳን ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ የምርጫ ድባብን ለማስፈን የሚያስችሉ አንዳንድ የህግ ማሻሻያዎች ቢጠናቀቁም ሌሎች አሁንም በሂደት ላይ ስለሚገኙ ሁሉም ተሟልተው እንዲጠናቀቁና የተረጋጉ አፈጻጸሞች እንዲመቻቹ ተጨማሪ ጊዜ ማስፈለጉ ግድ ነው፡፡

**ስምንተኛ፣** በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሚገኙ የፖለቲካ ስብስቦችና መሪ ተዋናዮች መካከል በድንበርና ማንነት ዙሪያ የተፈጠረው ውዝግብና እሰጥ-አገባ ለተረጋጋ ሰላም መስፈንና በትብብር ለመሥራት ከፍተኛ እንቅፋት አስከትሎ ቆይቷል፡፡ እነዚህን ተግዳሮቶች በአግባቡ ለመቅረፍና ከችግር የፀዳ የጋራ ትብብር የሚዘረጋበትን መደላደል ፈጥሮ የተጀመረውን የለውጥ ሽግግር የተሳካ ለማድረግም በቅርቡ የድንበርና ማንነት እንዲሁም የእርቀ-ሰላም ኮሚሽኖች ተመስርተዋል፡፡ ኮሚሽኖቹም ወደ ሥራ ለመግባት የሚያስችላቸውን ቅድመ ዝግጅት በመተግበር ላይ ሲሆኑ፤ ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንፃር ማጠናቀቅ የሚገባቸው ተግባራት ገና በጅምር ላይ ያሉና በቂ ጊዜ የሚጠይቁ ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ተመሣሣይ ምክንያቶች በጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻዎችና የህብረተሰብ ተወካዮች የሚታደሙበት መድረክ ተፈጥሮና ሠፊና በቂ ምክክር በማድረግና አጠቃላይ ስምምነት ላይ በመድረስ በግንቦት 12/2012 ሊካሄድ የታቀደው ቀጣይ ምርጫ የሚራዘምበትን የአፈጻጸም ፍኖተ-ካርታ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ግድ ይላል፡፡

የተዘረዘሩት ተግዳሮቶች ሳይወገዱና ሁኔታዎች ሳይስተካከሉ ገና ለገና ሕገ-መንግሥቱ ምርጫ በየአምስት ዓመት መካሄድ አለበት ይላል በሚል የተቸከለ ዕሳቤ ላይ በመንጠልጠል ወደ ምርጫ መግባት ከሚያስገኘው ጥቅም ይልቅ የሚያስከትለው ቀውስና ጠንቅ በእጅጉ እንደሚያመዝን ለመረዳት ነቢይ መሆንን አይጠይቅም፡፡ በእርግጥ ቀደም ሲል በአስቸጋሪ ሁኔታዎችና ሀገሪቱ ከኤርትራ ጋር ጦርነት በገባችበት ወቅት ጭምር ምርጫ ተካሂዷል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ግልጽና የማያሻማ ነው፡፡ ምክንያቱም እስካሁን በተደረጉት ሀገራዊና ክልላዊ ተከታታይ ምርጫዎች ማን እንደሚያሸንፍና ውጤቱም በምንም መንገድ ሊለወጥ እንደማይችል አስቀድሞ በመወሰኑ ነበር፡፡

## መደምደሚያ

በዚህ ጽሑፍ የተለያዩ ርዕሶች ሥር ለማብራራት እንደተሞከረው፣ ከንጉሣዊው የአገዛዝ ወቅት ጀምሮ እስከ 2007 በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱት ምርጫዎች

የዜጎችን ተገቢና አሳማኝ ፍላጎቶችን ማዕከል ያደረጉ አማራጮችን በማቅረብ የተከናወኑ ነበሩ ብሎ መደምደም አያስችልም። በንጉሡና በወታደራዊው አስተዳደር እንዲሁም በኢህአዴግ ዘመነ-ሥልጣን ምርጫን የማካሄድ ዓላማ ያተኮረው ለየሥርዓቶቹ የሕጋዊነት ሽፋን ለመስጠትና ቅቡልነትን ለማስገኘት የታለመ የይስሙላ አቀራረብና አስመሣይነትን የተላበሰ ክንውን ከመሆን አልዘለለም። ስለዚህም በማንኛውም መለኪያ ምርጫዎቹ የሕዝብን ትክክለኛ ተወካይነት ለማረጋገጥና በዚህም አማካይነት የዜጎችን ትክክለኛ ፍላጎት በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለማስተናገድ ተብለው መተግበራቸውን የሚያረጋግጥ በተግባር የተደገፈ ተጨባጭ ማስረጃ ሊቀርብላቸው አይችልም በስርዓቶቹ መካከል ሊጠቀስ የሚችል ልዩነት ቢኖር የፓርቲ ፖለቲካ በሀገሪቱ ውስጥ በመኖሩና ባለመኖሩ ብቻ የሚወሰን ነው።

በጽሑፉ እንደተጠቀሰው በንጉሡ ዘመን ሕጋዊነት ያገኘ አንድም ፖለቲካ ፓርቲ አልነበረም። በወታደራዊ አስተዳደር ወቅት በመጨረሻ ሕጋዊ እውቅና ያገኘ አንድ መሪ ድርጅት ብቻ የነበረ ሲሆን፣ በኢህአዴግ ዘመነ-ሥልጣን በርካታ ፓርቲዎች ተፈጥረው ወደ እንቅስቃሴ ገብተዋል። ዞሮ-ዞሮ የእነዚህን ሁሉ ድምር ውጤት ተመሣሣይ የሚያደርገው ምርጫና ፖለቲካ ሥልጣንን አማክለው በጨበጡ ኃይሎች ዙሪያ የተሽከረከሩ መሆኑ ነው። በተመሣሣይም፣ የህዝብ በፖለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ የመወከል ጉዳይ የዜጎችን ተገቢ ፍላጎቶች መሠረት አድርጎ የተቀየሰ ሳይሆን የየስርዓቶቹን ቁንጮዎች የሥልጣን ጥማትና ጥቅም በሚያራምድ መንገድ የተዋቀረ መሆኑን ነው። እነዚህ ጉዳዮች በጽሑፉ ውስጥ በበቂ ተነግረዋል ብዬ አስባለሁ። በ2012 ሊካሄድ የታሰበው ምርጫ ለምን መራዘም እንዳለበት የሚዘረዝሩ ምክንያቶችንና የመከራከሪያ ነጥቦችን በጽሑፉ ለማሳየት ሞክሬያለሁ። በእኔ ዕሳቤ እነዚህ ነጥቦች የተግዳሮቶች መገለጫ ስለሆኑና መንስኤዎችና መገለጫዎቻቸው መፍትሔ ሳያገኙ ባወጣ-ያውጣው በሚል ምርጫ ማካሄድ መጠነ-ሠፊ ቀውስን ከመጋበዝ በተጨማሪ ወደ ተለመደው ንትርክና ውዥንብር ከመግባት የዘለለ ፋይዳ ይኖረዋል የሚል ግምት እንደሌለኝ በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ። ስለዚህ ሁሉም ባለድርሻዎች የተጠቆሙትን ክፍተቶች ለመሙላት የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ በትጋት እስካበረከቱ ድረስ ችግሮች ቢበዛ በተጨማሪ አንድ ዓመት ጊዜ ተወግደው ምርጫ ለማካሄድ የሚያበቃ የተረጋጋ ሁኔታ መፍጠር ይቻላል የሚል እምነት አለኝ።

# የውክልና ፖለቲካ ሀገራዊ ምርጫ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ

*ዮናስ አሸኔ*

በኢትዮጵያ ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ከክርክሮች እና ከብዙ ጥያቄዎች ጋር በተጀመረው የፖለቲካ መፍታታት እና ሽግግር ዐውድ ውስጥ እየታለመ ነው። ይህ ጽሑፍ በዚህ ምርጫ ፖለቲካ ላይ በማተኮር በምርጫው ዙርያ የሚነሱ ጉዳዮችን ከውክልና ፖለቲካ፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ፓርቲ ሥርዓት ጋር ይመለከታል። በቅድሚያ የውክልና ፖለቲካ ምርጫ እና የፖለቲካ ማህበራት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ላይ በመመስረት ንድፈ-ሀሳባዊ እና ፅንሠ-ሀሳባዊ ትንተና ያቀርባል። ምርጫ እና የፖለቲካ ፓርቲ ጅማሮ፣ ፋይዳ እና እድገት በኢትዮጵያ፣ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ፓርቲዎች ታሪካዊ እና መዋቀራዊ ሁኔታዎችን ከአሁኑ የአገሪቱ የፖለቲካ መፍታታት ወይም ሽግግር አንፃር ይመለከታል። በመቀጠልም ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ይካሄድ ወይስ አይካሄድ? መቼ ይካሄድ? እና በመሰል ጥያቄዎች ዙርያ የሚነሱ ክርክሮችን ከፖለቲካዊ፣ አሰተዳደራዊ እና ሕጋዊ ትርክቶች አንፃር ይተነትናል። እግረ መንገድም ምርጫውን የተሣካ ለማድረግ ምርጫ አስፈፃሚ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት፣ ከፖሊቲካ ማህበራት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት መስራት ያለባቸውን ሥራዎች ለመጠቆም ይሞክራል።

## መግቢያ

የሕዝብ የውክልና ፖለቲካ የሕዝብ ሉዓላዊነት መገለጫ አንዱ ዓምድ ነው። ሕዝብ እንደራሴውን የመምርጥ፣ የመጠየቅና የመቀየር ሥልጣን፤ በፖለቲካ ማሕበራት የመሣተፍ የመመረጥ እና የመወከል መብትን ጭምር ያቀፈ የዘመናዊ ፖለቲካ አንዱ ገፅ ነው። የሕዝብ ውክልና በምርጫ ዘመን ብቻ ሳይሆን በዕለት ተዕለት የሕዝብ ሕይወት ዑደት ውስጥ ይተገበራል። የውክልና ፖለቲካ እንደራሴን ለምክር ቤቶች ከመምረጥ ባለፈ በድሕረ-ምርጫ ዘመን ዜጎች የፖለቲካ ተሳትፎ በማህበር ወይም በተናጥል በተለይ ብዙ አማራጭ የፖለቲካ ሜዳዎችን በመጠቀም የሚያደርጉትን ተሳትፎ ያቀፈ ነው። ለምሳሌ፣ የሙያ ማህበራትም ሆነ ሌሎች ሲቪል ተቋማትን በመጠቀም ዜጎች ጥያቄ መንሣት እና ሰፊ የፖለቲካ ተሣትፎ

ሊያደርጉ ይችላሉ። ሕዝቦች በማንኛውም ወቅት የሚያነሱት ጥያቄ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ የጤነኛ የፖለቲካ ማሕበረሰብ ምልክት ነው።

ምርጫ ሌላው የሕዝብ የወክልና ሉዓላዊነት መገለጫ ነው። ምርጫ ዘመን ጠብቆ የሚመጣ ዑደታዊ የፖለቲካ ኹነት ነው።ይህ ውስብስብ የፖለቲካ ሂደት የሕዝቦች ተሳትፎ አንዱ ገፅ ሲሆን ለዜጎች የፖለቲካ ንቃት በተለይም ለዲሞክራሲ ሰብዕና ግንባታ አስተዋፅዖ ያደርጋል። በምርጫ ዘመን ዜጎች ድምፃቸውን ያሰማሉ፣ የሌሎችን ዜጎችን ንግግሮች ያዳምጣሉ፣ የሀሳብ ልውውጦች ይካሂዳሉ፤ ይህም በሂደት የአገሪቱን ፖለቲካ ያዳብራል። ስለዚህ ምርጫ ወንበር ከማከፋፈል ያለፈ ሚና እንዳለው ይታመናል። የምርጫ ዘመን በሌሎች የፖለቲካ ምሕዳሮች ለሚካሄዱ ክርክሮች እና ስምምነቶች፤ ጥያቄዎች እና መልሶች ተጨማሪ ዐውድ ይሆናል። በተለይ እንደኛ አገር የዲሞክራሲ ተቋማት እንዳያድጉ በሆነበት ሁኔታ ወስጥ የምርጫ ዘመን ለፖለቲካ ቅራኔዎች አማራጭ መተንፈሻ ዐውድ ነው። ስለዚህ ምርጫ ለእንደራሴዎች መምርጫ ምህዳር ብቻ ሳይሆን ለፖለቲካ ማስተንፈሻና ማፍታቻ ዐውድ ተድርጎ ሊወሰድ ይችላል። በንድፈ-ሀሳብ ደረጃ የአገራችን ሕዝቦች ለፖለቲካ በተነቃቁበት፣ በተንቀሣቀሱበትና ብዙ ጥያቄዎች ያለፍርሀት በሚያነሱበት በዚህ ወቅት፣ የሀገራዊ ምርጫውን በስኬት ለማካሄድ መልካም አጋጣሚ ነው ተብሎ ሊታሰብ ይችላል። ለዚህ ሂደት የተሻለ ስኬት ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና የላቀ ነው።

በማንኛውም አገር ፓርቲዎች አንድ የፖለቲካ ምህዳር ገፅ ተደርገው ይታሰባሉ። ፓርቲዎች ማህበረሰቡን በተመሳሳይ የሀሳብ ፅዋ ዙርያ ያሰባስባሉ። የህዝብ ጥሬ ፍላጎቶችን ወደ ሀሳብ በማሸጋገር ርዕዮተ ዓለም ይቀርፃሉ፣ ትርክት ይገነባሉ፣ ረቂቅ የፖሊሲ መከራከሪያ ዲስኩር ይደርሳሉ። ማህበራቸውን ተቋማዊ ቅርፅ በመስጠት በማንቀሣቀስ የዲሞክራሲ ልምምድ መድረክ በመሆን ሀገራዊ የዲሞክራሲ ልምድ እንዲዳብር የራሣቸውን አስተዋፅኦ ያድርጋሉ። ፓርቲዎች ሀሳብ እና ተቋም ብቻ ሳይሆን መሪ ያዋልዳሉ። ዜጎችን ለፖለቲካ በመመልመል፣ በማስተማር በማለማመድ የዲሞክራሲ ተዋንያንን ያስመርቃሉ። “መሪ ከፓርቲ መድረክ ይወለዳል” ስለሚባል ተተኪ መሪ ፍለጋ ወደ ፓርቲዎች እንጂ ወደ ቤተ እመነቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች አይኬድም። በፖለቲካው ዓለም ግሉል የሚባል ተዋንያን የለም። በአገራችን ሰሞነኛ ፖለቲካ ታዋቂ ሰዎችን እና አዋቂዎችን በመመልመል የፖለቲካ አመራር ክፍተቱን ለመሙላት ጥረት ሲደረግ አይተናል። ማንኛውም ሹም ከቤተ እምነት ፣ ከቲያትር ቤት ወይም ከዩኒቨርሲቲ ቢመጣ፣ የፖለቲካ ተዋናይ እንጂ ኢፖለቲካዊ ፅድቅ ሊሆን አይችልም። የፓርቲዎች

መዳከም ሚናቸውን አለመወጣት የፈጠረው ክፍተት እንጂ የፖለቲካ ሽግግር አመራሩን ከነዚህ ተቋማት ባልተመለመለ ነበር። ነገር ግን ምርጫ የጎደለ ሊያሟላ በመጣ ተዋንያን አይከናወንም እና ፖለቲካ ፓርቲዎች መመስረት፣ መጠናከር እና ተራማጅ የፖለቲካ መሪዎችን የማፍራት ሚና መጫወት አለባቸው።

ምርጫን ምርጫ የሚያደርጉት ተመራጮቹ ወይም አማራጭ አቅራቢዎቹ ፓርቲዎች ናቸው። የፓርቲዎች ምስረታ፣ ዕደሳ፣ ውህደት፣ መለያየት፣ የምርጫ ዘመቻና ክርክር የፖለቲካውን ማዕድ ሙሉ ያደርገዋል። ፓርቲዎች ለዚህ ሁሉ እንቀስቃሴ ህብረተሰቡን ያንቀሳቅሳሉ፣ ያነቃሉ፣ ለአባልነት እና ለድጋፍ ይመለምላሉ። ስለዚህ ምርጫና ፓርቲዎች በሠርግና ሙሽሮች ሊመሰሉ ይችላሉ። ፓርቲዎች የድግሱ ዋነኛ ተዋንያን እና ከያኒያን ናቸው። በአገራችን ወርኃ ግንቦት በየአምስት ዓመቱ ለፓርቲዎች ትልቅ ብሔራዊ የፖለቲካ ሰርግ ነው። ባለፉት አምስት ሀገራዊ ምርጫዎች እንደተመለከትነው የምርጫው ዓመት ከገባ ጀምሮ ነባር ፓርቲዎች ቀስ በቀስ እንቅስቃሴ የሚጀምሩበት፣ አዲስ ፓርቲዎች ተመስርተው ለድግሱ የሚሻሙበት፣ ለአራት አመታት እንቅስቃሴ ሳያደርጉ የቆዩ በርከት ያሉ የትርፍ ጊዜ ፓርቲዎች ሕይወት የሚዘሩበት ወቅት ነው።

ስለ ሕዝብ የውክልና ፖለቲካ፣ ምርጫ እና ፓርቲዎች ይህን ሲባል ግን ፓርቲዎቸ የፖለቲካ መሚሀን፣ ምርጫም የፖለቲካ ዓልፋ እና ኦሜጋ አይደለም። የማህበረሰቡም ፍላጎት በምርጫ ሳጥን ውስጥ ተካትቶ የሚያከትም ሳይሆን፣ ሳጥኑ ፍላጎትን ከመግለጫ መንገዶች አንዱ ብቻ ነው። የሕዝቦች የፖለቲካ ሕይወትም በምርጫ ሰሞን ብቻ በሚደረግ እንቅስቃሴ የተገደበም አይደለም። ነገር ግን ፓርቲዎች እና ምርጫ በአገራችንም ሆነ በመላው አፍሪካ የሚታዩት ከዚህ በተለየ መልኩ ሆኖ፣ በተለይ ምርጫ የፖለቲካ መጨረሻ በሚመስል ሁኔታ ብዙ ሀብት ጊዜ እና በተለይ ግጭትን ስለሚወልድ ከፍተኛ አሉታዊ ጉዳት ያስከትላል። ስለ ምርጫ እና ፓርቲዎች ሲነሳ ትክክለኛ ታሪካዊ ቦታቸው ከጅምሩ መገለፅ አለበት። ምርጫ እና ፓርቲዎች እንደውም ባጠቃላይ የውክልና ዲሞክራሲ የሕዝቦች የፖለቲካ ሕይወት አንድ ገፅ ብቻ ነው። የሕዝቦች የፖለቲካ ሕይወት ከፓረቲዎች የሰፋ መካነ ፖለቲካ ከምርጫ ዑደታዊ ኹነት የጠለቀ እና ውስብስብ የፖለቲካ ምህዳር ያለው በየዕለቱ በየቦታው በየትየለሌ ጉዳዮች የተዋቀረ ነው።

## የውክልና ፖለቲካ እና ሕዝባዊ እምቢተኝነት

“የውክልና ፖለቲካ የሕዝብ ሉዓላዊነት መገለጫ ነው” ሲባል በዘመናዊ ፖለቲካ የሕዝቦችን ድምፅና ተሳትፎ ሲቪል ማረጋገጫም ስለሆነ ነው። ይህ የሉዓላዊነት መገለጫ የሕዝቦች ታሪካዊ የትግል ፍሬ ነው። እንደ ሕዝቦች ትግል ባይሆን ኖሮ

ዛሬ ስለ ፖለቲካ ሽግግር በኢትዮጵያ ባላወራን ነበር። በየጊዜው በዘመናዊ ኢትዮጵያ እንደ ተከሰቱ የሽግግር ዘመናት የዚህ የኛ ዘመን ተራማጅ የፖለቲካ ሽግግር ዋዜማ የሕዝቦች እምቢተኝነት ነው። የውክልና ፖለቲካ ሁልጊዜ በሰፊው ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች፣ በእምቢተኝነት እና በሕዝባዊ አብዮት ጥላ ስር ይካሄዳል። የውክልና ፖለቲካ ሲወድቅ ሲዳከም እና እንዳይሰራ ሲደረግ አብዮት ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ይፈጠራል። አብዮት ከውክልና ፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ይወለዳል።[22] ይህ የሕዝብ ቀጥተኛ የፖለቲካ ተሳትፎ የሚወልደው የፖለቲካ ኹነት የታደሰ ወይም አዲስ የፖለቲካ ስርዓት መፍጠሪያ ዐውድ ይፈጠራል። አብዮት ወይም ማንኛውም ሕዝባዊ ማህበረ-ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የተሳካ ከሆነ ለህዝቦች የውክልና ፖለቲካ መብት እና ሥልጣን አዲስ በር ይከፍታል። አብዮት ራሱ በውክልና ፖለቲካ ጥላ ስር የሚካሄድ ይመስላል።

የውክልና ፖለቲካ ወይም ምርጫ የመገዛትና የመግዛት ትርክትን አስወግዶ ለመተዳደር ነፃ ፍቃድ መስጫ ነው። የውክልና ፖለቲካ ሲቃወስ አብዮት ወይም ሕዝባዊ እምቢተኝነት ገዢነት እና ተገዢነት የሚወገድበት የፖለቲካ ኹነት ሆኖ ይከሰታል። የተሳካም ከሆነ ለአዲስ ሕይወተ-ማሕበር (assocational life) በር ይከፍታል።[23] እንደ ኢትዮጵያ ባለ አገር የውክልና ፖለቲካ እና አብዮት የአገሩ የፖለቲካ ታሪክ ሁለት ገፆች ናቸው። የኢትዮጵያን የፖለቲካ ታሪክ በአፅንኦት ለተመለከተ፣ የውክልና እና የአብዮት ጉራማይሌ መሆኑን ይገነዘባል። ይህ ቡራቡሬ ታሪክ የተፃፈው ሁልጊዜ ተራማጅ ብለን የምንቀምረው እና የምንሞክረው የውክልና ፖለቲካ በሚከፍተው ቀዳዳ መፈንቅለ መንግስትን፣ ህዝባዊ እምቢተኝነትን ወይም አብዮትን ስለሚወልድ ይመስላል። ይህም ቢያንስ በመጀመሪያው ሕገ-መንግስትት መረቀቅ ላይ ከተካሄደው ክርክር ጀምሮ ያለምንም ጦርነት እና ግጭት የተጀመረውን የውክልና ፖለቲካ ልምድ በአብዮት እየተደናቀፈ ዛሬ ላይ ደርሰናል። በቅርቡ በአገራችን የተካሄደው ሕዝባዊ

[22] Arendt Hannah. "Disobedience" in *Crises of the Republic*. San Diego: A Harvest/HBJ Book, 1972: 69 She argues that "if history teaches anything about the causes of revolution- and history does not teach much, but still teaches considerably more than social-scinece theories-it is that a disintegration of political systems precedes revolutions, that the telling symptom of disintegration is a progressive erosion of governmental auhtoerity and that this erosion is casued by the government's inability to function properly, from which spring the citizens' doubts about its legitimacy."

[23] Arendt Hannah. *On Revolution*. London: Penguin Books. 2006

እምቢተኝነት በአገሪቱ ከተሞከረው የሕዝባዊ ፖለቲካ ውክልና ቀውስ የተወለደ ነው።

አሁን ያለንበትም የፖለቲካ መፍታታት ዘመን የአገሪቱን የውክልና ፖለቲካ፣የምርጫ እና የፓርቲ ስርዓት ግንባታ ልምዶች እና ሙከራዎች ተጠንተው የሕዝባዊ እምቢተኝነቱ ያነሳቸውም ጥያቄዎች ታሳቢ ተደርገው የተሻለ የውክልና ፖለቲካ ምሕዳር የሚፈጠርበት ታሪካዊ ወቅት ላይ እንገኛለን። ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ራሱን ፈትሾ ፖለቲካዊ፣ ተቋማዊና አስተዳደራዊ ማሻሻያዎች እንዲያደርግ ታሪክ ዕድል የሰጠው ወቅትም ነው። ይህም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር ቀጥሎ ሁለተኛ ራሱን የማደስ ዕድል ያገኘው የኢህአዴግ አስተዳደር ነው። ሁሉም የዘመናዊ ኢትዮጵያ አስተዳደሮች ተራማጅ ዘመናቸውን በወግ አጥባቂ ዘመን እየተኩ ራሳቸውን የማደስ ዕድል ሳይጠቀሙበት በሕዝባዊ እምቢተኝነት ሲሸኙ በታሪክ አይተናል።[24]

መጪውን የስድሰተኛው ሀገራዊ ምርጫን በስኬት ለመከወን ከአንድ ዓመት ያነሰ ጊዜ ብቻ ይቀራል። ለሽግግሩ መሳካት የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጨምሮ ሌሎች የዲሞክራሲ እና የሕዝባዊ ምርጫ ማስተዳደርያ እና ማስፈፀሚያ ተቋማት በሚዘጋጁበት ዘመን ላይ እንገኛለን። በኢህአዴግ መሪነት የሚደረገው ይህ የፖለቲካ ሽግግር ወሳኝ ወቅት መጪው ሀገራዊ ምርጫ ነው። ምርጫው ይካሄድ ወይስ አይካሄድ? መቼ ይካሄድ? ምርጫ በምን ሁኔታ ውስጥ ነው የሚካሄደው? በማለት፣ ዜጎች እና የፖለቲካ ኃይላት ጥያቄ ሲያነሱ የሚገነቡት ፖለቲካዊ፣ ሕጋዊ (ሕገ-መንግስትታዊ) እና አስተዳደራዊ ትርክቶች ምንድን ናቸው? ለነዚህ ፈታኝ ጥያቄዎችስ ምን አማራጭ መልሶች አሉ? እነዚን ጥያቄዎች ለመተንተን ብሎም አመራጮችን ለመመልከት የኢትዮጵያ የውክልና ፖለቲካ በተለይም የሕዝብ ሉዓላዊነት መገለጫ የሆኑት ምክር ቤቶች፣ የምርጫ ሥርዓት እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ጅማሮ እና ሽግግር ምን እንደሚመስል በወፍ በረር መቃኘት ያሻል።

## ፓርቲዎች በኢትዮጵያ፡- ታሪካዊ ምልከታ

የፓርቲዎች ታሪክ በኢትዮጵያ ሦስት ትውልድ አሳልፏል። የመጀመርያው የፖለቲካ ማህበራት ትውልድ በ1950ዎቹ ጀምሮ የተመሰረቱት የፖለቲካ

[24] ባሕሩ ዘውዴ *ኃይለ ሥላሴ ከተራማጅነት ወደ ወግ አጥባቂነት* በውይይት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ማኅበር መጽሔት 3ኛ ሴሪ ቅጽ 2 ቁጥር 1 መጋቢት 1985 አዲስ አበባ ገፅ 35-54 ፕሮፌሰር ባሕሩ ተራማጅ ሲል *ታሪክን በቅጡ ተረድቶ ይህንኑ ሂደት ለማፋጠንና ለማበረታት በፅኑ ሲጥር ነው* ይላል ወግ አጥባቂ ደግሞ *የታሪክን እርምጃ ካለመረዳት ወይም ካለመፈለግ ለሂደቱ እንቅፋት ወይም ፍሬን ሰገኝ ነው* ይላል (ገፅ 39) በዚህ ድርሰት ውስጥ እነዚህን ሁለት ፅንሰ-ሀሳቦች በዚህ ተርጉም አንፃር ተጠቅሜያቸዋለው።

ማህበራት ያካትታል፡፡ የዚህ ትውልድ ፓርቲዎች ዐውድ እንደ ምዕራባዊያን የፓርቲ ምስረታ ታሪክ ከዲሞክራሲ መስፋፋት፣ ከመብት እና የምርጫ ፖለቲካ መጀመር ጋር የተያያዘም አልነበረም፡፡ እንደ አብዛኛው የአፍሪካ ፓርቲዎች ምስረታም በቅኝ ግዛት ሰማይ ስር የተመሰረቱም አልነበሩም፡፡[25] በኢትዮጵያ የመጀመርያው ትውልድ የፖለቲካ ማህበራት በገበሬዎች አመፅ በተማሪዎች እንቅስቃሴ እና በብሔርተኝነት እንቅስቃሴዎች ዐውድ ውስጥ የተመሰረቱ ነበሩ፡፡ ዓላማው ስልጣን ይዞ የተሻለ የተባለውን ሀሳብ ለማራመድ መወዳደር ሳይሆን በዘመናዊ ሀገረ-መንግስት ምስረታው ጋር የተፈጠሩ ቅራኔዎች የወለዳቸው ጥያቄዎችን ለማራመድ የተፈጠሩ ነበሩ፡፡ ከፊሎቹ አዲስ ሀገረ-መንግስት ለመመስረት ዓላማ ይዘው የተመሰረቱ ነፃ አውጪ ድርጅቶች ሲሆኑ (ለምሳሌ ህወሀት እና የኤርትራ ድርጅቶች) ሌሎቹ ደግሞ በሥልጣን ላይ የነበረውን መንግስት በአብዮታዊ መንገድ ለማስወገድ በተለይም የተማሪዎች እንቅስቃሴ የወለዳቸው ማርክሳዊ ሌኒንያዊ ድርጅቶች (ማሌድ) ነበሩ፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች አብዮት እንዲኖር ከተፈለገ አብዮታዊ ፓርቲ የግድ ያስፈልጋል በሚል መርሕ ስር በአብዮት ዓውድ ውስጥ የተመሰረቱ ነበሩ፡፡[26] ከነዚ በተቃራኒ ተሸናፊውን የዘውድ አገዛዝ የሚወክል ፓርቲ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኅብረት በሚል ተመስርቶ ነበር፡፡ በወታደራዊ ክንፍ የተመሰረተው ጊዚያዊ ኮሚቴ አገር የሚያሥተዳድር ማህበረ ወታደሮች በኋላም የኢትየጵያ ሠራተኞች ፓርቲን (ኢሠፓ) የሚወልደው ደርግ በዚሁ ትውልድ ያጠቃልላል፡፡[27]

በፅንሠ-ሀሳብ ደረጃ ራሳቸውን በተለያ ስም ሰይመው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሲሆን፣ አንድ ማህበር በመጀመርያ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አርነት ድርጅት፣ በኋላ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ፓርቲ በማለት በ1967 ዓ/ም ተመሰረተ፡፡[28] የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በማለት ራሱን ፓርቲ ብሎ ሲሰይም ሌሎች ለምሳሌ መላ ኢትዮጵያ ሶሺያሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) የኢትዮጵያ ሕዝብ

---

[25] Mohamed Salih M. A. “Introduction: The Evoltion of African Political Parties” in *African Political Parties: Evolution, Institutionalisation and Governance*. Edited by Mohamed Salih M. A. London: Pluto Press,2003፡፡1-36

[26] “If there is to be a revolution there must be a revolutionary party*” Challenge: The national Democratic Revolution in Ethiopia.* Volume xii number 1 October 1962 A journal of the world wide Union of Ethiopian Students published by the Ethiopian Students Union in North America.

[27] Andargachew Tiruneh *The Emergence and Proliferation of Political Organizations in Ethiopia* Tsehai Publishers, 2015.

[28] ክፍሉ ታደሰ *ያ ትውልድ ቅፅ አንድ ዴርቶጋዳ አሳታሚዎች፣* 119

ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢሕዴን) ንቅናቄን እንደ መጠርያ ስም ተጠቅመው ነበር፡፡ የስም ልዩነት ቢኖራቸውም በዐብይ ጎዳዮች ተመሳሳይ አቋም ያላቸውና ብዙም ርዮተ-ዓለማዊ ልዮነት ያልነበራቸው ማርክሳዊ ሌኒንያዊ ደርጅቶች (ማሌድ) ነበሩ፡፡ የዚህ ትውልድ "ማህበራት ምርጫ ፖለቲካ ከተጀመረ ቢያንስ ሁለት አስር አመታት በኋላ የተመሰረቱና ከምርጫ ፖለቲካ ጋር ምንም አይነት ርዕዮተ-ዓላማዊ ትስስር ያልነበራቸው፣ አብዛኞቹ የታጠቁ እጅጉን ሚስጥራዊ የሆኑ፣ ሕቡዕ የገቡ፣ ትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ እና እርስ በእርስ ጭምር የተዋጉ ድርጅቶች ነበሩ፡፡[29] ለምሳሌ መኢሶን በ1960 መጀመርያ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም እስከ 1960ዎቹ አጋማሽ ብዙም የማይታወቅ በሕቡ የተደራጀ ማህበር ነበር፡፡[30]

የሁለተኛ ትውልድ ፓርቲዎች፣ በመጀመርያው ትውልድ ድርጀቶች ላይ ተመስርተውና መለያ ደርበው በአዲስ ዐወድ ከ1980ቹ ጀምረው መንቀሳቀስ የጀመሩ ፓርቲዎችን ያጠቃልላል፡፡ በድህረ 1983 ዓ.ም. የፖለቲካ ዘመን በምዕራቡ ዓለም ብቻ ሳይሆን በአፍሪካም ምርጫን እና ፖለቲካ ፓርቲዎች የአንድ አገር ፖለቲካ ዋነኛ ኹነቶች ሆነው ብቅ ያሉበት ዘመን ነበር፡፡[31] በአገራችንም የነበሩ ነፃ አውጪ ደርጅቶች ከዓለም ሁኔታ መቀየር ጋር ራሰቸውን ማዘጋጀት ሲገባቸው፤ ትጥቅ ሳይፈቱ፣ ተቋማዊ አደረጃጀታቸውንና ስማቸውንም እንኳ ሳይቀይሩ ወደ ውክልና ምሕዳርና ምርጫ ሜዳ ነበር የገቡት፡፡ ኢህአዴግ የተመሰረተውም በትጥቅ ትግል ደርግን አሸንፈው ሥልጣን በያዙ ነፃ አውጪ ድርጅቶች ነው፡፡ እነዚህ አብዮታዊ ድርጅቶች ሁለት የሚጋጩ ዓላማዎችን፡ አብዮትና ዲሞክራሲን ይዘው ስለሆነ ከጅምሩ አንዱን ጥለው ሌላውን አንጠልጥለው በውክልና ፖለቲካ ዐወድ ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ በሂደትም በንግድ ውሰጥ መሰማራት ስለጀመሩ የአገሪቱ የፓርቲ ስርዓት መዋቅራዊ ጉድለት ይዞ እንዲጀምር አድርጎታል፡፡

በዚህ ዘመን ከተመሰረቱ ፓርቲዎች አብዛኞቹ በጥቂት ግለሰቦች የተመሰረቱ የልሂቃን ፓርቲዎች ሆነው ከገዢው ፓርቲ ወይም ከዲያስፖራ የፖለቲካ ኃይሎች አጀንዳ የሚቀረፅላቸው እና ቀለብ ወይም በጀት የሚቆረጥላቸው ጭፍራ ፓርቲዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ከፊሉ "*በትሮይ ፈረስ*" የሚመሰሉ የኢህአዴግ ጭፍራዎች ናቸው፡፡[32] በተለይ በክልሎች የሚንቀሳቀሱት ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ

[29] Kassahun Berhanu. "Party Politics and Political Culture in Ethiopia" in *African Political Parties: Evolution, Institutionalisation and Governance*. Edited by Mohamed Salih M. A. London: Pluto Press,2003። 115-147

[30] *ክፍሉ ታደሰ ያ ትውልድ ቅፅ አንድ ዴርቶጋዳ አሳታሚዎች*፣ 118

[31] Mohamed Salih M. A. "Introduction,1-36

[32] Kassahun Berhanu. "Party Politics and Political Culture in Ethiopia"፣ 135

ድርጅት በሚል ስም በስፋት የተደራጅ የብሔር ድርጅቶች ሚናቸው ከትሮይ ፈረስነት የተለየ አይደለም::[33] በራሳቸው የማይቆሙ ወይም ሕዝባዊ ተቀባይነት የሌላቸው ድርጅቶች ናቸው:: እነዚ ለውክልና ፖለቲካም ሆነ ለዲሞክራሲ የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ይልቅ ጉዳታቸው እጅግ የላቀ ነው:: ከነዚህ በተለየ የተቋቋሙ የተለያዩ ፓርቲዎች ምንም እንኳ የሕዝብ ወክልና አንድ አማራጭ ቢሆኑም በአብዛኛው በመሲህ መሰል ግለሰቦች የሚመሩ የሴቶች አመራርነት በዙም የማይታይባቸው ፓርቲዎች ናቸው::

## መሲሀዊ ፖለቲካ ፓርቲዎች፡- ሌላው የፖለቲካ ፓርቲ ሥርዓት ጉደለት

በአብዛኛው የፖለቲካ ማህበራት ምንም እንኳን የተለያየ አወቃቀር ቢኖራቸውም፣ በግለሰብ ጥላ ስር የተጠለሉ ምናልባትም እንደ ቅደመ-ዘመናዊ ኢትዮጵያ ኃይማኖታዊ ማህበራት በአንድ መምህር ስር እንደተሰበሰቡ ደቀመዛምርቶች እና ተከታዮቻቸውን የመሰሉ ናቸው:: እነዚህ ማህበራት የጥበብ ዕዋቸውን የሚጠጡት እና ሊቃውንታዊ እንቅስቃሴ የሚያካሂዱት በመስራቹ ግለሰብ ስር ነው::[34] አስተምህሮቱም በመስራቹ ሊቃውንት ስም የተሰየመ መስራቹ በሕይወት እያለም ሆነ ካለፈ በኂላ ማህበሩ በሱ ሲጠራ ይኖራል:: የዘመናዊው ፖለቲካ ማህበራትም ከጅምሩ እስከ ዘመናችን ድረስ ከዚህ የተለዩ አልነበሩም::

የመጀመርያ ትውልድ ፓርቲዎች ምንም እንኳ ጠንካራ ስብስብ እና አባላትን የማንቀሣቀስ ባህርይ ቢኖራቸውም የግለሰብ መሪዎቹ ተፅዕኖ የጎላ ነበር:: ከመኢሶን የኃይሌ ፊዳን፣ ከኢሕአፓ የብርሀነ መስቀል ረዳን ሚና ለምሣሌ መውሰድ ይቻላል:: ኂላም የሁለተኛው ትውልድ ፓርቲዎች በተመሳሳይ በግለሰቦች ጥላ ስር የቆሙ ተቋማዊ ጥንካሬ ሳይሆን ግለሰባዊ ግርማሞገስ ያቆማቸው ናቸው:: ምናልባትም ፖለቲካችን አንጄላ ዴቪስ የአፍርካ አሜሪካን ፖለቲካ ለመግለፅ የተጠቀመችበት መሲሐዊ ስርዓት (messianic complex) የኢትዮጵያን የፓርቲ ሥርዓት ሁነኛ መገለጫ ሊሆን ይችላል::[35] "የኢትዮጵያዊው ማንዴላ"

---

[33] Merera Gudina Ethiopia: *From Authocracy to Revoltionalry Democracy, 1960s-2011.* Addis Ababa: chamber Printing House, 159

[34] ለምሳሌ በዘመነ ዘርያቆብ የተነሱት ሦስቱ ኃይማኖታዊ የሊቃውንት እንቅስቃሴዎች ማለትም ኤዎስጣቴዋሳውያን፣ ደቂቀ እስጢፋኖስ ወይም እስጢፋኖሳውያን እና ዘሚካኤላውያን ስማቸው እንደሚያሳያው በሦስት ሊቃውንት ዙርያ ማለትም በአባ እስጢፋኖስ በአባ ገበርኤል እና በአባ ዮስጣጤዎስ አስተምህሮት ስር የተመሰረቱ ነበሩ። ጌታቸው ኃይሌ *ደቂቀ እስጢፋኖስ። በሕግ አምላክ* አዲስ አበባ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ 2002

[35] Angela Y. Davis *The Meaning of Freedom: And Other Difficult Dialogues.* San Francisco: City Lights Publishers, 2012.

ትርክት በ1997፣ "የአሻጋሪው ሙሴ" ትርክት በዚህ በዘመናችን የፖለቲካ ሽግግር ዘመን ምንኛ ጎልተው እንደወጡ መጥቀስ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል:: እነዚህ መሰል ግለሰቦች ከፓርቲው ሲለዩ ማህበራቱ ቆመው የሚቀሩ፣ የሚከስሙ ወይም ከመስመራቸው ወጥተው ሲዳከሙ ወይም ሲከፋፈሉ ማየት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ አዲስ አይደለም::

በኢትዮጵያ የፓርቲዎች ታሪክ አንቶኒዮ ግራምሼ እንደሚለው የአንድ ማሕበራዊ ስብስብ ወይም ክፍለ-ሕብረተሰብ መደብ ብሔር ወዘተ ከሌሎች ወዳጅ ማህበረሰቦች እና ከተፎካካሪ ስብስቦች ባጠቃላይ ከሰፊው የአገሪቱ ህዝብ እና ዓለም አቀፍ ኹነቶች እና ተዋንያን ጋር የሚያደርገው እንቅስቃሴ ታሪክ ተደርጎ አይወሰድም:: የፓርቲዎቹ ታሪክ ሲፃፍም በአብዛኛው "እኔና የፖለቲካ እርምጃዬ" በሚል ዘውግ ወስጥ እንደ ህይወት ታሪክ ነው::[36] በአገራችን ከተቋማት ታሪክ መፅሐፍት ይልቅ የሕይወት ታሪክ መፅሐፍት የበዛው ለዚህም ይሆናል::

የፖለቲካ ማህበራት እና የአገሪቱ ስርዓተ-ፖለቲካ ማህበር የተዳከመ እንዲሆን ዋናው ምክንያትም ይህ ከግለሰብ ጥላ የተላቀቁ ዲሞክራሲያዊ ማህበራት ያለመገንባታቸው ነው:: የፓርቲ ፖለቲካው ከግለሰቦች እጅ ሊወጣ እና በተቋማዊ አደረጃጀት ሊመራ ይገባል:: የኒኮሎ ማካቬየሌ ፈርጣማው፣ ሁሉን አድራጊው እና ብልሀተኛው መሢሀዊ ልዑል በሚመሰል መሪም ሊመሩም አይገባም:: እንደውም ከእንደዚህ አይነት ግለሰቦች ተፅዕኖ መላቀቅ የዘመናዊ ፖለቲካ አንዱ መገለጫ ነው:: ለዚህም ነው ፖለቲካ ፓርቲዎች ራሳቸው ዘመናዊው ልዑላን የሚባሉት:: ይህም በመሢሀዊ ልዑል ስለሚመሩ ሳይሆን እንደ ተቋም አንዱ በቁሳር ይተገበር የነበረውን ፖለቲካ በፓርቲዎች መተካቱን ለማመለከት ነው::[37] የፓርቲዎች የማሕበረሰብን ዕምቅ ኃይል በመደራጀት፣ ህዝባዊ የፈጠራ አቅሙን ወደ ተቋማዊ ማንነት በመለወጥ ንቃተ ሕሊናው የዳበረ እና ስነ-ስርዓት የተላበሰ ተራማጅ ሊሂቃን ስብስብ በማፍራት የአገሪቱን ፖለቲካ የማዘመን ሚና የላቀ ነው::

በኢትዮጵያ ፓርቲዎች ወይም የፖለቲካ ማህበራት ምስረታ ሶስተኛ ትውልድ አሁን በመታደስ እና በመመስረት ላይ ሲሆን አሁንም ከመሲሐዊ የፖለቲካ ፓርቲ ስርዓት ያለመውጣት አዝማሚያዎች ይታያል:: ራሳቸውን አድሰናል ያሉም ሆነ ራሳቸውን በማክሰም አዲስ ፓርቲ የመሰረቱ እና በቅርቡ ከሀገራዊ የፖለቲካ

[36] ለምሳሌ ኃይሉ ሻውል (ኢንጂነር) ሕይወቴ እና የፓለቲካ እርምጃዬ በፍሬው አበበ የተዘጋጀ 2005 ዓ. ም ፋሪስት ትሬዲንግ

[37] Antonio Gramsci, Selections from Political Writings 1910-1920, ed. by Quintin Hoare (New York: International Publishers, 1977), 188-189. ግራምሼም እንደ ሌሎች ግራዘመም ሊቃውንት ፓርቲ ሲል አብዮታዊ ፓርቲ ማለቱ ነው።

መፍታታት ዐውድ ውስጥ የተወለዱ ፓርቲዎች ተቋማዊ አድማሳቸው ከዚህ መሲሀዊ የፖለቲካ-ስርዓት የተለየ በማድረግ በውስጣቸው የስልጣን ሽግግር ባህል በማዳበር የአገሪቱን የሥርዓተ ፖለቲካ ማህበር ወደፊት ማራመድ ይጠበቅባቸዋል።

ከፓርቲ ውጪም የሚካሄደውም ፖለቲካ ምንም እንኳ ሠፊውን ሕዝብ ያሳተፈ ቢሆንም፣ ከግለሰብ ልሂቅ ተፅዕኖ ስር ያልወጣ በመሆኑ የዲሞክራሲ ጉዞውን አዳጋች ያደርገዋል። ይህ መሲሀዊ ስርዓት ተፅዕኖ መጪውን ምርጫ ብቻ ሳይሆን የድህረ ምርጫ ሲቪክ ፖለቲካ ላይም የሚያርፍ ይሆናል። በኢትዮጵያ የሕዝባዊ ፖለቲካ ግለሰቦች የለወጡ አቀጣጣዮች በመሆን ሚናቸው ጉልህ ቢሆንም፣ የአንበሳውን ድርሻ የሚይዘው ሰፊው ማህበረሰብ መሆኑ ግልፅ ነው። ለምሳሌ በፖለቲካ መፍታታቱ ዘመን ያለው እንቅስቃሴ በግል የሚንቀሳቀሱ አንቂዎች መሀከል የሚካሄደው ጉንጭ አልፋ ጭቅጭቅ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲፈጥር ቆይቷል። እነዚህ ግለሰቦች በአብዛኛው ከማንኛውም የፖለቲካ አደረጃጀት ከፓርቲም ይሁን ሌላ ሲቪል ማህበር ሳይታቀፉ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ሆነው ለመቆየት መወሰናቸው በተቋማዊ ፖለቲካ ላይ ባጠቃላይ በፖለቲካ መፍታታት ሂደት ላይ ተፅእኖ ፈጥሯል። አንዳንዶች በፖለቲካ ፓርቲ የታቀፉም ቢሆን፣ የፖለቲካ ባህርያቸው ከግል አክቲቪስቶች ያልተለየ መሲሀዊ ፖለቲካ የሚያራምዱ ሆነዋል። በፓርቲ ሥርዓቱ ላይ ያሉ ችግሮች ተቋማዊ መዋቅራዊ አብዛኞቹ ከታሪክ የተወረሱ ሌሎቹ አሁን በአይናችን ስር የተፈጠሩ ችግሮች ሲሆኑ፣ ዛሬ ማድረግ የሚቻለው ችግሮቹን ነቀሶ በማውጣት በሂደት ለማከም መሞከር ነው። ወደ 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ የሚደረገው ጉዞ የፓርቲ ስርዓቱ ያለበትን ችግር ተረድቶ በምርጫው ላይ ያለውን ተፅዕኖ ለመቀነስ ሰራ መሰራት አለበት። የፓርቲዎች አለመዘጋጀት እንደምክንያት በመውሰድ ምርጫው ይራዘም የሚል ሀሳብ ብዙም አሳማኝ አይደለም። ምክንያቱም አንደኛ ተዘጋጁ የሚባሉት ፓርቲዎች ራሳቸው የሰፊው ችግር አካል በመሆናቸው፣ ሁለተኛ የፓርቲዎች እንቅስቃሴ የሚሟሟቀው ምርጫው በደንብ ሲቀርብ መሆኑ ታውቆ ምርጫውን የተሳካ ለማድረግ ስራዎች ቢሰሩ የተሻለ ነው።

## ሀገራዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ጊዜው ገና ነው፡- ያ እስኪሆን ድረስ

በኢትዮጵያ የውክልና ፖለቲካ ከ1923 ዓ.ም የመጀመርያው ሕገ-መንግስትት ጀምሮ አጀንዳ በመሆን ሲያከራክር ነበር። ይህ ወቅት መላው አፍሪካ በቅኝ ግዛት ስር ሆኖ ለነፃነት ትግል ሲያደርግ የነበረበት ዘመን ነው። ሕገ-መንግስትት በማርቀቅ፣ የሕዝብ ውክልና መብት ዕውቅና በመስጠትና ምክር ቤት በማቋቋም

ዙርያ የተደረገው ክርክር ከተማሪዎች እንቅስቃሴ በፊት የተደረገ ዋነኛ ሀገራዊ የፖለቲካ ክርክር ነበር። ተራማጅ ልሂቃን በአንድ ወገን፣ የመሳፍንቱ መደብ በሌላ ወገን ሆነው ያደረጉት ወይይት የውክልና ፖለቲካ እና ብሔራዊ ምክር ቤቶችን በሂደት ያዋለደ ነበር።[38]

ምንም እንኳ የፀደቀው የመጀመሪያ ሕገ-መንግስትት የሕዝብ እንደራሴዎችን የመምረጥ መብት ለሕዝቡ ባያጎናፅፍም የሕዝብ እንደራሴነት እና ምክር ቤት እንደ ፖለቲካ ተቋማት እና ፅንሰ-ሀሳብ ወደ አገሪቱ የፖለቲካ ገበታ የተዋወቁበት ዘመን ነበር። ሀሳቡ *ሥዩመ-እግዚያብሔር* የሆነውን ንጉስ *ሥ*ልጣኑን በመገደብ የሕዝብ ውክልና በምርጫ እንዲቋቋም ታስቦ ምክር ቤቶችን ቢያስተዋውቅም፣ የፀደቀው ሕገ-መንግስትት ግን አዘጋጁ እንዳሰቡት የሕዝብ ውክልና ፖለቲካ መጀመርያ ሊሆን አልቻለም።[39] ሕዝቡ ለአቅመ ምርጫ እስኪደርስ ምክር ቤቶቹን የሚሞሉት አባላት ንጉሱ (ለሕግ መወሰኛ ምክር ቤት)፣ የአውራጃው ገዢዎች እና ሹማምንት (ለሕግ መምርያ ምክር ቤት) በሞግዚትነት እንዲመርጡለት የታሰበ ነበር።[40]

የመሣፍንቱ መደብ ራሱን የሕዝብ ተቆርቋሪ፣ አሳቢ እና ሕዝቡን በቅርብ የሚያውቅ ተወካይ አድርጎ ይመለከት ነበር።[41] የሕዝብ ውክልና ዘመን ያልደረሰ እንደውም መሣፍንቱ "ጊዜው ገና ነው፤ ያ እስኪሆን ድረስ" እያሉ የውክልና ፖለቲካ ጅማሮን አዘግይተውታል።[42] የሕዝቡ ንቃተ ሕሊና እና ዝግጁነት፣ ሕዝባዊ ምርጫ እንዳይካሄድ እንደ ፖለቲካዊ ምክንያት ይቀርብ ነበር። በወቅቱ ምርጫ ለማካሄድ ወይም ለማዘግየት የሚነሱ ብዙም አስተዳደራዊ ጉዳዮች አልነበሩም። ዋናው ክርክር አገረ-መንግስቱን ለማሻሻል እና ሕገ-መንግስትታዊ ቅርፅ ለመስጠት ነበር ክርክሩ የተደረገው። ሕገ-መንግሥቱ ፀድቆ ያለምንም

---

38 ዘውዴ ረታ *የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት 1ኛ መጽሐፍ 1923-1948* ሻማ ቡክስ አዲስ አበባ።2005 18-47

39 *የመጀመርያ ሕገ-መንግስት ለመፃፍ እንደኛው ፍልስፍና እንደ ተክለ ሐዋርያት አገላለፅ ሕዝቡ ከጥቃት እንዲያድን የታመነ መመከቻ እንዲኖረው ለመተዳደርያው የሚሆነውን መሪ ሐሳብ ራሱ በፍቃዱ እያግረጠ መቁረጥ እንዲቻለው ነበር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም ኦቶባዮግራፊ (የሕይወቴ ታሪክ)* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ አዲስ አበባ፡ 1998።401-402

40 ዘውዴ ረታ *የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግስት 1ኛ መጽሐፍ 1923-1948፣* ሻማ ቡክስ አዲስ አበባ። 2005 18-47

41 የመሳፍንት መደብ ወክለው ሲከራከሩ የነበሩት ራስ ካሣ ኃይሉ አስተያየት ለመመልከት *የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት ገፅ* 28-29 ይመልከቱ ።

42 ልዑል ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ *ካየሁት ከማስታውሰው* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ አዲስ አበባ 2002 ።182-186

ሕዝባዊ ምርጫ የመጀመርያው ፓርላማ ጥቅምት 24 ቀን 1924 ዓ/ም. ተከፈተ::[43]ሆኖም ይህ ምክር ቤት ለረጅም ዘመን የመሣፍንቱን የሕዝብ ሞግዚትነት እና የተወካይነት ሥልጣን በመርህ ደረጃም ቢሆን መሸርሸር የቻለ ምናልባትም አዲስ የውክልና ፖለቲካ እና የምክር ቤት ታሪክ በአገሪቱ የፖለቲካ ጉዞ ላይ መፃፍ መጀመሩን ያበሰረ ነበር።

ይህን የውክልና ፖለቲካ ያስተዋወቀው የ1923ቱ ሕገ-መንግስትት *ዘመናዊና ዲሞክራሲያዊ* ባለመሆኑ ለነበረው ሕዝባዊ አስተሳሰብ፣ አዲሰ ለተመሰረተው የኢትዮጵያና ኤርትራ ፌዴሬሽን ብሎም ለዘመኑ ዓለም አቀፋዊ ዐውድ የማይመጥን በመሆኑ በ1940ዎቹ ሁለተኛው የውክልና ፖለቲካ ክርክር ፈጠረ::[44] የዲሞከራሲ ፅንሰ-ሀሳብ በሰፊው የፖለቲካ ቋንቋ መሆን የጀመረው በዚህ ክርክር ላይ ነበር:: ይህም ክርክር ሁለተኛው በሕዝባዊ ውክልና ላይ የተደረገ ክርክር ነበር:: የክርክሩ ዋነኛ ይዘትም ምርጫ ምክር ቤቶች እና ፓረቲዎችን ጨምሮ በውክልና ፖለቲካ ዙርያ ነበር::[45] ዴሞክራሲ ሲባል የተቀላጠፈ አስተዳደር መመስረትና የውጪ ተፅዕኖን መቋቋም እንጂ ለህዝብ ሉዓላዊነትን ማረጋገጥ የሚለው ሀሣብ አልነበረም::[46] ሆኖም የሚደረገው አስተዳደር መሻሻል *ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎትና ምኞት እንዲከተል* የሚል አቋምም በክርክሩ ተሰምቷል::[47]

ይህም ክርክር የ1948 ዓ/ም. የተሻሻለ ሕገ-መንግስትትን ወለደ:: በዚህም መሠረት የተሻሻለ ሕገ-መንግስትት አንቀጽ 76 የሕግ መምርያ አባላት ለመጀመርያ ጊዜ በህዝብ እንዲመረጡ በማድረግ የሕዝቡን የመምረጥ መብት በከፊልም ቢሆን መለሰ::[48] ማሻሻያው *የህዝብ አስተሳሰብ እና አኗኗር አስኪሻሻል* የምርጫ መብትን

[43] *ዘውዴ ረታ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት 1ኛ መጽሐፍ 1923-1948* ሻማ ቡክስ አዲስ አበባ።2005 18-47

[44] *የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት* የጃንሆይን መንግሥት ለማሻሻል የሁለቱ ሰዎች (መኮንን እንዳልካቸው እና ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ) ፕላንና አቋም *ገፅ* 625-638 እና አበራ ጀምበሬ "የኢትዮጵያ ሕግጋተ መንግሥት አጭር ታሪካዊ ቅኝት" በውይይት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ማኀበር መጽሔት 3ኛ ሴሪ ቅጽ 2 ቁጥር 1 መጋቢት 1985 አዲስ አበባ *ገፅ* 55-67.

[45] ዘውዴ *ረታ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት 1ኛ መጽሐፍ 1923-1948* ሻማ ቡክስ አዲስ አበባ::2005 ፣633

[46] የጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ዕቅድ፣ የአክሊሉ ሀብተ ወልድ እና ይልማ ደሬሳን አስተያየት *የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት ገፅ፡ 633-634 ላይ ይመልከቱ ::*

[47] ለቢተውደድ መኮንን እንዳልካቸው አስተያየት *የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግስት ገፅ 627 ይመልከቱ ::*

[48] አበበ ወርቁ ሕገ-መንግሥትና የሥልጣን ክፍፍል *በውይይት* የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ማኀበር መጽሔት 3ኛ ሴሪ ቅጽ 2 ቁጥር 1 *መጋቢት* 1985 አዲስ አበባ *ገፅ* 67-78

ከሕዝብ አንስቶ መንግስት ራሱ በሞግዚትነት ሲሾም የቆየውን አሰራር አስቀርቷል። የተደረጉት ሁለት ክርክሮችም ለዚሁ ዘመን ወይይቶች ጥሩ ተሞክሮ ሊሆኑ ይችላሉ። ክርክሮቹ ያመጡት ለውጥ ወንበር በሲመት ብቻ ሳይሆን በምርጫም እንደሚገኝ ተግባራዊ ማሳያ ነበር። ይህ ምርጫ በየአራት አመቱ እየተካሄደ ወደ አብዮቱ ዘመን ደርሷል። በዚህ ዘመን ፖለቲካ ፓርቲዎች ገና ያልተመሰረቱበት ተመራጮችም ባለ ንበረት በሆኑ ግለሰቦች ተወላጅ (ዜጎች) የተወሰነና ተፅዕኖውም ደካማ ነበር። ዘመኑ መላው አፍሪካ ነፃነት መጎናፀፍ የጀመረበት ብቻ ሳይሆን የፓርቲ ስርዓት መመሠረት እና ዴሞክራሲ ማቆጥቆጥ የጀመረበት ሲሆንም የኢትዮጵያ የውክልና ፖለቲካ ዕድገት በንፅፅር ያን ያህል አኩሪ አልነበረም።[49] ይህ ያልዳበረ የውክልና ፖለቲካ ዕድገት የፈጠረው ቀዳዳ የ1953 መፈንቅለ መንግሥት ያስከተለው። የከሸፈው መፈንቅለ መንግሥት ለነበረው አስተዳደር የማንቂያ ደውል ሌላ የመሻሻያ ዕድል ቢሰጥም፣ ሦስተኛው ሕገ-መንግስት ማርቀቅ ቢጀመርም፣ አስተዳደሩ የተሰጠውን ጊዜ በማባከን ከአብዮቱን ሊቀድም አልቻለም።[50] *ማንኛውም አብዮት በተዳከመ እና በተቃወሰ የፖለቲካ ሥርዓት ጥላ ስር የፈጠራል* የሚባለው በኢትዮጵያ ታሪክ ሁሌም ይፈፀማል።[51]

ነገር ግን አብዮት እንደ ምርጫ የሚተነበይ ዑደት የለውም። የ1966 የኢትዮጵያ አብዮት አሮጌውን አገዛዝ አስወግዶ አዲሱን በተለየ አዲስ ስምምነት ሳይመሠረት ወታደራዊ አገዛዝ ራሱን የሰየመበት ኹነት ሆኖ አለፈ። አብዮት አሮጌውን ቢያስወግድም፣ አዲሱን ለመመስረት ሌላ የተለየ ጦር የማይፈታው ሲቪል የፖለቲካ ስሌት እና ጨዋታ ይጠይቃል። በድህረ አብዮት ዘመን አዲስ የሕዝብ ሉዓላዊነት የሚያረጋግጥ የውክልናም ሆነ ሰፊ ሕዝባዊ ዲሞክራሲ ሊመሠረት ይገባል። አብዮተኞች ግን ሁሌ ይሄን መረዳት ይሳናቸዋል።

የምርጫ ታሪክ በኢትዮጵያ ዘገምተኛ በሆነ ጉዞ ከአብዮት በኋላ በ1980 ብሔራዊ ሸንጎ ሲመሠረት እንደገና አዲስ የምርጫ ዘመን የጀመረ ቢመስልም ምርጫው በአንድ ፓርቲ ማለትም በኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) የብቻ ውድድር የተካሄደ ነበር። ከምርጫና የፓርቲ ፖለቲካ በላቀ ሁኔታ ብዙኃን ማኅበራት በተለይም የከተማ ነዋሪዎች እና የገበሬዎች ማኅበራት ጥሩ ጅምር በማኅበር

[49] Mohamed Salih. Introduction

[50] አበራ ጀምበሬ "የኢትዮጵያ ሕግጋተ መንግስት አጭር ታሪካዊ ቅኝት" በውይይት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ማኅበር መጽሔት 3ኛ ሴሪ ቅጽ 2 ቁጥር 1 መጋቢት 1985 አዲስ አበባ ገፅ 55-67

[51] Arendt Disobedience

የመሳተፍ ዕድል የፈጠረ ነበረ። ይህም ዕድል በደርግ ጥላ ስር እስኪገባ ድረስ። የደርግ ዘመን በሕዝብ ውክልና በምርጫ እና ዴሞክራሲ ረገድ ብዙ የሚባልበት ሥርዓት አልነበረም። ብዙም ሳይዘልቅ ሌላ ባለተራ 1983 ዓ/ም ሥልጣኑን በኃይል ነጥቋል። ከ1923-1983 ዓ. ም ያለውን ታሪክ ለመረመረ የምርጫ እና የውክልና ፖለቲካ በመርሕ ደረጃ ተቀባይነት ቢኖረውም፣ ማደግና መዳበር እየተሳነው ምናልባትም በኢትዮጵያ አብዮት እና ሕዝባዊ እምቢተኝነት ብቸኞቹ የሥልጣን ሽግግር ታሪክ ጸሐፍት፤ ኃይል ደግሞ ብቸኛ መዋቅራዊ የሥልጣን ምንጭ የሆነ ይመስላል።

የ1983ን መንግስት ለውጥ ተከትሎ የሽግግሩ ቻርተር በኋላም የ1987ቱ ሕገ መንግሥት ዋነኛ ፍልስፍና ወይም መርሆ ሕዝባዊ ሉዓላዊነት ነው። ይህም ሕዝባዊ ሉዓላዊነት የሚገለጸው *በውክልና ምርጫ እና በቀጥታ በሚደረግ ተሳትፎ* ነው።[52] የ1923ቱ ሕገ-መንግስት ረቂቅ መርሕ *የነበረው ሕዝቡ ከጥቃት ራሱን* እንዲያድን የታመነ መመከቻ እንዲኖረው ለመተዳደርያው የሚሆነውን መሪ ሐሳብ ራሱ በፈቃዱ እያማረጠ መቁረጥ እንዲቻለው በመርሕ ደረጃም ቢሆን የተደነገገው በዚሁ በ1987ቱ ሕገ መንግሥት ነበር። ሌሎቹ መርሆዎችም በቀጥታም ይሆን በተዘዋዋሪ ከውክልና ፖለቲካ፣ ከምርጫ እና ከመደራጀት መብት ጋር የተሳሰሩ ናቸው። ሕዝብ እንደራሴውን የመምረጥ ብቻ ሳይሆን እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው የማንሣት መብት ተደንግጓል።[53] በተለይም አንቀፅ 31 እና 38 የመምረጥ እና የመመረጥ መብትን፣ በተወካይ አማካይነት በሕዝብ አስተዳደር መሳተፍን፣ በፖለቲካ ደርጅቶች እና በሙያ ማህበራት መሳተፍን በሰፊው እውቅና ሰጥቷል።[54] በተጨማሪም በሕገ-መንግስቱቱ መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፤ *ሁሉ አቀፍ፣ ነፃ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በሚስጥር በሚሰጥበት ሥርዓት* በየአምስት አመቱ በሕዝብ መመረጥ አለባቸው።[55] እነዚህ እና ሌሎች የሕገ-መንግስትቱ አንቀጾች ለውክልና ፖለቲካ እና ዴሞክራሲ ሰፊ የሕግ ዐውድ በመፍጠር ተራማጅ ዘመንን አውጀው ነበር።

---

[52] አንቀጽ 8 የሕዝብ ሉዓላዊነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ 1987 ዓ. ም. አዲስ አበባ

[53] አንቀፅ 12 የመንግስት አሠራር ተጠያቂነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት

[54] አንቀፅ 31 የመደራጀት መብት እና አንቀፅ 38 የመምረጥ እና የመመረጥ መብት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ 1987 ዓ. ም. አዲስ አበባ

[55] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት፣አንቀጽ 54 ።

ለዚሁ ሕገ-መንግስትት መሠረት በሆነው የሽግግር ጊዜ በ1984 ዓ/ም. የመጀመርያው አካበቢያዊ ምርጫ የመድበለ ፓረቲ ሥርዓት መጀመር በማበሰር ሌላ የእድገት ምልክት አስመዘገበ። በዚሁ ጎን ለጎን የተጀመረው የውክልና ፖለቲካ ብዙዎችን በተለይ ነባር ፓርቲዎችን ያገለለ እና ከተካተቱትም የፖለቲካ ድርጅቶች ዋነኞች ከሽግግሩም እና ከምርጫው በውጣታቸው የተጀመረው የውክልና ፖለቲካው ከጅምሩ እንቅፋት ገጠመው።[56] ከጅማሬው የነበረው የፖለቲካ ግድፈት በኢህአዴግ አስተዳደር የተጀመረው ተራማጅ የፖለቲካ ጉዞ ሙሉ እንዳይሆን አድርጎታል።

በ1987ቱ ሕገ-መንግስት መሠረት አገራችን የብሔራዊ ምርጫ ዑደት በየአምስት አመቱ ነው።[57] እስካሁን ደረስ አምስት አገር አቀፍ ምርጫዎች ተካሂደዋል። በመጀመርያው አገር አቀፍ የመድብለ ፓርቲ ምርጫ 1987 ዓ/ም ተካሂዷል። ሁለተኛው 1992 ዓ/ም. የፖለቲካ ፓርቲዎች የምረጡኝ ዘመቻ እና የፖለቲካ ክርክር በመገናኛ ብዙሀን የተላለፈበት ነበር። ሦስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ 1997 የተካሄደው በብዙ መልኩ ብዙ ፓርቲዎች ያሠተፈ፣ በተለይ ከቅድመ ምርጫ እስከ ድምፅ መስጫ ዕለት ድረስ ሰፊ የሕዝብ ሉዓላዊነት መገለጫ የሆኑ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች የተደረጉበት፣ የኢህአዴግ አስተዳደር ተራማጅ ዘመን ነበር። በድኅረ ምርጫው ዘመን በሁሉም የፖለቲካ ሀይሎች የተወሰዱት እርምጃዎች የአገሪቱን የውክልና ፖለቲካ የዲሞክራሲ ጉዞ ያሥተጓጎለ፣ የኢህአዴግ አስተዳዳር በጉልህ ወግ አጥባቂ መሆን የጀመረበት ነበር። ይህም የውክልና ፖለቲካ በተለይም ምርጫ አንዱ የሕዝብ ሉአላዊነት መገለጫ ሆኖ የተጀመረው ጅማሮ እና በየአምስት አመቱ ተከታታይ አምስት ምርጫዎች መካሄዳቸው ጥሩ ስኬት ቢመስልም ከሦስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ በኊላ እደገቱ ተገቶ ከሕገ-መንሰግሰታዊ መንፈስ ተቃራኒ፣ ምክር ቤቶቹ የገዢው ፓርቲ ጠቅላላ ጉባዔ እነዲመስሉ አድርጓል።

ከጅምሩ የነበረው መዋቅራዊ ግድፈት ከሦስተኛው ምርጫ በኊላ እየሰፋ መጥቶ በቀጣዮቹ አራተኛ እና አምስተኛ አገር አቀፍ ምርጫዎች ስለውክልና ፖለቲካም ሆነ ሰለዲሞክራሲ እና ፓርቲዎች ዕድገት ማለት የሚቻለው ጥቂት ሆኖ ስርዓቱ ተመልሶ ወደ አንድ አውራ ፓርቲ ስርዓት የገባበት ዘመን ነበር። ይህ ሌላው የፖለቲካ ስርዓት በተግባር መፍረስ የፖለቲካ መህዳር መጥበብ እና የዲሞክራሲ ተቋማት መዘጋት ሌላ አብዮት እና ሕዝባዊ እምቢተኝነት እንዲሰፍን መንገድ

[56] Kassahun Berhanu. “Party Politics and Political Culture in Ethiopia”.

[57] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት፣አንቀጽ 54 ።

ከፈተ። ታሪካዊው የውክልና ፖለቲካ እና የአብዮት መፈራረቅ በዚህ ዘመንም ተደገመ። አሁንም አብዮት ሆነ ሕዝባዊ እምቢተኝነት የዲሞክራሲ ሆኔታዎችን ይፈጥራል እንጂ ዘለቄታዊ የውክልና ስርዓትን አይፈጥርም። የዲሞክራሲ ስርዓት የውክልና ፖለቲካ ጨዋታ የተለየ የፖለቲካ ስሌትን ይጠይቃል። ይህም በሕዝብ ሉዓላዊነት ከልብ ማመንን፣ በመድበለ ፓርቲ እና አማራጭ የሲቪል ተቋማት በመገንባት ምህዳሩን ማስፋትን ብሎም ለስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ሕጋዊ፣ ፖለቲካዊ እና አስተዳደራዊ ዐውዶችን ማሰናዳትን ይጠይቃል። *"ጊዜው ገና ነው፤ ያ እስኪሆን ድረስ"* እያሉ ምርጫን በፖለቲካዊ አመክኖ መሰረዝ ጠቃሚ አይደለም። ይህን ሲባል የምርጫውን ፖለቲካዊ ዋጋ እውቅና ሰጥቶ ሁሉም የፖለቲካ ሀይሎች ለምርጫው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል ማለት ነው።

## መጪው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምርጫ

መጪው የኢትዮጵያ 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ በስራ ላይ ባለው ሕገ-መንግስት መሠረት 2012 ግንቦት ወር መካሄድ ይኖርበታል። በሕገ-መንግስቱ መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፤ *ሁሉ አቀፍ፣ ነፃ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በሚስጥር በሚሰጥበት ስርዓት* በየአምስት ዓመቱ መመረጥ አለባቸው።[58] በምርጫው ውጤት መሠረትም አዲስ ምክር ቤት እና አስተዳደር ለቀጣይ አምስት አመታት ስልጣኑን ይረከባል። ይህ ሕገ-መንግስታዊ ሁኔታ ባለበት ሁኔታ ከሀገራዊ የፖለቲካ ሽግግር ጋር ተያይዞ *ምርጫው ይካሄድ ወይስ አይካሄድ?* የሚል የአደባባይ ክርክር እየተካሄደ ነው። ዜጎች እና የፖለቲካ ኃይላት ይህን ጥያቄ ሲያነሱ በጥቂቱ ሦስት ትርክቶችን ይገነባሉ። እነዚህም ሕጋዊ (ሕገ-መንግስትታዊ)፣ ፖለቲካዊ እና አስተዳደራዊ ትርክቶች ናቸው።

## ሕገ-መንግስትታዊ ትርክት

ብዙ ዜጎች እና የፖለቲካ ኃይሎች ሕገ-መንገስቱን በመጥቀስ ምርጫው በምንም አይነት ከተያዘለት ጊዜ ሊሻገር እንደማይችል እና ቢደረግም ኢ-ሕገ-መንግስታዊ ስለሚሆን ሕገ-መንግሥቱን የሚጠብቁ ኃይሎች ሕገ-መንግስታዊ ግዴታቸውን መወጣት እንዳለባቸው ይሞግታሉ። ሀሳቡን በቅን ልቦና የተሰነዘረ ከሆነ ምርጫን ማራዘም ኢዲሞክራሲያዊ እና የሕዝቦችን ሉዓላዊ ሥልጣን የመግፈፍ ሁኔታን ሊፈጥር ስለሚችል ስጋቱ ማንም ሰው ሊረዳው ይችላል። ሆኖም ከላይ በኢትዮጵያ የምክር ቤት ጅማሮ እንደነበረው የምርጫ ጊዜ ይለወጥ የተባለው *ጊዜው ገና ነው፤*

[58] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት፣ አንቀጽ 54

ያ እስኪሆን ድረስ ወይም ሕዝቡ እስኪነቃ አኗኗሩ እስኪቀየር በሚል ፖለቲካዊ አመክንዮ አይደለም። ከዚህ በተቃራኒው ለምርጫ ስኬት የሚያስፈልጉ ስራዎች አልተሰሩም። በዚሁ የሕግ ትርክት ስር ምርጫውን ለመካሄድ ሌላ ሕገ-መንግስታዊ ሁኔታ መሟላት አለበት ይላሉ። ይህንንም ለምሳሌ የሕዝብ ቆጠራ አለመካሄድ ምርጫውን ለማካሄድ ሕገ-መንግሥታዊ ዐውድ አልተዘጋጀም በማለት ምርጫው የሕዝብ ቆጠራ እስኪካሄድ መራዘም አለበት ይላሉ።

ምርጫው ሕገ-መንግሥታዊ ኹነት በመሆኑ ይካሄድ ከሚሉ ሀይሎች አንዳንዶቹ የሕዝብ እና ቤት ቆጠራ አይካሄድ የሚሉ የነበሩ ናቸው። በሕገ-መንግሥት አንቀፅ 103 መሠረት የሕዝብ ቆጠራ በየአሰር አመቱ መካሄድ እንዳለበት ይደነግጋል።[59] ይህም ምርጫ ቦርድ የምርጫ ክልሎችን ለመከለል ዋነኛ ግብዓት በመሆን ለምርጫው መካሄደ ቁልፍ ሚና አለው። የምርጫ ጉዳይ ስናነሳ አንዱን የሕገ-መንግስት ሀሳብ ብቻ ሳይሆን የሕገ-መንግሰቱን መንፈስ እና ፍልስፍና በጥቅሉ መመልከት አለብን። ምርጫው ይካሄድ ካልን ወደ ሕዝብ እና ቤት ቆጠራ በፍጥነት በማካሄድ ሕገ-መንግሥታዊ ሁኔታውን ማሟላት ግድ ይላል። ከሕገ-መንግሰታዊ መንፈስ ተነስተን ሰፊውን የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ (objective condition) መዳሰስም አለብን። ይህም ወደ ፖለቲካዊ ትርክት ይመራናል ።

## የፖለቲካዊ ትርክት

ከላይ እንዳያነው የፖለቲካ አመክንዮ የሚያቀርቡት ዜጎች እና ፓረቲዎች የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ (objective condition) ሁሉን አቀፍ፣ ነፃ፣ ቀጥተኛ ምርጫ ለማካሄድ አይፈቅድም። ይህም ሕገ-ምንግሥታዊ መንፈሱን በመጠበቅ ምርጫ ማካሄድ የሚያስችል ፖለቲካዊ ዐውድ የለም ይላሉ። ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታው እንደተገለጸው ልዩ እና ጤናማ ያልሆነ (exceptional) ከሆነ፣ ምርጫው የሚራዘመው ሕገ መንገሥቱን በማክበር እና ሕገ-መንግሥታዊነቱን ለመጠበቅ ይሆናል። የዚህ ሀሳብ አቅራቢዎች አሁን ያለው ነባራዊ የአገራችን ሁኔታ ለመተንተን የሚከተሉትን ትንተናዎች ይጠቀማሉ፤

1. ምርጫው ለማካሄድ የሚያስፈልገው ሲቪል ዐውድ ባብዛኛዎቹ ክልሎች ውስጥ የለም። በዙ ተጓዳኝ የታጠቀ ሚሊሻ እና ልዩ ኃይል ክልሎችን ኢ-ሲቪል የሆነ (supremacy of the armed forces) ሁኔታን ፈጥሯል። ይህ ከመደበኛ የመከላከያ እና የደህንነት ኃይል በተለየ ከፖለቲካ ግሉል ያልሆነ ኃይል ስለሆነ

[59] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት፣ አንቀጽ 103

ምርጫውን ሕገ-መንግሰታዊ ለማድረግ አዳጋች ይሆናል:: ምርጫ ለማካሄድ አንዱ ሁኔታ የሲቪል ዐውድ መፈጠር ነው::[60]

2. *ብዙ ክልሎች በአውራ ፓርቲዎች ቁጥጥር ስር መሆናቸው::* ሌላው ከላይኛው አመክንዮ ጋር የተያያዘው ትንተና ባለፉት ምርጫዎች ውጤት ምክንያት ክልሎች በአንድ አውራ ፓርቲ ቁጥጥር ስር መዋላቸው እና እያንዳንዱ ፓርቲ እንደ ቀደሙት መሳፍንት ክልሉን ርስት፣ ራሱን የክልሉ ሕዝብ ብቸኛ ተወካይ አድርጎ መቁጠሩ ለምርጫ የሚሆን ሜዳ በእንዲህ አይነት ክልል በማዘጋጀት ምርጫውንም ነፃ እና ገለልተኛ ማድረግ አይቻልም የሚለው ነው:: ለዚህም አንዳድ የክልል አመራሮች ይሄ ፓርቲ በክልሉ አይንቀሳቀስም ይሄኛው ዝግጅቱን በዚህ ከተማ አያዘጋጅም ማለታቸውን እንደ ማስረጃ ያቀርባሉ:: ይህ ድርጊት ምርጫውን በሕገ-መንግሥቱ መንፈስ መሠረት ለማከናወን እንቀፋት ይፈጥራል በማለት ይሞግታሉ::

3. *ሲቪል እና የብዙኃን ማኅበራት ገና መቋቋም ላይ ሰለሆኑ የምርጫ ሁኔታ የተሟላ አይደለም*:: ምርጫን የተሳካ ለማድረግ ወሳኝ የሆኑ ሲቪል እና የብዙኃን ማኅበራት የተዘጉ ወይም በመንግስት ቁጥጥር ስር የዋሉ በመሆኑ የመሻሻል ሰራዎች ገና በመስራት ላይ ናቸው:: አዳዲስ ተቋማትም ገና በመመስረት ላይ በመሆናቸው ለመጪው ምርጫ የሚጠበቅባቸውን ሚና መጫወት አይችሉም:: በምርጫ መታዘብ እና በማንቃት ስራ ላይ የሚጠበቅባቸው ሚና መጫወት አይችሉም::

4. *ሰፊው ሕዝብ ለምርጫው ዝግጁ አይደለም*:: ሌላው ሰፊው ሕዝብ ካለው ፖለቲካዊ ትኩሳት እና አካባቢዊ ግጭት ምክንያት ለምርጫው ዝግጁ አይደለም:: ይህም በተለይ ዜጎችን መፈናቀል ፣ የክልሎች ወይም ክልሉን የሚመሩት ፓርቲዎች ፉክክር ሕዝቡንም ሆነ ፖለቲካዊ ዐውዱን ለምርጫ ምቹ እንዳይሆን አድርገውታል::

5. *የፖለቲካ ፓርቲዎች ዝግጁ አይደሉም*:: የፖለቲካ ፓርቲዎች አዲሶቹም ሆነ ነባሮች አብዛኞቹ በለውጥ ውስጥ ስለሆኑ ለምርጫው መዘጋጃ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል:: ይህ ሁኔታ ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግን ጨምሮ ለምርጫው ያልተዘጋጁ መሆኑ ከላይ ለሚከሰቱት ክልላዊም ሆነ አገር አቀፍ ችግሮች እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ::

እነዚህ በአምስት የተከፈሉ የአገሪቱ የፖለቲካ ዐውድ የተለየ ጤናማ አለመሆኑን የሚያስረዱ ሀሳቦቸ ከሞላ ጎደል እውነት ሊሆኑ ይችላሉ:: ነገር ግን ሁሉም ዞሮ ዞሮ የሚሄደው በቅድሚያ አገሪቷን ተረክቦ በማስተዳደር ላይ የቆየው የኢህአዴግ አስተዳደር ነው:: ይኸውም በብሔራዊም ሆነ በክልል ደረጃ ሕገ-መንግስታዊ ዐውድ መፍጠር ግዴታው በመሆኑ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት በተለይም በኢህአዴግ አባል

60 Bratton, M. and Van de Walle, N. Democratic experiments in Africa: regime transition in comparative
perspective. New York: Cambridge University Press, 1997.

ወይም አጋር ድርጅቶች የሚፈጠሩ ኢ-ሕገ-መንግሰታዊ ድርጊቶች ማስቆምና ለምርጫም ሆነ ለዘላቂ የመድብለ-ፓርቲ እንቅስቃሴ ምቹ ምሕዳር መፍጠር አለበት። ድርጅቱ ራሱን የማደስ እና መንግስታዊ ማሻሻያ የማድረግ ዕድል በአግባቡ ተጠቅሞ ለፖለቲካ ሽግግሩ ታሪካዊ ሚና መጫወት ይጠበቅበታል። ይህን ማድረግ ብቸኛው አማራጭ በመሆኑ እነዚህን ስራዎች የ6$^{ኛው}$ ሀገራዊ ምርጫ ዝግጅት ፍኖተ ካርታ ጋር ማካተት ኢህአዴግ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ ከሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች እና ከሕብረተሰቡ ጋር መስራት ይጠበቅበታል።

## አስተዳደራዊ ትርክት

ምርጫ ሕገ-መንግስታዊ እና ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን አሰተዳደራዊ ኹነትም ነው። በዘመናችን ምርጫ ቲክኒካል ሂደቱ ውስብስብ፣ በቴክኖሎጂ የሚታገዝ እና ብዙ ባለሙያዎችን የሚጠይቅ ሆኗል። ምርጫውን ለማስፈፀም ዋና ሚና ያላቸው ተቋማት በተለይም የምርጫ ቦርድ የሽግግር ጊዜውን ጨርሶ ወደ ምርጫ ዝግጅት የሚገባበት ጊዜ አስተዳደራዊ ትንተና እና መልስ ይጠይቃል። የአስተዳደር ጉዳይ ምንም እንኳ ከፖለቲካ ጉዳይ ባይርቅም የምርጫ አስተዳደር የሚጠይቀው ወስብስብ ሂደት ከአሰተዳደር ባለሙያዎች፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሰፊውን ሕዝብ ባሳተፈ መልኩ ሊመከርበት ይገባል። የምርጫ ቦርድ የተጣለበት ሕገ-መንግስትታዊ ሀላፊነት ለመወጣት ያለውን ዝግጁነት ቴክኒካዊ እና አስተዳደራዊ ብቃት በግልፅ ማሣወቅ ይጠበቅበታል። ይህንም ለማድረግ በጊዜ ገደብ የተወሰነና ተአማኒነት በሚያሰፍን ሁኔታ ሽግግሩን ጨርሶ አሰተዳደራዊ አቅሙን በቶሎ መገንባት ይኖርበታል። ይህ ከተደረገ "የምርጫው ጊዜ ይራዘም" የምንልበት አስተዳደራዊ አመክንዮ አይኖርም ማለት ነው። ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ በአሰተዳደራዊ ምክንያት በጥቂት ወራት ምርጫውን ማራዘም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ይህ ካልሆነ ምርጫው በሕጉ መሠረት ይደረግ ብንል እንኳ የሕዝቦችን የፖለቲካ መነቃቃት እና ተሳትፎ በአግባቡ ሳንጠቀም ወደተለመደው የድህረ ምርጫ የግጭት አዙሪት ሊከተን ይችላል።

## እንደ መደምደሚያ

ምርጫው ይካሄድ ወይስ አይካሄድ የሚለው አንጉል ጥያቄ ፖለቲካ ፓርቲዎች እና ግለሰቦች ካሉባቸው ግላዊ ዐውድ በመነሳትና በተነጠለ ምክንያት ከመከራከር ከብዙ ሁኔታዎች ማለትም ከሕግ እና ሕገ-መንግስት፣ ከፖለቲካ ዐውድ እና ከምርጫ አስተዳደር ጉዳዮች መተንተን ይጠይቃል። በዚህ ጽሁፍ ውሰጥ ለመግለጽ የተሞከረው ከአገሪቱ የውክልና ፖለቲካ፣ የምርጫ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ታሪክ በመነሳት መዋቅራዊም ሆነ ተቋማዊ ችግሮችን በመጠቆም ዛሬ

እንደ አዲስ የሚቀርቡ ፖለቲካዊ ችግሮቻችን ነባር እና ለስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ መራዘም ምክንያት እንዳይሆኑ ይሞግታል። አብዛኞቹ ችግሮቻችን በሂደት በረጅም ጊዜ የምንፈታቸው ጉዳዮች እንጂ፣ በአጭር ጊዜ የሚታከሙ ደራሽ ችግሮች አይደሉም። ለምሳሌ በመሳፍንቱ ሲራመድ የነበረው *የብቸኛ የሕዝብ ተወካይነት ሥልጣን* ዛሬ ከፓርቲዎች ልሣን ስንሰማ ችግሩ ሰሞነኛ ብቻ አለመሆኑን መረዳት ያስችለናል።

ሰሞነኛ ችግሮችም ቢሆኑ ራሱን እንዲያድስ ዕድል የተሰጠው የኢህአዴግ አስተዳደር በቁርጠኝነት በመፍታት ለ6[ኛው] ሀገራዊ ምርጫ መሳካት ሚናውን ሊጫወት ይገባል። ኢህአዴግ በውስጡ ያሉ ችግሮችን ፈትቶ እንደ አንድ ተራማጅ ፓርቲ ከታሪክ ጋር አብሮ መጓዝ ይጠበቅበታል። ይህን በማድረግ እና ሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎችን በማስተባበር ሰላማዊ እና በየአምስት ዓመቱ የሚካሄድ ምርጫ ብቻ ሳይሆን ሕገ-መንግስትታዊ፣ ነፃ እና ፍትሀዊ ምርጫ ማካሄድ ያስችላል። ሰሞነኛ ጉዳዮች ከፖለቲካ ማሻሻያ ስራዎች ጋር ብቻ ሳይሆን ከዝግመታዊ ለውጥ ከሚካሄደው የዲሞክራሲ ታሪክ ስለሚመነጩ በቶሎ ይፈታሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም።

መጪው ሀገራዊ ምርጫ በኢትዮጵያ እስካሁን ለተካሄደው አዎንታዊ ጉዞ ወሳኝ ነው። የፖለቲካ ማፍታታት ሂደት ለረጅም ዘመን ዘላቂ የፖለቲካ ሽግግር እንዲተካ ምርጫውን በስኬት ማካሄድ ወሳኝ ነው። ፖለቲካ ፓርቲዎችም ቀጣዩን አሻጋሪ ምርጫ ከታሪካዊ እና ነባራዊ ሁኔታ በመመልከት ወንበር ከማግኘት ያለፈ ራዕይ ይዘው ሊንቀሳቀሱ ይገባል። ሀገራዊ ምርጫ ለሕዝቡ የፖለቲካ መጀመርያ ወይም መጨረሻ አለመሆኑን መረዳት እና ሌሎችን ማስረዳት ከፖለቲካ ኃይሎች ይጠበቃል። በድህረ ምርጫ ለሚካሄድ የዕለት-ተዕለት ሕዝባዊ ፖለቲካ ሁሉም ፓርቲዎች እና ሌሎች ሲቪል ማሕበራት ዝግጁ ከሆኑ መጪው ምርጫ የረጅሙ የፖለቲካ ሕይወታችን አንዱ ክፍል አድርገን ለፖለቲካ ማሻሻያ ደግሞ አሻጋሪ አድርገን ልንመለከተው እንችላለን።

# የውይይቱ ፕሮግራም

| | የውይይት ርዕስ | የውይይት ቀን | የውይይት ሠዓት |
|---|---|---|---|
| 1. | ሕገ-መንግስትት፤ ብሔር-ተኮር ፌድራሊዝም እና ፖለቲካዊ ሪፎርም | ግንቦት 29 ቀን 2011 | ከጥዋቱ 3፡00 - ከቀኑ 7፡00 |
| 2. | የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሕዝባዊ ምርጫና የህዝብ ውክልና በኢትዮጵያ | ሠኔ 27 ቀን 2011 | ከጥዋቱ 3፡00 - ከቀኑ 7፡00 |
| 3. | የማክሮ-ኢኮኖሚ ፖሊሲ እና በኢኮኖሚ ውስጥ የመንግስት ሚና | ነሐሴ 2 ቀን 2011 | ከጥዋቱ 3፡00 - ከቀኑ 7፡00 |
| 4. | የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ማዛወርና የኢኮኖሚ መዋቅር ማሻሻያ | መስከረም 08 ቀን 2012 | ከጥዋቱ 3፡00 - ከቀኑ 7፡00 |
| 5. | የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በአፍሪካ ቀንድና መካከለኛው ምስራቅ | ጥቅምት 13 ቀን 2012 | ከጥዋቱ 3፡00 - ከቀኑ 7፡00 |
| 6. | የአባይ ወንዝ ውሀ አጠቃቀምና የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ | ሕዳር 11 ቀን 2012 | ከጥዋቱ 3፡00 - ከቀኑ 7፡00 |

# የመወያያ ፅሁፎቹን ያቀረቡ ምሁራን



**ዶ/ር አሰፋ ፍስሀ** በአዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የፌዴራሊዝም እና አስተዳደር ማዕከል ተባባሪ ፕሮፌሰር ናቸው። ኣንድ መፅሀፍ ፌዴራሊዝም እና የብዝሀነት ተካታችነት በኢትዮጵያ፡ንፅፅራዊ ጥናት (እ.ኤ.አ. 2006) እና 20 ጥናታዊ ፅሁፎች በታዋቂ መጽሔቶች አሳትመዋል።



**ዶ/ር ዘመላክ አይተነው** በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፌዴራሊዝም እና አስተዳደር ጥናት ተባባሪ ፕሮፌሰር እና የማዕከሉ ዳይሬክተር ናቸው። በተጨማሪም የማስትሬት እና የፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪዎች በተቀበሉበት በምእራብ ኬፕ (ዩ.ደብሊው.ሲ) ዩኒቨርሲቲ ዱላ ኡመር ኢንስቲትዩት ውስጥ በልዩ ሁኔታ ተባባሪ ፕሮፌሰር ናቸው። ዶ/ር ዘመላክ፣በአካባቢያዊ አስተዳደር እና በፌዴራል ሥርዓቶች ዙሪያ ከ 15 በላይ ጥናታዊ ፅሁፎችን እና የመጽሐፎችን ምዕራፎች በታዋቂ መጽሔቶች አሳትመዋል። በወቅታዊ የፖለቲካ እና ህገ-መንግስታዊ ጉዳዮች ላይ በተለያዩ ጋዜጦችም እንዲሁ በርካታ መጣጥፎችን አውጥተዋል።



**ፕሮፌሰር ካሳሁን ብርሀኑ** በአዲስ አባባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለምአቀፍ ግኑኙነት ትምህርት ክፍል ፕሮፌሰር ሲሆኑ ላለፉት 30 አመታት የአዲስ አባባ ዩኒቨርስቲን በመምህርነትና እና በአስተዳደረዊ ስራዎች ሲያገለገሉ ቆይተዋል። ፕሮፌሰር ካሳሁን አለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ስመጥር የጥናት መፅሄቶች ላይ ከማህበራዊ ሳይንስ በተለይም ከፖለቲካ ሳይንስ ጋር የተገናኙ የምርምር ጽሁፎችን አሳትመዋል። ካሳተሟቸውም ጽሁፎች ውስጥም ያለተማከለ ስርዓት እና የመንግስት አስተዳደር፤ የመንግስት እና ህብረተሰብ ግኑኝነት። የሰላም ግንባታና ግጭት፤ የከፍተኛ ትምህርት አስተዳደር። የግብርና ፖሊሲ ፖለቲካል ኢኮኖሚ፣ ምራጫና የምርጫ ሲስትሞች፤ ህገ-መንግስታዊነትና የፓርቲ ፖለቲካ በዋናነት ይጠቀሳሉ።



**ዶ/ር ዮናስ አሽኔ** በአዲስ አባባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለምአቀፍ ግኑኙነት ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ናቸው። የፒኤችዲ ዲግሪያቸውን በ ኢንተርዲሲፕሊናዊ ማህበራዊ ሳይንስ ከ ማካሬሬ ዩኒቨርስቲ የተመረቁ ሲሆን፤ የጥናትና ምርምር ትኩረታቸውም በዋነኝነት የፖለቲካ ቲዮሪ እና ታሪካዊና አንጻራዊ ፖለቲካ በመንግስትና ማህበረሰብ ግኑኝነት በአፍሪካ በተሰኙ እርእሶች ላይ ያጠነጥናል።